# እንከን-የለሹን ጎዳና አገኘሁት

በ ዶ/ር ሙሐመድ አል-ቲጃኒ አል-ሰማዊ

ትርጉም፡-

ጣሂር መሐመድ አል-ጎዳነምቢ

# እንከን-የለሹን ጎዳና አገኘሁት

በ ዶ/ር ሙሐመድ አል-ቲጃኒ አል-ሰማዊ

ትርጉም፡-

ጣሂር መሐመድ አል-ጎዳነምቢ

**ማውጫ** **ገጽ**


ስለ መጽሀፉ ........ 1

መታሰቢያነቱ ........ 2

መግቢያ ........ 4

አጭር የሕይወት ታሪኬ ........ 5

ወደ አላህ ቤት የተደረገው ታሪካዊ ጉዞ ........ 8

በግብጽ አገር ........ 20

የመርከቡ ላይ ትውውቅ ........ 24

በኢራቅ ያደረግሁት የመጀመሪያ ጉብኝት ........ 31

አብዱልቃር አል-ጂላኒና ሙሳ አል-ካዚም ........ 33

ጥርጣሬና ጥያቄ ........ 43

በአል-ነጀፍ የተደረገ ጉብኝት ........ 50

ከአል-ኡለማ (ምሁራን) ጋራ የተደረገ ስብሰባ ........ 53

ከአል-ሰይድ መሀመድ ባቂር አል-ሰድር ጋራ መገናኘት ........ 62

ጥርጣሬና መምታታት ........ 75

የሂጃዙ ጉዞ ........ 84

ጥናትና ምርምሩ ተጀመረ ........ 99

የዝርዝር ጥናቱ መጀመር ........ 102

የነቢዩ ሰሃቦች በሺአና በሱኒዎች አይታ ........ 102

ሰሃቦቹ በአል-ሁደይቢያህ የሰላም ስምምነት ........ 108

ሰሀቦቹና ራዚያት የውም አል-ኸሚስ (የሀሙሱ አሳዛኝ ገጠመኝ) ........ 112

የኡሳማህ በጦር መሪነት መሾምና የሰሀቦቹ ሁኔታ ........ 120

ስህቦችን በተመለከተ የቁርአን አስተያየት.......... 137
ወደኋላ መመለስን የሚያወሳው አንቀጽ .......... 139
የቅዱስ ጦርነት (ጂሃድ) አንቀጽ.......... 141
አጅ መስጠት.......... 143
ስህቦችን በተመለከተ የመልዕክተኛው አስተያየት.......... 144
የኩሬው ሀዲስ (የሀውድ ሀዲስ) .......... 144
ለዚህ ዓለም ስለመፎካከር የሚያወሳ ሀዲስ.......... 145
ስሀቦች እርስ በራሳቸው ላይ የነበራቸው አስተያየት.......... 147
የነቢዩ ሱናህ ስለመቀየራቸው ራሳቸው
የሰጡት ምስክርነት.......... 147
ስሀቦቹ በሰላት ላይ እንኳ ለውጥ አድርገዋል.......... 152
ስሀቦች በራሳቸው ላይ ሲመሰክሩ .......... 154
ሁለቱ ሽይኮች በራሳቸው ላይ የሰጡት የምስክር ቃል.......... 154
የለውጡ መጀመሪያ.......... 171
ከአንድ ምሁር ጋር ያደረግኩት ውይይት.......... 173
ከተሃድሶዬ ጀርባ የነበሩ ምክንያቶች.......... 189
ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ የኸሊፋነቱን ቦታ ርክክብን
በተመለከተ የተቀመጠው ሐዲስ.......... 190
በፋጡማና በአቡበክር መካከል የነበረው አለመግባባት.......... 193
የመሪነቱ ቦታ ከማንም በላይ ለአሊ የሚገባ ስለመሆኑ.......... 197
አሊን መከተል እንደሚገባ የሚያሳዩ የነቢዩ ሐዲሶች.......... 204
«እኔ የዕውቀት ከተማ ነኝ፣ አሊ ደግሞ መግቢያው
በር ነው» የሚለው የነቢዩ ሐዲስ.......... 204
«ዓሊ ሆይ! አንተ ከኔ እንዣር ያለህ ቦታ ነቢይ

ያለመኖሩ እንጂ ሐሩን ለሙሳ ያለው ቦታ
ዓይነት ነው፡፡» የሚለው ሐዲስ.................................................... 207
«እኔ አለቃቸው ለሆንኩት ሁሉ አሊም አለቃቸው ነው፤
አላህ ሆይ! እሱ የሚወደውን ውደድ፣ እሱ የሚጠላውን
ጥላ፣ የሚረዳውን እርዳ፣ ከእሱ የሚለየውን ተለየው፤
በዞረበት ሁሉ እውነትን ከርሱ ጋር አድርግ»
የሚለው ሐዲስ.. ........................................................................ 207

«አሊ ከእኔ ነው እኔም ከአሊ ነኝ፤ ከእኔ ከራሴና ከአሊ
በስተቀር የኔን ተግባር ማንም ሊያከናውን
አይችለውም፡፡»የሚለው ሐዲስ.................................................... 209
የማስጠንቀቂያው ቀን የቤቱ ሐዲስ.............................................. 210
አህሉል ቤይትን መከተል ግዴታ መሆኑን የሚያሳየው
ትክክለኛ የነቢዩ ሐዲሶች........................................................................ 211
«ሁለቱ ሚዛን የሚደፉ ነገሮች» የሚለው ሐዲስ..................211
ስለመርከቡ ምሳሌ የተነገረ የነብዩ ሐዲስ..............................225

«አንደ እኔ ለመኖር የሚመኝ» የሚለው የነብዩ ሀዲስ...........227
ግልጽ በሆኑ ነገሮች ላይ የግል አስተያየት በመስጠት
ያጋጠመውን ችግሮቻችን (ነስን የሚጋፈጡ እጅቲሀድ
የሚያመጣው መዘዝ)................................................................................231

«አህል አል-ሱናህ ወ አል-ጀማዓህ» የተሰኙትን ቃላት
በመጀመሪያ የተጠቀመው ማን ነበር?...................................................... 241
በምርምር ጥናቱ እንዲሳተፉ ለወዳጆች የተደረገ ጥሪ ....................... 243
ወደ እውነት የሚመራ ሐቅ ................................................................... 250
ዋቢ መጻሕፍት........................................................................................ 264

# ስለ መጽሀፉ

ምንም እንኳ ሁሉም የእስልምና ቡድኖች (መዝሀቦች) የየራሳቸውን እምነቶች ወደ «እውነተኛ መንገድ» የሚመራ ነው ቢሉም ይህ መጽሐፍ «እውነት» እና «እውነተኛውን መንገድ» ከነዚህ ከተለያዩ የእስልምና ክፍሎች ውስጥ ይዳስሳል (መርምሮ ያወጣል)። ይሁን እንጂ አንዱና ብቸኛው «የእውነት መንገድ» ያቀፈውን ፍጹም የሆነውን እውነት የሚያውቀው አላሁ ተአላ ነው። ከእዉነት ሌላ ያለዉ ነገር ደግሞ ጥመት ብቻ ነዉ። ያ እዉነት ግን አንድ እና አንድ ብቻ ነዉ። ያ የእዉነት ጎዳና አንድ ብቻ ነዉ። ከእውነት ያፈነገጠ ነገር ቢኖር በተሳሳተ ነገር መመራት ብቻ ነው።

ይህ መጽሐፍ የአንድ ቀና የሆነ «እውነት ፈላጊ፣ እና ወደ ቀና መንገድ» የተመራ ሰው ጥረት ነው።

«***ወደ እኛ መንገድ ለሚያመራው ለዓላማችን የሚቆምና የሚጥረውን ሁሉ እንመራዋለን። አላህ በእርግጥም ከትክክለኞቹ ጎን ነው***»። (ቅዱስ ቁርዓን 29:69)።

እያንዳንዱ ሀቀኛ ሙስሊም ይህን መጽሐፍ በአጽኖት እንዲያነብ ጥሪ ተላልፎለታል። ምክንያቱም ዋነኞቹ የእስልምና ክፍሎች ስሚለያዩባቸው አበይት ጉዳዮች ግልጽ የሆኑ ማስረጃዎችንና መልሶችን ስለያዘ ነው።

## መታሰቢያነቱ

ይህቺ መጽሐፌ የምታኩራራ ትልቅ ስራ ሳትሆን ቀለል ያለች ስራ ነች፡፡ ስለ አንድ ጉዞ የምታወሳ፣ ቴክኒካዊ ወይም ተፈጥሮአዊ ግኝትን ሳይሆን ሃይማኖታዊና የተለያዩ የፍልስፍና ትምህርት ቤቶችን ተመርኩዛ ስለአዲስ ግኝት የምትተርክ ናት፡ በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱ ግኝት የሰውን ልጅ ከሌላው ፍጡር ከሚለየው ጤናማ አዕምሮና ግልጽ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ እኔም ይህቺን መጽሐፍ ለእያንዳንዱ ጤናማ አዕምሮ እንደማስታወሻነት ለማበርከት እፈልጋለሁ፡፡

እውነትን በተግባር ከሚፈትን፣ ስህተት የሚያስከትለውን ውድመት ለሚገነዘብ አዕምሮ፣ በፍትህ ሚዛን ውስጥ የሚነገረውን ሁሉ አመዛዝኖ ምንጊዜም ቢሆን ምክንያታዊ የሆነውን ነገር ለሚቀበል አዕምሮ፣ ቃላትንና አባባሎችን አወዳድሮ ምክንያታዊ የሆነውን ካልሆነው፣ ጠንካራውን ከደካማው የመለየት ችሎታ ላለው አዕምሮ፡፡ ከሁሉም በላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል፡፡ «***አባባሎችን (የተነገሩትን ሁሉ) አድምጠው ምርጥ የሆኑትን የተከተሉ፣ እነሱ ናቸው በአላህ የተመሩ መልካምም ግንዛቤ ያላቸው፡፡***»

ይህችን መጽሐፍ ለማስታወሻነት ላበረከትኩላቸው ሁሉ ከምንም በላይ የሆነው አላህ ምስጋና ይግባውና ከአይኖቻችን በፊት አዕምሮአችንን ክፍት እንዲያደርግልንና እንዲመራን፣ ልቦናችንን ብሩህ እንዲያደርግልን፣ ትክክለኛ ውን መንገድ እንድንከተል በግልጽ እንዲያሳየን፣ በአንፃሩም የተሳሳተውን መንገድ በግልጽ አሳይቶን ገሸሽ እንድናደርገውና ከእሱ መልካም አገልጋዮች እኩል እንዲቀበለን ምኞታችን ነው፡፡ አላህ የባሪያዉን ተማጽኖ የሚሰማ እና ምላሽም የሚሰጥ ጌታ ነዉ፡፡

## መግቢያ

የሰማዩ ጌታ ለሆነው አላህ ምስጋና ይግባውና ሰውን ከጭቃ ፈጥሮ ውብ አድርጎ ቀረፀው:: ከሌሎች ፍጥረታት አስበልጦም ስለወደደው ለሱ ቅርብ የሆኑትን መላኢካዎች እንዲሰግዱለት አደረገ:: ጥርጣሬውን ፍፁም በሆነ እምነት እንዲተካው የሚያስችለውን አዕምሮ አጎናፀፈው:: ሁለት ዓይኖች፣ አንድ ምላስና ሁለት ከናፍር ለግሶት ሁለት መንገዶችንም (ቀናና መጥፎ) ለይቶ መራዉ:: መልካም ዜና የሚያበስሩና የሚያስጠነቅቁ እንዲሁም ከተረገመዉ ዲያብሎስ ጥመት እና እኩይ ተግባር ይጠነቀቁ ዘንድ መልዕክተኞችን ላከለት:: ሸይጣን ጠላቱ ስለሆነ እሱን እንዳያመልክ ቃል አስገባዉ:: አሳማኝ በሆነ እምነትና በበቂ ግንዛቤ አላህን ብቻ እንዲያመልክና የሱን ትክክለኛ ጎዳና እንዲከተል ነገረው:: ያለ ምንም ማስረጃ እና ዕዉቀት ቀድሞ የነብሩትን ሰዎች የተከተሉትን የቀደምት አባቶች፣ ጓደኞችና አዝማድ መንገድ ጋር በእምነቱ እንዳይመሳሰል (ተቅሊድ እንዳያደርግ) አስጠነቀቀዉ:: «***ወደ አላህ ፊቱን ካዞረ፣ ጥሩ ሥራዎችንም ከሠራ፣ ብሎም ከሙስሊሞቹ አንዱ ነኝ ካለው ሰው ሌላ ምን የተሻለ የሚናገር ይኖራል***» (ሱራህ ፉሲለት፡ 33)

ለህዝቡ ምህረት ላስገኘ፣ የደካሞችና የተጨቋኞች አጋር ለሆነ፣ ከመሀይምነት ጨለማ የሰውን ልጅ ሁሉ ላወጣን፣ ወደ አማኞቹና መልካሞቹ ብሩህ ጎዳና ለሚመራ ታላቁ መልዕክተኛ የአላህ ሰላትና ሠላም ለእሱ ይውረድ::

የሙስሊሞቹ ነቢይና ብቸኛው አጋፋሪ የእኛ አለቃ መሐመድ ኢብን አብደላህ ላይና እንዲሁም አላህ ከመላው አማኞች መካከል ለመረጣቸው

ከአሳቸው አብራክ ለተገኙት ለመልካሞችና ለጠሩት ትውልዶቹ ሰላትና ሰላም ይሁን። አላህ እነሱን ካጠራቸውና ስህተት አልባ ካደረጋቸው በኋላ እንወዳቸው ዘንድ ቁርዓን ውስጥ በአጽንኦት ገልጾታል። የእነሱን (የአህሉል ቤይት) መርከብ የተሳፈረ እንደሚድንና በመርከቡ ያልተሳፈረ ሁሉ እንደሚጠፉ ቃል ገብቷል። ከሱ ጎን ለቆሙት፣ ላከበሩት፣ ለእስልምና ድልና ለእሱም ሲሉ ለተሰውት ክቡር ጓዶቻቸው ሶላትና ሰላም ይሁን።ሀቅን በማወቃቸዉ ቃል ኪዳናቸዉን በደስታ ለሰጡት (በይዓ ያደረጉ)፣ የሀቁን መንገድ ሳይቀይሩ እስከ መጨረሻዉ በጽናት ለቆዩና አመስጋኝ ለነበሩት ሁሉ ላይ በረከትና ሰላም ይዉረድ። ለእስልምናና ለሙስሊሞች ለሰጡት ግልጋሎት አላህ ምንዳቸውን ይክፈላቸው። አሁንም የአላህ ቡራኬዎችና ሠላምታዎች ለተከታዮቻቸውና በብርሀናቸዉ እስከ መጨረሻዉ ለተመሩት ሁሉ ይሁን።

አላህ ሆይ! አንተ ሁሉንም የምትሰማ፣ ከሁሉም በላይ አዋቂ ነህና እባክህ ልመናዬን ተቀበለኝ። አላህ ሆይ! ወደ ፍፁም እውነት የምትመራን አንተ ነህ፣ እባክህ ልቤን ብሩህ አድርግለኝ። ጌታዬ ከታማኞቹ አገልጋዮችህ መካከል መርጠህ ጥበብን የምትለግስ አንተ ነህና እባክህ ራሴን በትክክል እንድገልጽ እርዳኝ። እባክህ ጌታዬ ተጨማሪ ዕውቀትን ለግሰኝና ከመልካሞች ጋራ ደብለኝ።

## አጭር የሕይወት ታሪኬ

አባቴ ለመጀመሪያ ጊዜ በረመዳን ወር የአል-ታራዊህ ሰላት ሥነ-ሥርዓት ወደሚከናወንበት አካባቢያችን ከሚገኝ መስጊድ የወሰደኝን ዕለት እስከ አሁን አስታውሰዋለሁ። የዛን ጊዜ የአሥር ዓመት ልጅ ነበርኩኝ። አባቴ እያዞረ ለሰዎች ሲያስተዋውቀኝ ሰዎቹ በሙሉ አግራሞታችዉን መደበቅ አልቻሉም ነበር።

አስተማሪዬ፣ የአል-ኢሽፋዕ[1] ሶላት ለተከታታይ ሁለት ወይም ሦስት ምሽቶች እንድመራ ፕሮግራም ይዞልኝ እንደነበረ ቀደም ብዬ አውቄያለሁ። ከአካባቢው ልጆች ጋር በመሆን ከሰውየው ኋላ በመኮልኮል ሰላት እያደረስን የቁርዓን ሁለተኛው አጋማሽ ማለትም ሱራህ መርየም ላይ የሚደርሱትን ኢማም መጠበቁ የተለመደ ነገር ነበር። ቁርዓንን ትምህርት ቤት ገብተን መማራችንን እንዲሁም እቤት ውስጥ ደግሞ ቁርዓንን በቃሉ በሚያነበንብ ዘመዳችን ከሆነ አንድ ዓይነ-ስውር ተጨማሪ ትምህርት ማግኘታችንን አባቴ በደንብ ይከታተላል። ገና በልጅነቴ ቁርዓንን መቅራት በመቻሌ አስተማሪዬ በመደሰቱ በምቀራበት ወቅት የሩኩዕ ቦታዎችን ሊያስተምረኝ ጥረቱን ተያያዘው። መመሪያዎቹን በደንብ መረዳቴን ለማረጋገጥ በተደጋጋሚ ይፈትነኝም ነበር።

እንደተጠበኩት ሁሉ ፈተናውን ሁሉ በሚገባ በማለፌ ሰላትን መምራቴንና መቅራቴን በማጠናቀቁ ሰው ሁሉ እየመጣ እኔንና አባቴን እንኳን ደስ ያላችሁ በማለት አስተማሪዬን ለፍሬያማ ጥረቱ አመስግነውት እስልምናን ለሰጠን አላህም ተገቢውን ምስጋና አደረሱ።

ከዚህ በኋላ የነበሩት ቀናት ትዝታዎች እስከዛሬም ድረስ ከኔ አልተለዩም፡፡ ከፍተኛ አድናቆትን አግኝቼ ዝናዬም ከመንደራችን አልፎ በከተማው ሙሉ ተሠራጩ፡፡ እኒያ የረመዳን ምሽቶች እስከዛሬ ድረስ ሃይማኖታዊ ምልክቶችን በኔ ላይ እንደጣሉ ናቸው፡፡ የተምታታ ሁኔታ ውስጥ በገባሁበት ጊዜ ሁሉ አንድ እንግዳ የሆነ ሃይል ጎትቶ አውጥቶ ወደ ትክክለኛው መንገድ ሲመራኝ ይሰማኛል፡፡ የነፍስያ ድክመት እንዲሁም የሕይወት ትርጉም የለሽነት በተሰማኝ ጊዜ እኒያ ትዝታዎች ፊቴ ላይ ይደነቁና ወደ መንፈሳዊ ደረጃ ከፍ አድርገውኝ ሀላፊነቴን ከግቡ ለማድረስ እንዲቻለኝ የእምነትን ፋና በንቃተ ህሊናዬ ውስጥ ይለኮሳሉ፡፡

በአባቴ ወይም በአስተማሪዬ የተሰጠኝ ሃላፊነት በሊጋ እድሜዬ ጀምአውን በሰላት የመምራቱን ተግባር በብቃት እንዳልተወጣሁት ወይም ከእኔ እንደሚጠበቀው ደረጃ እንዳላደረግሁ ይሰማኝ ነበር፡፡

ስለሆነም የልጅነትና የጉርምስና ጊዜዬን አንፃራዊ በሆነ መልካም ስነ-ምግባር አሳለፍኩ፡፡ ይህንንም ስል የልጅነት ጨዋታዎችን ሳልጫወትና የማወቅና የመመሳሰል ጉጉት ሳያድርብኝ ማለቴ አይደለም፡፡ እኒያን ወቅቶች በሙሉ በመለኮታዊ እንክብካቤ በመከበቤ በዝምተኛነቴና ሰብሰብ ያልኩም ስለነበርኩ፣ እንዲሁም ከማንኛቸውም የመጥፎ ስነ-ምግባር መገለጫ ድርጊቶች የራቅሁና በትክክለኛው መንገድ ላይ የነበርኩኝ በመሆኔ ከወንድሞቼ መካከል ተለይቼ እታወቅ ነበር፡፡

በእኔ ላይ ትልቅ ግፊት ያሳደረችብኝን እናቴን (አላህ ነፍሷን ይባርከውና) እዚህ ላይ መጥቀሱን መርሳት የለብኝም፡፡ የቅዱስ ቁርዓንን አጫጭር ምዕራፎች (ሱራዎች)፣ ፀሎቶችንና የሃይማኖታዊ ንጽሕና ህግጋትን

አስተምራኝ፣ አይኖቼን ገለጠችልኝ፡፡ ለእኔ ትልቅ እንክብካቤ ታደርግልኝ የነበረችው የመጀመሪያ ልጇ በመሆኔ ይሆናል፡፡ ወይም ደግሞ ከአባቴ የመጀመሪያ ሚስትና ወንድ ልጆችዋ ጋር አብራ በአንድ ቤት ውስጥ በደባልነት ስለምትኖር እኔን በማስተማር ምናልባትም ደስታን እያገኘች ይሆናል፡፡

ከአልጀሪያ በመጣው በሼክ ሲዲ አህመድ አል-ቲጃኒ ልጅ ከተጎበኘበት ጊዜ ጀምሮ የቲጃኒ ሱፊ ጣሪቃን በተቀበለው በአል-ሰማዊ ቤተሰብ ውስጥ በእናቴ የወጣልኝ ቲጃኒ የተሰኘው ስም ልዩ ትርጉም አለው፡፡ የቤተሰቦቼ የትዉልድ መንደር የሆነችዉ የጋፍሳ ነዋሪ የሆኑ ብዙ ስዎች የቲጃኒ ሱፊ ጠሪቃ ተከታይ ሲሆኑ በተለይም ደግሞ የዚች ከተማ ነዋሪ የሆኑ ሀብታምና የተማሩ ሰዎች ይህንን ጣሪቃ ለማስፋፋት ትልቅ ሚና የተጫወቱ ናቸዉ፡፡

በስሜ ምክንያት በሰማዊ ቤተሰብ ውስጥም ሆነ ቤተሰብ ውጭ በተለይም ከቲጃኒ ጠሪቃ ጋር በተቆራኙት አካባቢ በጣም የታወቅሁ ሆንኩ፡፡ በመሆኑም ከላይ በጠቀስኩት በረመዳን ወር ምሽት ላይ የነበሩት አዛውንቶች እንኳን ደስ ያለህ ሊሉት ወደ አባቴ ሲመጡ እኔንም ግንባሬንና እጄን እየሳሙ እንዲህ ይሉ ነበር፡፡ «እኒህ የአለቃችን የሼክ አህመድ አል-ቲጃኒ በረካዎች ናቸው፡፡» እዚህ ላይ የቲጃኒ ሱፊ ጠሪቃ በሞሮኮ፣ አልጀሪያ፣ ቱኒዚያ፣ ሊቢያ፣ ሱዳንና ግብጽ ውስጥ በጣም የተስፋፋ መሆኑን መግለጽ ተገቢ ነው፡፡ የዚህ ጠሪቃ ተከታዮች ደግሞ ጠሪቃዉን በተመለከተ ወግ አጥባቂ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ የሌሎችን ጠሪቃ ባለቤቶች መቃብር እንኳን አይጎበኙም ነበር፡፡ ይህም የሆነዉ ሌሎች የጠሪቃ ባለቤቶች ዕዉቀታቸዉን ያገኙት ከርስ በርሳቸዉ ሲሆን አህመድ ኢል-ቲጃኒ ግን ምንም እንኳ ከ13

ምዕተ አመት በፊት ቢመጡም ዕዉቀታችዉን የቀሰሙት ቀጥታ ከአሏህ መልእክተኛ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነዉ ብለዉ ስለሚያምኑ ነዉ፡፡ ሼክ አህመድ አል-ቲጃኒ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ይነጋገሩ የነበሩት በህልም ሳይሆን በእዉን እንደሆነ ይታመን ነበር፡፡ በተጨማሪም እሳቸዉ ያዘጋጁት ሰለዋት (ነብዩን ማወደስ) ቁርአንን 40 ጊዜ ቀርቶ ከመጨረስ ይበልጣል ተብሎ ይታመን ነበር፡፡ ነገሩን ለማሳጠር ስለ ቲጃኒ ሱፊ ታሪክ መናገሬን እዚህ ላይ ገታ አድርጌ ኢንሻ አላህ በሌላ ገጽ ላይ እመለስበታለሁ፡፡

እኔም እንደ ሌላው ማንኛውም ወጣት በዚህ እምነት ውስጥ ነው ያደግሁት፡፡ እኛ ሁላችንም ምስጋና ለአላህ ይሁንና፣ የዳር አል- ሂጅራ ኢማም የነበሩትን የኢማም ማሊክ ኢብን አነስን አስተምህሮ የምንከተል ሱኒ ሙስሊሞች ነበርን፡፡ ሆኖም ግን እኛ ሰሜን አፍሪካ ያለነው በሱፊ ጠሪቃ ውስጥ ተከፋፍለናል፡፡ ለምሳሌ በጋስፋ ብቻ እንኳ አል-ቲጃኒያ፣ አል-ቃዲሪያ፣ አል-ራህማኒያ፣ አል-ሰላሚያና አል-ኢሳዉያ አሉ፡፡ ከላይ ለተጠቀሰው ጠሪቃዎች፣ በተለያዩ ስነ-ስርዓቶች ማለትም በጋብቻ፣ በግርዛት፣ በቃል-ኪዳን ወቅት ግጥሞችና ዚክሮችን የሚያነበንቡ ተከታዮችና ደጋፊዎች ነበሩ፡፡ ከአንዳንድ መጥፎ ጎኖች በስተቀር እኒህ የሱፊ ጠሪቃዎች ሀይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቶችንና የአዋቂዎቻቸውን ክብር በመጠበቅ አበይት ሚና ተጫውተዋል፡፡

## ወደ አላህ ቤት የተደረገው ታሪካዊ ጉዞ

በመካ ላይ በተካሄደው የመጀመሪያው የእስላምና የአረብ እስካውቶች ኮንፈረንስ ላይ ከስድስት ቱኒዚያዊ ተወካዮች መካከል አንዱ ሆኜ እንድሳተፍ

የቱኒዚያ ብሔራዊ እስካውቶች ማህበር ሲስማማ የ18 ዓመት ልጅ ነበርኩ:: ከልዑካኑ መካከል በትምህርት ዝቅተኛና በእድሜም ስነጻጸር አነስተኛው እኔ ስሆን፣ ሌሎቹ ሁለቱ የት/ቤት ርዕስ መምህራን፣ ከዋናው ከተማ የመጣ አንድ አስተማሪ፣ አንድ ጋዜጠኛና አምስተኛው ደግሞ በኋላ እንደተረዳሁት የዛን ወቅት የትምህርት ሚኒስቴር የነበሩት ግለሰብ ዘመድ የነበረና ሥራው ምን እንደነበረ ያላወቅሁት ሰው ይገኝበታል:: ጉዞአችን በቀጥታ አልነበረም፣ መጀመሪያ ያረፍነው አቴንስ ሲሆን እዚያም ሁለት ቀናት ቆየን፣ ቀጥሎ ደግሞ የጆርዳን ዋና ከተማ አማን ላይ አራት ቀናት ቆየን፣ ከዚያም ሳውዲአረቢያ ደርሰን በጉባኤው ከተሳተፍን በኋላ የኡምራ ስነ-ስርዓት ፈፀምን::

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አላህ ቤት ስገባ የተሰማኝን ስሜት ፍፁም ልገልፀው አልችልም፣ እንባዬ ያለማቋረጥ በጉንጮቼ ላይ ኮለል እያለ ሲወርድ፣ ልቤም በከፍተኛ ፍጥነት እየመታ እንዲያው ውልቅ ብሎ ወጥቶ ይህን ጥንታዊ ቤት ለራሱ ሊያየው የፈለገ መስሎ ተሰማኝ:: መላኢካዎች ተሸክመውኝ ከሀጅ አድራጊዎች በላይ አንስተው ወደ ቅዱሱ ካዕባ አናት ላይ አውጥተውኝ ከዚያ ላይ ሆኜ ለአላህ ጥሪ መልስ ስሰጥ ተሰማኝ:: «አላህ እነሆ የአንተ አገልጋይ ሳገለግልህ ከዚህ መጥቻለሁ ለበይክ አላሁመ ለበይክ»:: ብዙዎቹ ሐጃጆች ሲያወሩ እንደሰማኋቸው መካ ለመምጣት ዕድሜ ልካቸውን ገንዘብ ሲያጠራቅሙ እንደነበረና ለብዙ ጊዜም እንደጠበቁ ለመረዳት ቻልኩ::

ለእኔ ግን ጉዞው ያልተዘጋጀሁበትና ድንተገኛም ነበር:: አባቴ፣ የአውሮፕላን ቲኬቴን ካየ በኋላና ወደ መካ ሂጄ ሀጅ እንደማደርግ እርግጠኛ መሆኑን ሲያረጋግጥ እምባ እየተናነቀው ሲሸኘኝ ያለኝን አስተውሰዋለሁ:: «እንኳን

ደስ ያለህ ልጄ! አንተ የሲዲ አህመድ አል-ቲጃኒ ልጅ ስለሆንክ፣ ከእኔ ቀድመህ በዚህ ዕድሜህ መካ ሄደህ ሐጅ እንድታደርግ አላህ ፈቅዷል። እኔንም ኀጢአቴን ይቅር እንዲለኝ በአላህ ቤት ዱዓ አድርግልኝ፣ ቤቱ ድረስ ሄጄ ለሐጅ እንዲያበቃኝ ለምንልኝ።» (እኔም ሁሉም ሊጎበኘው የሚጓጓውን ገሚሱም የማይሳካለትን ወደዚህ ታላቅ ቦታ አላህ ራሱ ጠርቶኝ ተንከባክቦኝ እንዳመጣኝ ተሰማኝ።)

ይህንን ዕድል አደነቅሁት፣ በመሆኑም ሰው ሁሉ ከዘምዘም ውሃ ለመጠጣትና አል-ኑር ኮረብታ ላይ ወደ ሚገኘው የሂራ ዋሻ ለመድረስ ሲታገል እንኳን እኔ ፀሎቴን በማድረሱና በጠዋፍ (በከዕባ ዙሪያ በመሽከርከሩ ላይ) ተጠመድሁ። በዚህ ረገድ በአንድ ወጣት ሱዳናዊ ሀጅ አድራጊ ብቻ ተበለጥኩ፣ ከሁለት ሰው፣ ሁለተኛ ሆንኩ ማለት ነዉ። እዚያ እንደደረስኩ ልክ በታላቁ ነቢይ ጭኖች ላይ እንደተንከባለልኩና ትንፋሻቸውን እንዳሸተትኩ እየመሰለኝ ዝም ብዬ በወለሉ ላይ መንከባለሌን ተያያዝኩት። ምንኛ ውብ የሆኑ ትዝታዎች ናቸው! ፍፁም ከአይነ ህሊናዬ የማይጠፉ ማህተም ጥለውብኛል።

አላህ በብዙ መንገድ እኔን ተንከባክቦኛል፣ በጉባኤው ውስጥ ያገኘኋቸው ሁሉ ወደውኝ አብዛኛዎቹ ወደፊት ደብዳቤ ሊጽፉልኝ አድራሻዬን ወስደዋል። ቱኒዚያውያን ጓደኞቼ ግን ገና ከመጀመሪያው ለጉዞአችን ዝግጅት ለማድረግ በቱኒዚያ ዋና ከተማ ባደረግነው ስብሰባ ላይ በእኔ ላይ ንቀት አደረባቸው። ስሜታቸው ወዲያው ገባኝ። ነገር ግን ሰሜን የሚኖሩ ሰዎች ደቡብ የሚኖሩትን እንደኋላቀር ስለሚቆጥሩዋቸውና እንደሚንቋቸው ስለማውቅ ሁኔታውን በትዕግስት ያዝኩት። ብዙም ሳይቆይ አመለካከታቸው መለወጥ ጀመረ።

በጉዞውም ላይ ሆነ በጉባኤው ወቅት እንዲሁም በሀጁ ወቅት በግጥም ችሎታዬና ብዙ ሽልማቶች በማሸነፌ የእነሱን ከበሬታ ላገኝ በቃሁ:: ከተለያዩ ሀገር ዜጎች የተሰጡኝን ከሃያ በላይ የሚሆኑ አድራሻዎችን ይዤ ወደ ሀገሬ ተመለስኩ::
ሳውዲአረቢያ በቆየንባቸው 25 ቀናት ውስጥ ከብዙ ኡላማዎች ጋር ተገናኘን:: ትምህርታቸውንም ተከታተልን:: በአንዳንድ የዋሃቢ እስልምና እምነቶች ተመስጬ ሁሉም ሙስሊሞች ይህን ሃይማኖት እንዲከተሉ ተመኘ ሁ:: እነዚህን ሰዎች ከመላ አማኞቹ መካከል የአሏህን ቤት እንዲጠብቁ የመረጣቸው በዓለም ላይ ካሉት ሁሉ ንፁህና በጣም እውቀት ያላቸው ናቸው ብዬ አሰብኩ:: የዘይት ሀብትም ያሸከማቸው የርሁሩሁ አሏህ እንግዶች የሆኑትን ለሀጅ የሚመጡትን እንዲያገለግሉና እንዲንከባከቡ ነው ብዬም አሰብኩ::

ከሐጅ መልስ ወደ ሀገሬ ስገባ ለብሼ የነበረው የሳውዲን ብሄራዊ ልብስ ነበር:: አባቴም አዘጋጅቶልኝ በነበረው የአቀባበል ስነ-ስርዓት እጅግ ተደነቅሁኝ:: ከኢሳዊያ፣ ቲጃኒያ እና ከሱፊ ጠሪቃዎች በተውጣጡ ሼኪዎች የሚመራ ብዙ ህዝብ ከባቡር ጣቢያ ድረስ መጥተው ከበሮ እየደለቁ ተቀበሉኝ::

እየጨፈሩና እየዘፈኑ በመንደራችን መሀል መንገድ አጅበውኝ ሄዱ:: መስጊድ አጠገብ በደረስን ቁጥር ለአጭር ጊዜ እንድቆም ይደረግና ሌላው ሰው በተለይም አዛውንቶቹ ወደ እኔ ቀርበው እንኳን ደስ ያለህ ይሉኝና እንባ በተሞላባቸው ዓይኖቻቸው የአላህን ቤትና የነቢዩን መቃብር የመጎብኘት ጉጉታቸውን ይገልፁልኛል:: ሰው ሁሉ ከዚህ በፊት በጋፍሳ ውስጥ ሐጅ ያደረገ ሰው አይቶ እንደማያውቅ ነበር እኔን የሚመለከተኝ::

የህይወቴን አስደሳች ቀናት የኖርኩት በዚህን ወቅት ነበር፡፡ በጣም ብዙ ሰው፣ ከተማው ውስጥ አሉ የሚባሉትም ጭምር መጥተው ደስታቸውን ገልፀውልኝ፣ ብዙ ጊዜም አል-ፋቲሃን እንድቀራላቸዉ ይጠይቁኝ ነበር፡፡ ሊጠይቁኝ የመጡ ሰዎች ተሰናብተውኝ በሄዱ ቁጥር እናቴ እጣን ታጨስና ከመጥፎ መናፍስት ትንኮሳ እንድሰወር ትፀልይ ነበር፡፡

አባቴም የቲጃኒ ሱፊ ጠሪቃ ተከታዮችን በመጋበዝ ለተከታታይ ሦስት ምሽቶች በጎች በማረድ ትልቅ ፌሽታ አደረገ፡፡ ሰዎችም የተለያዩ ጥያቄዎች ይጠይቁኝ ነበር፡፡ የእኔም መልሶች ያተኮሩት ለእስልምና መስፋፋትና ድጋፍ ሳውዲዎች ያደረጉትን ጥረቶች በማወደሱ ላይ ነበር፡፡

ከዚያም ሰው ሁሉ *ሐጂ* እያለ ይጠራኝ ጀመር፡፡ አንዱ ጮክ ብሎ ሐጂ ብሎ ከተጣራ ያው እኔ መሆኑ የታወቀ ነበር፡፡ ቀስ በቀስም በተለያየ የሃይማኖት ቡድኖች አካባቢ በተለይም በሙስሊም ወንድማማቾች አካባቢ ታዋቂ ሆንኩ፡፡ በመስጊዶችም እየተዘዋወርኩ የሃይማኖት ጥያቄዎችን እያነሳሁ ማስተማር ጀመርኩ፡፡ በተለይም ሰዎች መቃብርን እንዳይስሙ እንጨቶችንም ለተበሩክ እንዳይነኩ ምክንያቱም ይህ በጣኦት ከማምለክ ስለማይለይ እንዲቀር ተናገርኩ፡፡ እንቅስቃሴዬም እየጨመረ ሄደ፡፡ ከኢማሙ ንግግር በፊት ዓርብ ዓርብ የሃይማኖት ትምህርት ማስተማር ጀመርኩ፡፡ ከአቢ ያዕቁብ መስጊድ ወደ ታላቁ መስጊድ ዞርኩ፡፡ ምክንያቱም የአርብ ሰላት በተለያየ ጊዜያት ስለሚካሄድ በአቢ ያዕቁብ እኩለ ቀን ላይ ሳደርግ በታላቁ መስጊድ ግን ከሰዓት በኋላ ነበር፡፡

የእሁድ ትምህርቴን የሚከታተሉት ደግሞ ቴክኖሎጂ ከማስተምርበት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚመጡ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያቱ

ያኔ ይርመሰመሱ በነበሩት የኮሚኒስትና የከሃዲዎች ፍልስፍና አስተማሪዎች ቅስቀሳ ተበርዞ የነበረውን አዕምሮአቸውን ለማጽዳት ብዙውን ጊዜዬን ሰውቼ ከፍተኛ ጥረት በማድረጌ እኒህ ተማሪዎቼ ይወዱኝም ያደንቁኝም ስለነበር ነው። ተማሪዎቼ እነዚህን የሃይማኖት ፕሮግራሞች በጉጉት ነበር የሚጠብቋቸው። ስጠየቅ የነበርኩትን ጥያቄዎችን በሚገባ ለመመለስና ራሴን ከጥያቄዎቹ ደረጃ አንጻር ለማጎልበት ይረዳኝ ዘንድ በርካታ መጽሀፍትን ገዝቼ በደንብ አነብ ነበር። በክበቡ ውስጥ ሊነሱ ለሚችሉ ጥያቄዎች ራሴን ለማዘጋጀት ስል በርካታ መጽሀፍትን ገዛሁ። አንዳንዶቹ ተማሪዎቼም ለእነዚህ መጽሐፍት ሲሉ ቤቴ ድረስ ይመጡ ነበር።

ከመካ ከተመለስኩ ልክ አንድ ዓመት በኋላ ሌላኛውን ግማሽ የሃይማኖት ግዴታዬን ተወጣሁ፣ ማለትም አገባሁ፣ ትዳር ያዝኩ። የአባቴ ልጆች ሲያገቡ ያየችውና ከማለፏም በፊት የኔን ጋብቻ ለማየት ትጓጓ የነበረችው የእናቴ ከፍተኛ ምኞት ነበር። አሳህም ምኞቷን አሳክቶላት ከዚህ በፊት ፍፁም አይቻት ከማላውቃት ወጣት ጋር ጋብቻ ፈፀምኩ። እናቴም የመጀመሪያና ሁለተኛ ልጆቼ ሲወለዱ ካየች በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች። አባቴ ግን ከእሷ ሁለት ዓመት ቀደም ብሎ ነበር የተለየን። አባቴም ከመሞቱ ቀደም ብሎ ለሀጅ ወደ መካ ተጉዟል። ከዚያም ከሁለት አመት በኂላ ከመሞቱ በፊት ተዉበት አድርጎ (ንሰሃ ገብቶ) ነዉ ያረፈዉ።

የሊቢያ አብዮት ድል የተቀዳጀዉ አረቦችና ሙስሊሞች በኢስራኤል ተሸንፈዉ ዉርደት ይሰማቸዉ በነበረ ጊዜ ነበር። አንድ ወጣት አብዮታዊ

መሪ ከህዝቡ ጋር ሆኖ ሲሰግድና ለእስልምና ቆሞ ሲሟገትና ስለ የአል ቁድስ ነጻነት ሲናገር አየን፡፡

እንደ አብዛኞቹ ወጣት ሙስሊሞችና አረቦች እኔም በጋዳፊ ሃሳቦች ተማረኩ፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ዲፓርትሜንት 40 ሰዎች ተውጣጥተን ወደ ሊቢያ ትምህርታዊ ጉዞ አደረግን፡፡ በአብዮቱ መጀመሪያ አካባቢ ሊቢያን ጎብኝተን ከተመለስን በኋላ በመላው ዓለም ውስጥ ሙስሊሞችና አረቦች የተሻለ ብሩህ መጪ ጊዜ እንደሚኖራቸው ተስፋ አደረብን፡፡

ባለፉት ቅርብ ዓመታት ዉስጥ በርከት ካሉ ጓደኞቼ ጋር ደብዳቤ ተለዋወጥኩ፡፡ ከአንዳንዶቹ ጋር የነበረኝ ጓደኝነት እየጠበቀ ስለመጣ እንድጎበኛቸው ጠየቁኝ፡፡ በዚህም ምክንያት በክረምቱ የሦስት ወር የእረፍት ጊዜ ለማካሄደው ጉዞ ዝግጅቴን አጠናቀቅሁ፡፡ ወደ ሊቢያና ግብጽ በመኪና ሄጀ ከዚያም ወደ ሊባኖስ፣ ሶሪያ፣ ጆርዳንና ሳውዲ አረቢያ በባህር ለመሻገር ወሰንኩ፡፡ ወደ ሰውዲ አረቢያ ለመሄድ የወሰንኩት ኡምራ ለማድረግና የሙስሊም ወንድማማቾች በሚያዘወትሩባቸው መስጊዶችና እንዲሁም በተማሪዎች መካከል በመገኘት ስለ ዋሃቢያ ያለኝን ጽናት ለማደስ ስለፈለግሁ ነበር፡፡

የዓርብ ሰላት ላይ ተሳትፈው ትምህርቴን በተከታተሉና ወደዚያው በሚመለሱ ሰዎች ሳይሆን አይቀርም ዝናዬ ከትውልድ መንደሬ አልፎ ወደ አጎራባች መንደሮች ተዛምቶ ነበር፡፡ የዝነኛው ባለ ቅኔ የአቡ አል-ቃሲም አል-ሻቢ ትውልድ ቦታ የነበረችው የአል-ጃሪድ ዋና ከተማ ቱዜር ውስጥ የሱፊ ጠሪቃ መሪ የሆኑት ሼክ እስማኤል አል-ሃዲፊ ዘንድም ዝናዬ ደረሰ፡፡

እኒህ ሼክ በቱኒዚያና በውጭም ጭምር በተለይም በፈረንሳይና ጀርመን የሠራተኛ መደቦች መካከል ብዙ ተከታዮች ነበሩአቸው።

ጋስፋ በሚገኙት ወኪሎቻቸው በኩል ግብዣ ደረሰኝ። እነሱም ለእስልምናና ለሙስሊሞች የሰጠሁትን ግልጋሎት አወድሰው ደብዳቤ ፃፉልኝ። በደብዳቤያቸውም ውስጥ የተማረ ሼክ አጠገቤ ባለመኖሩ እኔ የምሰራው ሥራ ትንሽ እንኳ ወደ አላህ እንደማያስጠጋኝ ገለፁልኝ። «ሼኩ አጠገቡ የሌለው፣ የሱ ሼክ ሸይጣን ይሆናል» እናም «መንገዱን እንዲያሳይህ ሼክ ያስፈልግሃል፣ አልያም ግማሹ እውቀት ከግቡ ያልደረሰ እውቀት ማለት ነው» ሼክ እስማኤል እራሳቸው ከግል የቅርብ ክበብ ተከታዮቻቸው መካከል አንዱ እንድሆን የመረጡኝ መሆኑን ገለጹልኝ።

ይህን ዜና ስሰማ በደስታ ፈነደቅሁ። ወደዚህ ከፍተኛና ምርጥ ቦታዎች ከፍ ላደረገኝ መለኮታዊ ክብካቤ የምስጋና እንባ አነባሁ። ምክንያቱም በተአምራቸው የታወቁትን የሱፊ ሼክ የሆኑትን የሲዲ አል-ሃዲ አል-ሃፊያን ዱካ በመከተሌና ከቅርብ ተከታዮቻቸው አንዱ በመሆኔ ነው። ከዚህም ቀደም በወቅቱ ዝናቸው ገኖ የነበረውን ሱፊ መሪዎችን እንደ ሲዲ ሲላህ ባልሳይንና ሲዲ አል-ጂላኒን የመሳሰሉትን አጅቤ ስለነበር ከኒህም ሼክ ጋር የምገናኝበትን ወቅት በጉጉት ጠበቅሁ። ወደ ሼክ ቤትም እንደገባሁ ቤቱ ሙሉ ነጭ ልቦሶችን የለበሱ ሼኮችን ጨምሮ በተከታዮቹ ተሞልቶ ነበር። የሠላምታ መለዋወጡ ስነ-ስርዓት እንዳበቃ ሼክ እስማኤል ብቅ ሲሉ ሁሉም ከመቀመጫው ብድግ ብሎ በታላቅ አክብሮት እጃቸውን ይስም ጀመር። የሳቸው ምክትል ሼክም እሳቸው መሆናቸውን በጥቅሻ ቢገልፁልኝም እኔ የጠበቅሁት አሁን ካየሁት የተለየ ሰው ስለነበር ምንም መደነቅ አላሳየሁም።

ወኪሎቻቸውና ተከታዮቻቸው እሳቸው ስለሚሰሩት ታምራቶች በነገሩኝ ላይ ተመስርቼ ለየት ያሉ ፍጥረት አድርጌ በአእምሮዬ ስያቸዉ ነበር። ግን አሁን ያየሁት ምንም ግርማ ሞገስ የሌለው ተራ ሰው ብቻ ነው። እናም ከእሳቸው ጋር ምክትላቸው ሲያስተዋውቀኝ ሞቅ አድርገው ተቀብለውኝ በቀኛቸው ከአስቀመጡኝ በኋላ ምግብ ሰጡኝ። ከእራት በኋላ እምነታዊ ስነ-ስርዓቱ ተጀምሮ ምክትላቸው ከሼኩ ቃለ መሐላ እንድቀበል አደረገና አስተዋወቀኝ። ከዚያም የተገኙት ሁሉ እንኳን ደስ ያለህ እያሉ መረቁኝ። ዘግየት ብዬም ሰዎች ከሚያወሩት እንደሰማሁት ስለእኔ እንደሚያውቁ ተረዳሁኝ። ይህም ሁኔታ ሼኩ ከጀማዓው ለሚሰነዝሩት ጥያቄዎች የሚሰጡት መልሶች ጋር አለመስማማቴን ለመግለጽ አደፋፈረኝ። እንዲህ ዓይነቱ ባህሪ ደግሞ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ቅሬታን አሳደረ። በተለይ አብዛኛውን ጊዜ ማንም ከማይከራከራቸው ሼክ ፊት እንዲህ ማድረጉ እንደብልግና ተቆጠረብኝ። ሼክም የሰፈነውን ውጥረት ተገንዝበው ሁኔታውን ለማቀዝቀዝ ብልጠታቸውን ተጠቅመው «አጀማመሩ የሚፋጅ ሰው መጨረሻው የሚያሸበርቅ ይሆናል» አሉ። ጀማዓውም ይህ አነጋገር መጨረሻው እንደሚያሸበርቅ ከሼኩ የተሰጠኝ ዋስትና ማረጋገጫና የፀጋ ምልክት አድርገው በመውሰድ ደስታቸውን ይገልፁልኝ ጀመር። ይሁን እንጂ ሼኩ ብልህና ብዙ ልምድ ያካበተ ስለነበረ በሚያበሳጨው ጣልቃገብነቴ እንዳልቀጥል ለማድረግ የሚቀጥለውን ታሪክ አጫወቱን።

ከእለታት አንድ ቀን አንድ የተማረ ሰው ሃይማኖታዊ የሆኑ ሰው ትምህርት ከሚሰጡበት ቦታ ለመከታተል መጣ። ሃይማኖታዊውም የተማረውን ሰው ተነስተህ ሄደህ ታጠብ አሉት፣ ሰውየውም ተነስቶ ወጥቶ ታጥቦ ትምህርቱን ለመከታተል ተመልሶ መጣ። ሃይማኖታዊው ሰውየም «ተነስተህ ሄደህ ታጠብ» ብለው በድጋሚ አዘዙት፤ የተማረው ሰውም ሄዶ

እንደገና ታጠበ፡፡ ወደ ትምህርት ክፍሉም እንደተመለሰ እንደገና ተነስቶ እንዲታጠብ ነገሩት፡፡ በዚህን ጊዜ የተማረው ሰው እያለቀሰ «አለቃ ከሰራሁትም ሥራ ሆነ ከዕውቀቴ በደንብ ታጥቤ ራሴን አጽድቻለሁ፣ አሁን በእርስዎ እጅ በኩል ከአላህ የተለገሰኝ ብቻ ነው የቀረኝ» በማለት ተናገረ፡፡

በዚህን ጊዜ ሃይማኖታዊው ሰው «አሁን መቀመጥ ትችላለህ» አሉት በታሪኩ ውስጥ ሼኩ የገለጹት ግለሰብ እኔ እንደሆንኩ ተረዳሁት፣ ሁሉም ሰው እንደ እኔው ተረድቶት ኖሮ ሼኩ ለእረፍት ወጣ እንዳሉ፣ የወቀሳ ናዳ አወረዱብኝ፡፡ በሥራዬ ውድቀት እንዳይደርስብኝ በትምህርት ጊዜ ዝም እንድልና ለሼኩ ተገቢውን አክብሮት እንዳሳይ ይህን የቁርዓን አንቀጽ በመጥቀስ ነገሩኝ «***ስማ አንተ አማኝ! ከነቢዩ ድምጽ በላይ ድምጽህን ከፍ አታድርግ፣ እርስ በርስህ እንደምታደርገው ሁሉ ከእርሳቸው ጋራ ድምጽን ከፍ አድርገህ አትናገር፣ አልያም ምኑንም ሳትጨብጥ ሥራህ ሁሉ መክኖ ይቀራልና***»፡፡ (ቅዱስ ቁርዓን 49:2)
እኔም ገደቤን ተረዳሁና ሰጥ ለጥ ብዬ ትዕዛዞችን ማክበር ጀመርኩ፡፡ ሼኩም ከአጠገባቸው አልለዩኝም፡፡ እኔም ከእሳቸው ጋር ለሦስት ቀናት ስቆይ ብዙ ጥያቄዎችን ጠየቅኋቸው፡፡ አንዳንድ የምጠይቃቸው ጥያቄዎችም ሆን ብዬ እውቀታቸውን ለመፈተን ነበር፡፡

ሼኩም ይህንኑ ተገንዝበው መልስ በሚሰጡኝ ጊዜ በቁርዓን ሁለት ዓይነት ትርጉሞች አሉ፣ አንዱ ገሃድ የወጣና ሌላው እስከሰባተኛው ደረጃ ድረስ ድብቅ የሆነ ነው ይሉኝ ነበር፡፡ የግል ካዝናቸውንም ከፍተው አቡ አል-ሀሳን አል-ሻድሂሊ በመሳሰሉ ሰዎች በኩል እሳቸውን ከኢማም አሊ ጋር የሚያገናኙ ሃይማኖታዊና የተማሩ ሰዎች ስም የያዙ የግል ማስረጃዎቻቸውን አሳዩኝ፡፡

እዚህ ላይ መጥቀስ የሚገባኝ ነገር እኚህ በሼኩ የሚካሄዱት ስብሰባዎች ሃይማኖታዊ መሆናቸውንና አብዛኛውን ጊዜም የሚጀመሩት ሼኩ የቁርዓን አንቀፆችን ከቀሩና ካዜሙ በኋላ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ጥቂት ግጥም አዘል ጥቅሶችን ካነበቡ በኋላ ጀመዓው ዜማዎችንና ዝክሮችን ያካሂዳል፡፡ ዜማዎቹም በአብዛኛው የሚያተኩረት በዚህ ዓለም ህይወት ከንቱነትና እራስን በሃይማኖታዊ ስነ-ስርዓት አንፆ ለወዲያኛው ዓለም መዘጋጀት ላይ ነው፡፡ ይህ ተግባር በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ከተገባደደ በኋላ፣ ከሼኩ በስተቀኝ በመጀመሪያ የተቀመጠው ሰው የሚችለውን ከቁርዓን ውስጥ አንብቦ «አላህ ይህንን በእውነት ነው የተናገረው» ሲል ሼኩ ቀበል አድርገው የአንድ ግጥም የመጀመሪያውን ስንኝ ሲያነቡ ጀመዓው ይቀበላቸዋል፤ ቀጥሎም እያንዳንዱ ሰው የቁርዓንን አንቀጽ ያነባል፡፡ ከዚህ በኋላ የዜማውን ስልት በመከተል ጀመዓው ቀስ እያለ አንዴ ወደ ቀኝ አንዴ ወደ ግራ ዘንበል ዘንበል ይላል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ሼኩ ብድግ ሲሉ፣ ሁሉም ብድግ ይሉና ሼኩን መሃል አስገብተው ክብ ይሠራሉ፡፡

ከዚያም አህ! አህ! አህ! እያለ ጀመዓው ሲጮህ፣ ሼክ በክቡ ውስጥ እየዞሩ ወደ እያንዳንዱ ሰው ይሄዳሉ፡፡ (ከዚያ በኋላ ዜማዉ ሞቅ እያለ ይሄድና ሰዎቹ እየዘለሉ በተቀናጀ መልኩ ነገር ግን በሚጨንቅ አይነት ቅላጼ ይጮሀሉ፡፡) ከጥቂት ውጣ ውረድ በኋላ ፀጥታው ቀስ በቀስ ሲሰፍን፣ ሼኩ የመጨረሻቸውን የግጥም ጥቅስ ካነበቡ በኋላ ሰው ሁሉ የእሳቸውን ግንባርና ትከሻ ስሞ ተመልሶ ይቀመጣል፡፡ የእነዚህን ሰዎች ሃይማኖታዊ ስርዓት ባላምንበትም አብሬያቸው ተካፍያለሁ፡፡ ከአላህ ጋር ለመገናኘት ምንም ዓይነት ሌላ ክፍል አያሻም ከሚለው እምነቴ ጋር ቢቃረንም ማለትም ማንኛውንም ነገር መጠየቅ ያለብን ከአላህ ብቻ እንጂ ከሌላ አይደለም፡፡ እንደኛው በቅዱሳንና በአዋቂ ሰዎች አማካኝነት ወደ አላህ

*መቅረብና በፍርሃት ላይ ተመስርቶ ዓለምን ትቶ ወደ መንፈሳዊነት መቀየሩን የሚያስተምረው የሱፊ አስተሳሰብ ወይም አይዲዮሎጂ ሲሆን ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ ወደ አላህ ለመቅረብ ምንም አማላጆች አያስፈልጉም፤ እንዲሁም የሚያደርጉትን ምንጊዜም አላህ አይምራቸውም* ብሎ *ያስተማረኝ* የወሀቢ እምነት *ነው*።

*ታላቁ* ነቢዩ *መሐመድ* (ሰ.ዐ.ወ) *መርዳት የማይችሉ ወይም ማማለድ የማይችሉ* ከሆነ ከእሳቸው በኋላ *የመጡት* ቅዱሳንና *ሃይማኖታዊ* ሰዎች *ታዲያ ዋጋቸው* ወይም ፋይዳቸው ምኑ ላይ *ነው*?

በጋስፉ ውስጥ ሼኩ የሳቸው ተጠሪ አድርገው አዲስ ሹመት ቢሰጡኝም እምነቱን *ሙሉ ለሙሉ* አልተቀበልኩትም። ለሱፊ *ጠሪቃ* አልፎ አልፎ *ድጋፌን* ባሳይና *ፈሪሀ* አላህ ላደረባቸው ሰዎችና ለቅዱሳኑም ስል አክብሮቴን *መቀጠል* አለብኝ የሚል ስሜት ቢያድርብኝም ክርክሬን በቁርዓን ጥቅሶች ላይ *መስርቼ* አበክሬ አከራከር ነበር። «***ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አትጥራ፣ አላህ እንጂ ሌላ አምላክ የለም***» (ቅዱስ ቁርዓን 28:88)። ሌላ ሰው ተነስቶም አላህ እንዲህ ብሏል

«***ስማ አንተ አማኝ ለአላህ ስለምታደርገው ድርጊት ተጠንቀቅ ወደ እሱ የምትቀርብበትንም መንገድ ፈልግ***» (ቅዱስ ቁርዓን 5:35) ቢለኝ እኔም *ፈጥኜ* የሳውዲ *ኡለማዎች እንዳስተማሩኝ እንዲህ መለስኩለት* «አላህን *መፈለግ* ጥሩ *ሥራን* በመ*ሥራት* ነው» *ያም ሆነ* ይህ ግን በዛን ወቅት *አዕምሮዬ ተምታትቶና* ተረብሾም ነበር። ይህ በእንዲህ እያለ አንዳንድ ተከታዮች አልፎ አልፎ ወደ እኔ ቤት እየመጡ አል-ኢምራህን (የዚክር ዓይነት ነው) አብረን እናከብር ነበር። ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ

ጎረቤቶቻችን በሚወጣዉ ድምጽ ተረብሸው ኖሮ በሚስቶቻቸዉ በኩል ለሚስቴ ቅሬታቸውን አስተላለፉ።

እኔም ይህን ያወቅሁ ጊዜ ተከታዮችን ዝክሩን በሌላ ሥፍራ እንዲደረግ ጠየቅኋቸው። እኔም ከዚያ በኋላ ለሦስት ወራት ወደ ውጭ እንደምሄድ ገልጬላቸው ጓደኞቼንና ቤተሰቦቼን ተሰናብቼ እሱን እንጂ ሌላ አምላክን ላላምን በሱም ላይ ተመክቼ አምላኬን ፍለጋ ተነሳሁ።

## በግብጽ አገር

የሊቢያ ዋና ከተማ ትሪፖሊ ውስጥ ከሚገኘው የግብጽ ኤምባሲ ወደ ኪናና ምድር ማለትም ወደ ግብጽ ልገባ የሚያስችለኝን የመግቢያ ቪዛ ለማግኘት ብዙ ቆየሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ በደንብ የረዱኝ ጓደኞች አገኘሁ። ላደረጉልኝም እርዳታ አላህ ምንዳቸውን ይክፈላቸው። ወደ ካይሮ ያደረግሁትም የመኪና ጉዞ በጣም ረጅም ነበር። ሊቢያ ውስጥ በሥራ ላይ የነበሩና ወደ አገራቸው የሚመለሱ አራት ግብፃዊያን ጋር በአንድ ታክሲ ሆነን ጉዞው ሦስት ቀናትና ሦስት ሌሊቶች ወሰደብን። በጉዞአችን ላይ እያለን ከእነሱ ጋር በመግባባት እየተጫወትኩ ቁርዓንንም አነብላቸው ነበር። እነሱም ወደውኝ ግብጽ ውስጥ እንግዳቸው እንድሆን ጠየቁኝ። እኔም ከእነሱ መካከል አህመድ የሚባለውን መረጥኩ። መንፈሳዊ ሰው ሆኖ ስላገኘሁትና ለእኔም ከፍተኛ መስተንግዶ ስላደረገልኝ እሱን ወደድኩት። ካይሮ ውስጥ ለሃያ ቀናት ተቀመጥኩ፤ በዚህ ጊዜ ከአባይ ወንዝ ትይዩ ሆኖ ከተሰራው ቤቱ ድረስ ሄጄ ፋሪድ አል-አትራሽ ከሚባለዉ ዘፋኝ ጋር ተገናኘሁ። በግብጽ ጋዜጦች ላይ ስለጨዋነቱ የተፃፈውን አንብቤ ወደድኩት። ግና ወደ ሊባኖስ ለመብረር በዝግጅት ላይ ስለነበር የተጨዋወትነው ለሃያ ደቂቃዎች ብቻ ነበር።

ድምጹን በጣም አድርጌ የምወደው ዝነኛውን የቁርዓን ቀሪ ሼክ አብዱልባሲጥ ሙሐመድ አብዱሰመድንም ጎበኘሁት፡፡ ከእሱም ጋር ለሦስት ቀናት ቆይቼ ከጓደኞቹና ከዘመዶቹ ጋር ብዙ ጉዳዮች ላይ ተወያይተን እነሱም በእኔ የማወቅ ጉጉት ግልጽነትና እውቀት የተነሳ ወደዱኝ፡፡ ስለ ስነ-ጥበብ ሲያነሱ ዘመርኩላቸዉ፡፡ ስለ ጥብቅ ሃይማኖታዊ ስነ-ስርዓትና ስለ ሱፊያም ሲያነሱ የቲጃኒና የሜዳኒ ጠሪቃ ተከታይ እንደነበርኩ እነግራቸዋለሁ፤ ስለ ምዕራቡ ዓለም ሲያነሱ በክረምቱ የእረፍት ጊዜያት ስለጎበኘሃቸው አገሮች ማለት ስለ ፓሪስ፣ ሎንደን፣ ቤልጅየም፣ ሆላንድ ጣሊያንና እስፔይን አጫውታቸዋለሁ፡፡ ስለ ሀጅ ሲያነሱ፣ ለሀጅ መካ እንደሄድኩኝ አሁንም ለኡምራ እንደምሄድ እነግራቸዋለሁ፡፡ ለሀጅ ወደ መካ ሰባት ጊዜ የሄዱ ሰዎች እንኳን የማያዉቃቸዉን ስለ የሂራ ዋሻ፣ የሰዉር ዋሻና የኢስማኢል መሰዊያ ስፍራዎች አጫወትኳቸዉ፡፡

ስለ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲያነሱ ሁሉንም ቁጥሮችንና ሳይንሳዊ መጠሪያዎችን እሰጣቸዋለሁ፤ ስለፖለቲካ ሲያነሱ አስተያየቴን እንዲህ በማለት ገለጽኩላቸዉ «እራሱን ከፈገግታው ዓለም ያስወጣውን የአል-ናስር ሰላሀዲን አል-አዩቢን ነፍስ አላህ ይማረው፣ በጣም ቅርብ የሆኑ ጓደኞቹ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንኳ ብዙ ጊዜ ፈገግ ሲሉ ይታዩ ነበር እያሉ ሲተቹት፤ የአል-አቅሳ መስጊድ በአላህ ጠላቶች እጅ ወድቆ እያለ እንዴት ፈገግ እንድል ትፈልጋላችሁ? በአላህ ስም እምልላችኋላሁ ወይ ነፃ ሳላወጣው ወይ ሳልሞትለት ፍፁም ፈገግ አልልም»

በአል አዝሃር ውስጥ ያሉ አንዳንድ ሼኮችም በእንደዚህ ያሉት ስብሰባዎች ተገኝተው ከቁርዓን ጥቅሶች የምቀራቸውን ከታላቁ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አባባሎችም የምጠቅሳቸውን ወደውልኝ ነበር፡፡ በማቀርባቸውም ጠንካራ

የክርክር ነጥቦች በመደነቅ ከየትኛው ዩኒቨርስቲ እንደተመረቅሁ ይጠይቁኛል፡፡ እኔም በኩራት ከአል-አዝሃር በፊት ከተቋቋመው ከአል-ዘይቱና ዩኒቨርስቲ እንደተመረጥኩ ብሎም አል-አዝሃርን ያቋቋሙት ፋጢሚያዎች የጀመሩትም ቱኒስ ውስጥ ከሚገኘው አል-መህዲያ እንደነበርም ዘርዝሬ አስረዳቸዋለሁ፡፡ በአል-አዝሃር በርከት ካሉ ምሁራን ጋር ተገናኘሁ፣ አንዳንዶቹም ጥቂት መጽሐፍት አበረከቱልኝ፡፡

አንድ ቀንም የአል-አዝሃር ዩኒቨርስቲ ጉዳይ ሃላፊ ከሆነ ባለሥልጣን ቢሮ ውስጥ ሳለሁ ካይሮ በሚገኘው በጣም ታላቁ የባቡር ጣቢያ ኩባንያ ውስጥ ሙስሊሞችና ኮፕቲኮች በሚሳተፉበት ህዝባዊ ስብሰባ ውስጥ ለመካፈል አንድ የግብጽ አብዮታዊ ደርግ አባል መጣ፡፡ ይህ ህዝባዊ ስብሰባም የተጠራው ከሰኔው ጦርነት በኋላ የተካሄዱትን የአሻጥር እንቅስቃሴዎችን ለማውገዝ ነበር፡፡ ይህም የደርግ አባል ወደ ህዝባዊ ስብሰባ አብሬው እንድሄድ ስለጎተጎተኝ ግብዣውን ተቀብዬ በመሄድ ለክብር እንግዶች በተዘጋጀው ሥፍራ ከአባ ሽኑዳህና ከአል-አዝሀሩ ሼክ መካከል ገብ አልኩ፡፡ በህዝባዊ ስብሰባ የባህል ኮሚቴዎችና መስጊዶች ንግግር የማድረግ ልምድ ስለነበረኝ በቀላሉ አደረኩ፡፡

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከጠቀስኳቸው ነገሮች ዋነኛው ነጥብ እንዲያው እራሴ ትልቅ እንደሆንኩና ከፍተኛ በራስ የመተማመን ሁኔታም ተሰማኝ፡፡ እውነተኛው ምሁርም እንደሆንኩ አድርጌ እራሴን ቆጠርኩት፡፡ በርካታ ከአል-አዝሀር ኡለማዎች ለእኔ ከመሰከሩልኝ አንዳንዶቹም አልፈው ተርፈው የአንተ ቦታ እዚሁ ከአል-አዝሀር ነው ሲሉኝ ለምን ታዲያ እንደዚያ ዓይነት ስሜት አይሰማኝ፡፡ እኔም በእጅጉ እንድኮራ ያደረገኝ ነገር ቢኖር የታላቁን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) አንዳንድ ቅርሶች እንዳይ ስለተፈቀደልኝ ነው፡፡ ካይሮ

የሚገኘው የሲዲ አል-ሃሳያን መስጊድ ሃላፊ ራሱ ብቻ ወደ ሚከፍተዉ ክፍል ወሰደኝ፡፡ ከፍተን ከገባን በኋላ በሩን መልሶ ቆልፎ አንድ መሳቢያ ከፍቶ የታላቁን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሽሚዝ አውጥቶ አሳየኝ፡፡ እኔም ሽሚዙን ተቀብዬ ሳምኩት፡፡ ከዚያም ሌሎች ቅርሶቻቸውን አሳየኝ፡፡ ከክፍሉም እንደወጣሁ በዚህ ሰውዬ በጎ ሥራ ተነክቼ ምንም ክፍያ ስላልጠየቀኝ እንዲያውም ገንዘብ ብሰጠው ፍፁም አሻፈረኝ በማለቱ ስቅስቅ ብዬ አለቀስኩ፡፡ በመጨረሻ ከእኔ ብዙ ጉትጎታ በኋላ ትንሽ ገንዘብ ወስዶ የታላቁን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ክብር ካገኙት አንዱ በመሆኔ እንኳን ደስ ያለህ አለኝ፡፡

ምናልባትም ያ ጉብኝት ልባዊ የሆነ ሀሴት ጥሎብኝ ሳያልፍ አልቀረም፡፡ ወሃቢያዎች ነቢያትን በተመለከተ የሚሉት ነገር፣ እንዴት እንደ ሞቱና እንደ ማንኛዉም ሟች ሰዉ እንዳለፉ ቀለል አድርገዉ የሚናገሩትን ነገር ለጥቂት ሌሊቶች ማሰላሰል ተያያዝኩ፡፡

ያን ሀሳብ ፍፁም አልወደድኩትም፣ እንዲያውም ሀሰትነቱን እየታየኝ መጣ፡፡ ለአላህ ሲል ሲዋጋ የተሰዋ ሰማዕት አይሞትም፣ በአምላኩ ህያው ነው፡፡ እናም የመጀመሪያውና የመጨረሻው አለቃም(ነቢዩ) እንዲሁ ነው፡፡ ለሼኩቻቸውና ለቅዱሳኖቻቸው ለችግሮቻቸው መፍትሔ እንዲያስገኙላቸው ሙሉ ስልጣን ከሚሰጡበት የሱፊ ትምህርቶች ጋር ቀደም ብዬ ራሴን አስተዋውቄ ስለነበር የውስጥ ስሜቶቼ ግልጽና ጠንካራ እየሆኑ መጡ፡፡ በእውነት ስለሚያምኑትና እሱ የሰጣቸውንም ፈቅደው በመቀበላቸው ምክንያት አላህ ብቻ ይህንን ሥልጣን ሊሰጣቸው እንደሚችል ያምናሉ፡፡ እሱስ በቅዱስ አባባሉ፣ እንዲህ አላለምን? «ባሪያዬ ሆይ! ታዘዘኝ ከዚያም እንደእኔ ትሆናለህ፣ ይሁን ብለህ ካዘዝክ ይሆናል»

በውስጤ የሚካሄደው ትግል በእኔ ላይ ተጽዕኖ ማሳየት ጀመረ:: በዚህን ወቅት የግብጽ ቆይታዬ እየተገባደደ መጣ:: ሆኖም ግን በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት በርከት ያሉ መስጊዶችን እየተዘዋወርኩ መጎብኘት በሁሉም ውስጥ ሰላቴን ሰገድኩ:: የማሊክ፣ አቡሃኒፋ፣ አል-ሻፊዒ፣ አህመድ ኢብን ሃንበል፣ አል-ሰይዳህ ዘይነብ እና የሰይዱና አል-ሁሴይን መስጊዶችን ጎበኘ ሁ:: የአል-ቲጃኒ ሱፊ ጠሪቃ ዛዊያም ጎበኘሁ:: አንዳንዶቹ ረዘም ያሉ ቢሆኑም እኔም አጠር ላድርገው ብዬ ነው እንጂ ስለጉብኝቶቹ በርከት ያሉ ታሪኮች ነበሩኝ::

## የመርከቡ ላይ ትውውቅ

ልክ የግብጽ መርከብ ወደ ቤይሩት በሚንቀሳቀስበት እለት እኔ ወደ አሌክሳንደሪያ ጉዞዬን ጀመርኩ:: አእምሮዬም ጉልበቴም ደክሞ ስለነበር ልክ መርከቡ ላይ እንደወጣሁ አልጋ ውስጥ ገብቼ ጅው ብዬ ለሁለት ወይም ለሦስት ሰዓታት ያህል ተኛሁ:: አንድ የሆነ ድምጽ «ወንድማችን የደከመው ይመስላል» ሲል ስሰማ ብንን አልኩ:: እኔም «ከካይሮ እስከ አሌክሳንደሪያ ያደረግሁት ጉዞ በጣም አድክሞኛል:: መርከቡ እንዳያመልጠን በሰዓቱ ለመድረስ ሳስብ ትላንት ማታ ብዙ አልተኛሁም» አልኩት:: ሰውየው ካነጋገሩ ግብፃዊ እንዳልሆነ ገባኝና እንደ ልማዴ ስለሰውየው የማወቅ ጉጉት አደረብኝና ልተዋወቀው ተጣደፍኩ:: እሱም ስሙ ሙኒም ሲባል ከባግዳድ ዩኒቨርሲቲ የመጣ ኢራቃዊ ነው:: በአል-አዝሃር ዩኒቨርስቲ ለዶክትሬቱ የሠራው ሥራ ሊያቀርብ ወደ ካይሮ የመጣ ምሁር ነው::

ስለ ግብጽና ግብፃዊያን ተጨዋውተን ከሽንፈቱ ጀርባ በነበሩት ምክንያቶች ላይ ተወያይተን ከስምምነት ደረስን:: የኛ ውርደት እንዲቀጥልና

መሬታችንም ተይዞ እንዲቀር ሆን ተብሎ በቅኝ ገዥዎች ተጋኖ የሚነገረውን የአረቦች ተራ ወሬ እንደምቃወም አክዬ ተናገርኩ። እኛ ሌላው ቀርቶ በሃነፊና በማሊኪ መካከል እንኳ ልዩነት እንደምናደርግ ገልጬ፣ በካይሮ አቡ ሃኒፋ መስጊድ ስለደረሰብኝ አንድ አሳዛኝ አጋጣሚ አጫወትኩት። እዚያ በነበርኩበት ጊዜ የአስርን ሰላት ከሰው ጋር አካሂጄ ስጨርስ አጠገቤ ቆሞ የነበረው ሰውዬ በንዴት «በሰላትህ ወቅት እጆችህን ደረትህ ላይ ለምን አላደረግካቸውም? ከዚያም ማሊኪዎች እጃቸውን ለቀው መስገድ እንደሚመርጡና እኔም ማሊኪ እንደሆንኩ በትህትና ነገርኩት። ከዚያም የሱ ምላሽ ግን «ታዲያ ሂድና እዛ ማሊኪ መስጂድ ስገዳ!» የሚል ነበር። እኔም መሮኝና አንገሽግሾኝ ስለነበር ከመስጊዱ ወጣሁ፣ ነገሩ ሁሉ በጣም እየተምታታብኝ መጣ።

የኢራቁ መምህርም ፈገግ ብሎ እሱ ሺዓ እንደሆነ ገለጸልኝ። በነገረኝም ነገር ትንሽ ረበሽ ብዬ ሳስብ እንዲህ አልኩት «ሺዓ መሆንክን ባውቅ ኖሮ በጭራሽ አላናግርህም ነበር» እሱም «ለምን?» ብሎ ጠየቀኝ። «ምክንያቱም እናንተ ሙስሊም አይደላችሁም እናንተ የምታመልኩት አሊ አብን አቢ ጧሊብን ነው። ከእናንተ መካከል የሚገኙት መካከለኞቹ አላህን ቢያመልኩም በነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ግን አያምኑም። «የተሰጠውን ሃላፊነት ክዷል፣ ከዚያም መልዕክቱን ለአሊ መስጠቱን ትቶ ለሙሃመድ አሳልፎ ሰጥቷል ብላችሁ መልአኩ ጅብሪልን አውግዛችሁታል» በማለት መለስኩለት።

እንዲህ ዓይነት ነገሮችን እየጠቃቀስኩ ንግግሬን ስቀጥል፣ ጓደኛዬ አንዳንዴ ፈገግ እያለ አልፎ አልፎም መገረምን እያሳየ በጥንቃቄ አዳመጠኝ። ንግግሬንም ሳበቃ «ተማሪዎችን የምታስተምር መምህር ነህ?» ብሎ

ሲጠይቀኝ «አዎን» ብዬ መለስኩለት፡፡ «መምህራኖች እንዲህ ከሆነ የሚያስቡት ምንም ትምህርት የሌላቸውን ሰዎች መውቀስ አንችልም» አለኝ እኔም ቀጠል አድርጌ «ምን ማለትህ ነው?» አልኩት «ይቅርታ አድርግልኝና እኒህን የተሳሳቱ ነገሮችን ሁሉ ከየት አገኘሃቸው?» ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ነገሮቹን ያገኘኋቸው ከታወቁ የታሪክ መፃህፍት ሲሆን ሌላውን ደግሞ ከሰዎች ነው አልኩት፡፡ «ደህና! ሰዎቹን እንተዋቸዉና እስቲ ምን ምን መጽሀፍት እንዳነበብክ ንገረኝ» አለኝ፡፡ እኔም በአህመድ አሚን የተጻፉትን «ፈጅር አል ኢስላም»፣ «ዱሀ አል-ኢስላም» እና «ዙህር አል-ኢስላም» የመሳሰሉትንና ሌሎች ብዙ መጽሀፍት ጠቃቀስኩለት፡፡ «ከመቼ ጀምሮ ነው አህመድ አሚን በሺዓ እንደማስረጃና ዋቢ የመሆን ስልጣን የተሰጠዉ?» ብሎ ጠየቀ፤ ቀጠል በማድረግም «ሚዛናዊና ትክክለኛ ለመሆን ኦርጂናል የሆኑ ትክክለኛ ምንጮች ማየት ግድ ይላል» አለኝ፡፡ «ለመናገር አንድ ሰው የአንድን ነገር የመጀመሪያ ምንጮች አግኝቶ ማየት ይኖርበታል» አለኝ፡፡ «በሁሉም ዘንድ በደንብ የሚታወቀውን ነገር ለምንድን ነዉ የምመረምረው?» በማለት ጠየቅኩት ራሱ አህመድ አሚን ኢራቅን ጎብኝቶ ነበር፡፡ ነጀፍ ውስጥ ካገኛቸው መምህራን አንዱ እኔ ነበርኩ፡፡ በሺዓ ላይ ስለጻፈው ጽሁፍ ትችት ባቀረብንለትም ጊዜ ስለሺዓ ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለና እንዲያውም ከሺዓዎቹ ጋር ሲገናኝ እኛ የመጀመሪያዎቹ እንደሆን ነግሮን ይቅርታ ጠየቀን፡፡ ስለእኛ አንዳችም ነገር ሳያዉቅ ስለኛ ሁሉንም መጥፎ ነገሮች የጻፈ በመሆኑ ከጥፋቱ በላይ ይቅርታዉ አስከፊ እንደሆነ ነገርነዉ፡፡

«ወንድም! ቁርዓን የኛ ፍፁም የሆነ ማረጋገጫችን ቢሆንም በእሱ ላይ ተመርኩዘን የሁዳ (አይሁድ) ክርስቲያኖችን እንዲህ ናችሁ ብንላቸው አይቀበሉንም፡፡ ስለሆነም ስህተቶቻቸውን በራሳቸው መፃህፍት ውስጥ

ማሳየት አለብን፡፡ ያኔ ማረጋገጫዉ ጥንካሬ ይኖረዋል፡፡ «ከቤተሰቧ የሆነ አንዱ መስካሪ መሰከረ» ከሚለዉ ምዕራፍ መሆኑ ነዉ፡፡» ንግግሩም በተጠማ ሰው ልብ ላይ እንደሚፈስ ውሃ በእኔ ልብ ላይም ኮለል ሲል ተሰማኝ፡፡ እኔም አባባሉ መሠረት ያለው አስተሳሰብና ጠንካራ ማረጋገጫ እንዳለው ስለተሰማኝ በጥላቻ ከጭፍን ሃያሲ ወደ አንድ ለማዳመጥና በደንብ ለማሰብ ወደፈለገ ሰውነት ለወጠኝ፡፡ ስለሆነም ጨዋነትን እያሳየሁ መምህሩን ማዳመጥ ነበረብኝ፡

«እኔም አንተ በነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ከሚያምኑት ሰዎች አንዱ ነህ ማለት ነው?» ስል ጠየቅኩት፡፡ «ሁሉም ሺአዎች እንደ እኔው በመልዕክቱ ያምናሉ፣ ወንድም! ትንሽ ጥርጣሬ እንዳያድርብህ ነገሩን ራስህ መርምረህ ብትደርስበት ይሻላል» ሲል መለሰልኝ፡፡ በማከልም «በእውነት ሀቁን ለመረዳት ከፈለግህ እራስህንም ለማሳመን እንዲያስችልህ ሁኔታውን በራስህ ዓይኖች ለማየት ኢራቅን እንድትጎበኝ ጋብዣለሁ፡፡ እዛም ከሺአ ኡለማዎችና ከተራው ህዝብ ጋር ተገናኝተህ እኒህን ሆን ተብሎ የተነዙትን ውሸቶች አብጠርጥረህ ታያቸዋለህ» አለኝ፡፡

«አንድ ቀን ኢራቅን ጎብኝቼ ስመጥር የሆኑትን እስላማዊ ቅርሶችን በተለይም የአባሲያንና የሀሩን አል-ረሺድን ቅርሶች ማየት ምኞቴ ነበር፡፡ ግና በመጀመሪያ ያለኝ የተወሰነ ገንዘብ ለኡምራ አድርሶ የሚመልሰኝ ብቻ በመሆኑ ሁለተኛም ደግሞ አሁን ያለኝ ፓስፖርት ኢራቅ ስለማያስገባኝ አሁን ጉብኝቱን ማድረግ አልችልም» አልኩት፡፡

«በመጀመሪያ ደረጃ ኢራቅን እንድትጎበኝ ስጋብዝህ ከቤይሩት ባግዳድ ደርሶ መልስ የሚያስፈልገውን የጉዞ ወጭ እራሴ እሸፍናለሁ ማለት ነው፡፡ ኢራቅ

ውስጥ እስካለህ ድረስ የእኔ እንግዳ ስለሆንክ ከእኔ ጋር ትኖራለህ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ኢራቅ ሊያስገባህ ስለማይችለው ፓስፖርት በተመለከተ፣ ታላቅ ለሆነው ለሱ ምስጋና ይድረሰውና እሱን ለአላህ አንተወው፡፡ አላህ እንድትጎበኝ ፈቅዶ ከሆነ ካለ ፓስፖርትም ልትጎበኝ ትችላለህ፡፡ ሆኖም ግን ቤይሩት እንደደረስን የመግቢያ ቪዛ እንድታገኝ ጥረት እናደርጋለን» አለኝ፡፡ ስለተደረገልኝ ግብዣ በጣም ተደስትኩ፡፡ ከምንም በላይ የሆነው አላህ ከፈቀደም መልሴን በሚቀጥለው ቀን እንደምሰጠው ለጓደኛዬ ቃል ገባሁለት፡ ፡ ከመኝታ ክፍሌ ተነስቼ ወደ መርከቡ ላይኛው ክፍል ወጣሁና አድማሱን በሞላው ባህር አእምሮዬ ጭልጥ ብሎ ሄዶ ንጹህ አየር እየተነፈስኩ በደንብ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ሰማይና ምድሩን የፈጠረውን እኔንም እዚህ ቦታ ያመጣኝን ፈጣሪዬን አመሰገንኩት፡፡ ከምንም በላይ የሆነው ጌታ ምስጋና ይድረሰውና ከክፉ ነገሮችና እኩይ ተግባራት እንዲሰውረኝ ከስህተቶችም እንዲጠብቀኝ ለመንኩት፡፡

በአለፉት ጊዜያት ያጋጠሙኝን ሁኔታዎች ማስታወስ ስጀምር አእምሮዬ ጭልጥ ብሎ ሄደ፡፡ የልጅነት ደስታዎቼን አስታውሼ ለወደፊቱ የተሻለ ሁኔታ አለምኩ፤ አላህና መልዕክተኛው የተለየ እንክብካቤ እንደሚያደርጉልኝ ተሰማኝ፡፡ ዳርቻዎችዋ አልፎ አልፎ በአድማሱ ላይ ብቅ የሚለውን የግብጽ ምድር እየተመለከትኩ በግብጽ ውስጥ አቻ የለሽ ትዝታዬ የሆነውን የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ሽሚዝ እንዴት እንደሳምኩት ትውስ አለኝ፡፡ እነዚህ የማይረሱ ዉድ የግብጽ ተዝታዎቼ ናቸዉ፡፡

በልቤ ውስጥ ከፍተኛ ደስታን ያስገኘልኝን የሺአውን ንግግር አስታወስኩ፡፡ ምክንያቱም የእስላማዊ ስልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረበት ጊዜ

በበርካታ ምዕራባዊያን ይደነቅ የነበረውን ዳር አል-ሂክማን የመሠረቱት የአል-ረሺድና የአል-መእሙን ሥርወ-መንግስትን የሚያስታውሰኝን የኢራቅን ሀገር የመጎብኘቱን ህልሜን ዕውን ያደርግልኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከማንም የላቀ አእምሮ የነበራቸውን ዝናቸውም በሁሉም ሀገር የተሰራጨውን የሼክ አብዱልቃድር አል-ጅላኒን ሀገር በመሆኗም ነበር፡፡ ይህንንም ህልሜን እውን ለማድረግ ስል ከአላህ የተደረገልኝ መለኮታዊ ክብካቤ እንደሆነ ገመትኩ፡፡ እንዲህ እያሰብኩ ጭልጥ ብዬ ሄጄ ተሳፋሪዎች ወደ እራት አዳራሽ እንዲመጡ በድምጽ ማጉያ ሲነገር ነቃሁ፡፡ እኔም ወደዚያው ሳመራ ሰው ተጨናንቆ ወደ አዳራሹ ለመግባት ሲጯጯህና ሲጋፋ ደረስኩ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ሺአው ከጀርባዬ መጥቶ ሽሚዜን ይዞ ጎተት አደረገኝና «ወንድሜ ራስህን አታስጨንቅ ወዲህ ና! ሰው ቀለል ሲል እንበላለን፡፡ እንዲያውም አንተን እየፈለግሁ ነበር» አለኝና «ሰላት ሰግደሀል?» ብሎ ጠየቀኝ «አይ እስካሁን አልሰገድኩም» ስለው አብረን እንድንሰግድ ጠየቀኝና «ግርግሩና ግፊያው ካበቃ በኋላ ተመልሰን መጥተን እንበላለን» አለኝ፡፡

በሃሳቡ ተስማማሁና ወደ አንድ ጭር ወዳለ ቦታ አብረን ሄደን ከተታጠብን በኋላ ቆየት ብዬ ለመስገድ አስቤ እሱ እንዴት እንደሚሰግድ ለማየትና ልፈትነውም ስል ሰላቱን እሱ እንዲመራ ጠየቅኩት፡፡ ልክ ፀሐይ ስትጠልቅ ለሚደረገው ሰላት ጥሪ አድርጎ ቁርአን ጥቅሶችን መቅራት ሲጀምር ሀሳቤን ቀየርኩ፡፡ በብዛት ስላነበብኳቸው ሃይማኖታዊና አላህን ፈሪ በሆኑት ከነቢዩ ጓደኞች በአንዱ የሚመራ መስሎ ተሰማኝ፡፡ ሰላቱን ካገባደደ በኋላ አገሬ ውስጥም ሆነ ሌሎች አገሮች ውስጥ ሰምቼ የማላዉቃቸዉን ዱኣዎች

አነበነበ፡፡ ነቢዩ መሀመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲሁም ቤተሰቦቻቸውን ሲያመሰግንና ተገቢውን ቦታ ሲሰጣቸው በሰማሁ ጊዜ ትልቅ እፎይታ ተሰማኝ፡፡

ከሰላት በኋላ አይኑ እንባ ማዘሉን ተመለከትኩ አላህ የእኔን አይኖች እንዲከፍትና ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ እንዲመራኝ ሲለምንም ሰማሁት፡፡ አሁንም ጭር ወዳለው የምግብ አዳራሽ ከገባን በኋላ እኔን መጀመሪያ እንድቀመጥ አድርጎ ከዚያም እሱ ተቀመጠና የምንበላው ሲቀርብልን እንደ አጋጣሚ የሱ ምግብ ውስጥ ብዙ ስጋ ስለነበረ ያንን ለኔ ሰጥቶ እሱ የኔን ወሰደ፡፡

ልክ እንደራሱ እንግዳ አድርጎ ወስዶኝ ስለምግብ ስለመጠጥና ስለአመጋገብ ስርዓት ከዚህ በፊት ሰምቻቸው የማላውቀው ታሪኮችን አጫወተኝ፡፡ የሰውየውን ስነ-ምግባር ወደድኩት፡፡ የምሽቱን ሰላት እሱ ራሱ ከመራ በኋላ እስካነባ ድረስ ረጅም ዱኣዕ አነበነበ፡፡ እኔም አላህ ምስጋና ይግባውና ሰውየው ላይ ያደረብኝን ጥርጣሬ እንዲያስወግድልኝ ለመንኩት ምክንያቱም «ትንሽ ጥርጣሬ ሃጢአት ሊሆን ይችላል» ግን ማን ያውቃል?

ያንን ሌሊት ስለኢራቅና ስለ አንድ ሺህ ከአንድ ሌሊት ታሪኮች ሳልም አደርኩ፡፡ የነቃሁትም ጓደኛዬ ለሱብሂ ሰላት ጥሪ ሲያደርግ ነው፡፡ አብረን ከሰገድን በኋላ ቁጭ ብለን አላህ ለሙስሊሞች ስላደረገው ፀጋዎች ተወያየን፡፡ ከዚያም ተመልሰን ከተኛን በኋላ ከእንቅልፌ ስነሳ እሱ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ መቁጠሪያውን ይዞ የአላህን ስም እየጠራ ነበር፡፡ ከእሱ ጋርም መሆኔ እያስደሰተኝ መጣና አምላኬንም ይቀር እንዲለኝ ለመንኩት፡፡

በምግብ አዳራሹ ምሳችንን እየበላን ሳለን መርከቡ ወደ ሊባኖስ ጠረፍ እየተቃረበ መሆኑን በድምጽ ማጉያው ተለፈፈ፡፡ እናም በአላህ እርዳታ በሁለት ሰዓታት ውስጥ ቤይሩት ወደብ እንደርሳለን፡፡ ጓደኛዬም ስለተነጋገርነው ነገር ምን እንደወሰንኩ ጠየቀኝ፡፡ አላህ ከፈቀደውና መግቢያ ቪዛ ካገኘሁ ኢራቅ የማልሄድበት ምክንያት እንደማይታየኝ ገለጽኩለትና ስለግብዣውም አመሰገንኩት፡፡

ቤይሩት ደርሰን እዛ አንድ ቀን ካደርን በኋላ ወደ ደማስቅ አመራን፡፡ እዛ ደማስቆ እንደደረስን ቀጥታ ወደ ኢራቅ ኢምባሲ ሄደን እንዲያው በማይታመን ፍጥነት ቪዛ አገኘን፡፡ ከኤምባሲው እንደወጣንም እንኳን ደስ ያለህ አለኝ፡፡ ሰላደረገልን ዕርዳታ አላህን አመሰገንነው፡፡

## በኢራቅ ያደረግሁት የመጀመሪያ ጉብኝት

ከደማስቆ ተነስተን የአል-ነጀፍ ኢንተርናሽናል ኩባንያ ንብረት በሆነ አንድ ባቡር ተሳፍረን ወደ ባግዳድ አመራን፡፡ የአየሩ ሙቀት 40 ዲግሪ ከነበረው ባግዳድ ስንደርስ አል-ኡማል ውስጥ ወደሚገኘው ጃሚላህ ተብሎ ወደሚጠራው የመኖሪያ ቤት ገባን፡፡ እረፍት ካደረግን በኋላ ዲሽዳሻ የሚባል ረጅም ሸሚዝ አምጥቶ ሰጠኝ ምግብና ፍራፍሬም ቀረበልኝ፡፡ ከዚያም የቤተሰቡ አባላት መጥተው አክብሮትና ትህትና የተሞላበት ሠላምታ ሰጡኝ፡፡ በተለይ አባቱ ልክ ከዚህ በፊት እንደምንተዋወቅ ዓይነት እቅፍ አደረጉኝ፡፡ ረጅም ቁጥር ኮት ለብሰው በሩ ላይ ቆመው የነበሩት የጓደኛዬ እናትም ሠላምታ ሰጥተውኝ እንኳን ደህና መጣህ አሉኝ፡፡ ሴት ወንድን መጨበጥ ስለማይፈቀድላት ጓደኛዬም ስለእናቱ ይቅርታ ጠየቀኝ፡፡ ምግባራቸውን ወደድኩትና ለራሴ እንዲህ አልኩኝ «አፈንጋጮች ናቸው

ብለን በምንወነጅላቸው እነዚህ ሰዎች ሃይማኖቱን ከእኛ የበለጠ ያከብሩታል» አብረን በተጓዝንባቸው ቀናቶች ውስጥ የጓደኛዬን የከበሩ ምግባራትን፣ በራስ መተማመንና ለጋስነትን በሚገባ ተመለከትኩ፡፡ ከዚህ በኋላ በማንም ውስጥ ያላጋጠመኝን ጨዋነትና ሃይማኖታዊነትንም አየሁበት፡፡ የእንግድነት ስሜት አልተሰማኝም ልክ እቤቴ ያለሁ መሰለኝ፡፡

ጨለማው ሲሰፍን ለመኝታነት ወደተዘጋጀልን ወደ ቤቱ ፎቅ ወጣን፡፡ ቅዠት መሰል ሁኔታ ውስጥ ስለነበርኩ እንቅልፍ በቀላሉ ሊወስደኝ አልቻለም፡፡ በእርግጥ ባግዳድ ውስጥ ከሰይድ አብዱል ቃድር አል-ጂላኒ አጠገብ ነው ያለሁት? ስለአብዱልቃድር አል-ጂላኒ የቱኒዚያ ህዝብ ምን ያስባል ብሎ ሳቅ እያለ ጠየቀኝ፡፡

እሳቸው ፈፀሙት ስለተባሉ ተዓምራትና በስማቸውም ስለሚጠሩትና ስለተቋቋሙት ቦታዎች አጫውተው ጀመር፡፡ እሳቸው «የክበቡ ማዕከል» እንዲሆኑና የአላህ መልዕክተኛ መሐመድ የነቢዮች ሁሉ አለቃ እንደሆኑ ሁሉ አብዱልቃድርም የቅዱሳን አለቃ መሆናቸውን ነገርኩት፡፡ እግሮቻቸዉ በቅዱሳን አንገት ላይ ያሉ መሆናቸዉን «እያንዳንዱ ሰው በቤቱ ዙሪያ ሰባት ጊዜ ይሄዳል እኔ ግን ከድንኳኖቼ ጋር በቤቱ ዙሪያ እሄዳለሁ» ያሉት እሳቸው መሆናቸውንም ገለጽኩለት፡፡

ሼክ አብዱልቃድር ወደተከታዮቻቸው በመሄድ የታመሙትን እንደሚንከባከቡና ያዘኑትንም እንደሚያፅናኑ ላሳምነው ሞከርኩ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በብዙ አምላኮች እንደማመን ይቆጠራል የሚለውን የዋሃቢ እምነት ያሳደረብኝን ተጽዕኖ ሳልረሳው አልቀርም፡፡ ይህንን ሁሉ ስነግረው በጓደኛዬ ላይ ምንም ዓይነት የመደነቅ ስሜት ሳላይበት ስቀር ያልኩት ሁሉ

ትክክል አይደለም ብዬ እራሴን ለማሳመን ሞከርኩ፡፡ ከዚያ እሱ ስላለው አስተያየት ጠየቅኩት፡፡

ጓደኛዬም ሳቀና እንዲህ አለኝ «ዛሬ ማታ ጥሩ እንቅልፍ ተኛ፡፡ ሰውነትህን በደንብ አሳርፈው፤ የአላህ ፈቃድ ከሆነ ነገ ሄደን የሼክ አብዱልቃድርን መቃብር እንጎበኛለን»፡፡

ይህንን ስሰማ እጅግ በመደሰቴ ምነው አሁን ንጋት በነበር ብዬ ተመኘሁ፡፡ በጣም ደክሜ ስለነበር ድብን ያለ እንቅልፍ ተኝቼ ፀሐይ እላዬ ላይ ስታርፍብኝ ነው የነቃሁት፡፡ አርፍጄ በመነሳቴም የሱብሂ ሰላት አመለጠኝ፡፡ ጓደኛዬም ብዙ ጊዜ ሊቀሰቅሰኝ ሞክሮ ስላልተሳካለት እንዳርፍ እንደተወኝ ነገረኝ፡፡

## አብዱልቃር አል-ጂላኒና ሙሳ አል-ካዚም

ከቁርስ በኋላ ወደ ባብ አል-ሸይክ ሄደን ሁሌም ለመጎብኘት እመኘው የነበረውን ቦታ አየሁት፡፡ ልክ ለማየት እንደጓጓና ዘሎ እቅፍ ውስጥ ለመግባት እንደፈለገ ሰው ከሥፍራው ለመግባት በረርኩ፡፡
ልክ መካ ላይ በአሏህ ቤት ዙሪያ ተኮልኩለዉ እንዳየኋቸዉ ሀጅ አድራጊዎች በዚህም ስፍራ ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ በርካታ የሆኑ ጎብኝዎችን ተቀላቀልኩ፡፡ እያንዳንዶቹ ጎብኝዎች ከረሜላዎች ይበትኑ ነበር፡፡ እኔም ቶሎ ብዬ ሁለቱን አነሳሁ፡፡ በረካውን ለማግኘት ስል አንዱን በላሁት፤ ሌላውን ደግሞ ማስታወሻ እንዲሆነኝ ወደ ኪሴ አስገባሁት፡፡ ከሥፍራው

ላይ ሰግጄ የልመና ፀሎቴንም አድርሼ ልክ ከዘምዘም እንደምጠጣ ዓይነት እዛ ያለውን ውሃ ግጥም አደረኩት፡፡

ቱኒዚያ ላሉት ጓደኞቼ የሼክ አብዱልቃድርን ቦታ ከነአረንጓዴው ጉልላቱ ለማሳየት ጥቂት ፖስት ካርዶችን እስክጽፍ ድረስ እንዲጠብቀኝ ጓደኛዬን ጠየኩት፡፡ እነሱ ሊደርሱበት ካልቻሉበት ሥፍራ ያመጣኝን ከፍተኛ ደረጃዬን ቱኒዚያ ውስጥ ላሉት ጓደኞቼና ዘመዶቼ እንደማስረጃነት ለማቀረብ ፈለግሁ፡፡

በዋናው ከተማ እምብርት ላይ በሚገኝ አንድ የታወቀ ምግብ ቤት ውስጥ ምሳችንን በላን፡፡ ከዚያም ጓደኛዬ አልካዚሚያህ ወደሚባል ሥፍራ ወሰደኝ፡፡ የዚህን ቦታ ስም ላውቅ የቻልኩት ጓደኛዬ ለታክሲ ሹፌሩ ሲነግረው ሰምቼ ነው፡፡ አልካዚሚያህ እንደደረስን ወደ አንድ አቅጣጫ ይጓዙ ከነበሩ ከተለያዩ አገሮች ከመጡ ሰዎች፣ ህፃናት ወንድና ሴቶች ጋር ተቀላቀልን፡፡ እያንዳንዱ ሴትም ሆነ ወንድ የሆነ ነገር ተሸክሟል፡፡ ይህም የመካን የሀጅ ወቅት አስታወሰኝ፡፡ ከወርቅ ከተሰሩ ጉልላቶችና ሚናሪዎች የሚወጡ ነፀብራቆችን እስካየሁ ድረስ ሰው ሁሉ ወዴት እንደሚሄድ አላወቅሁም ነበር፡፡ የሺአ መስጊድ እንደሆነ ገባኝ፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳ እስልምና የከለከለው ነገር ቢሆንም እነሱ መስጊዶቻቸውን በወርቅና በብር እንደሚያስጌጡ ከዚህ በፊት አውቅ ስለነበር ነው፡፡ ወደ መስጊዱ ስንገባ ዘና የማለት ስሜት አልተሰማኝም፡፡ የጓደኛዬን ስሜት መጠበቅና ካለምንም ምርጫ እሱኑ መከተል ነበረብኝ፡፡

የመጀመሪያውን በር አልፈን ስንገባ አንዳንድ አዛውንቶች ሲዳስሱትና ሲሰሙት ተመለከትኩ፡፡ እኔም ከዚያ ላይ የተፃፈውን ፁሁፍ በማንበብ

ራሴን በሥራ ጠመድኩ። «ያልተሸፈኑ ሴቶች እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም» ከታች የኢማም አሊ ጥቅስም «ሴቶች ገላቸውን የሚያሳዩ ልብሶች የሚለብሱበት ጊዜ ይመጣል፣ እንዲያውም እራቁታቸውን . . . ወዘተ»

ወደ መስጊዱ (Shrine) ስንደርስ ጓደኛዬ ወደ ዉስጥ ለመግባት ፈቃድ በመጠየቅ ላይ ሳለ እኔም ሥራ እንዳልፈታ ግዙፋን መግቢያ እየተመለከትኩ በዚያ ሁሉ ወርቅና ብር ላይ በተቀረፁት የቁርዓን ጥቅሶች እጅግ ተደነቅሁ። ጓደኛዬ መጀመሪያ ሲገባ እኔም ተከተልኩት። አእምሮዬም መጽሐፍት ውስጥ ባነበብኳቸው ሺዓን በሚያወግዙ አፈ ታሪኮችና ተረቶች አይምሮዬ ሙሉ ለሙሉ ተሞልቶ ነበር። ከዚህ በፊት ፍፁም አይቼ የማላውቀው የተቀረፁ ጹሁፎችና ጌጦች በመቅደሱ ውስጥ ተመልክቼ በነሱም እንዲሁ እጅግ ተደነቅሁ። ባልታወቀና እንግዳ በሆነ ዓለም ውስጥ የገባሁ መሰለኝ። በመቃብሩ ዙሪያ በመዞር የመቃብሩን ብረቶችና ጠርዞች እየሳሙ የሚያለቅሱ ሰዎችን በጥላቻ ተመለከትኩ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከመቃብሩ አጠገብ ይሰግዳሉ። በዚህን ጊዜ ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተናገሩት ነገር በአእምሮዬ መጣ «የቅዱሳኖቻቸውን መቃብሮች መስጊዶች ያደረጉትን አይሁዳዎችና ክርስቲያኖችን አላህ ረግሞአቸዋል» ወዲያው እግሩ ገባ እንዳለ ማልቀስ የጀመረውን ጓደኛዬን ፀሎቱን ያድርስ ብዬ ትቼው ከአጠገቡ ሄድኩ። ባጌጠ መደብ ላይ በተለይ ስለጉብኝት ተቀርፆ  የተፃፈውን ጠጋ ብዬ አነበብኩና የማላውቃቸው ስሞች የያዘ በመሆኑ ሊገባኝ አልቻለም። ወደ አንድ ጥግ ስፍራ ሄድኩና የቁርዓንን መክፈቻ ሱራህ (አል-ፋቲሃ) ቀራሁና በመቃብር ውስጥ ያለውን ሰውዬ አላህ ምህረት እንዲያደርግለት እንዲህ ሲል ጠየቅኩት «ያ አላህ ይህ የሞተ ሰው ሙስሊም ከሆነ ምህረት አድርግለት ምክንያቱም ከእኔ የበለጠ አንተ ታውቃለህና» ጓደኛዬም አጠገቤ

መጥቶ እንዲህ ሲል በጆሮዬ ሹክ አለኝ፡፡ «ይህንን ሥፍራ የ«ሓጃ» በር ብለን ስለምንጠራው አንተም የምትፈልገው ነገር ካለ እዚሁ ቦታ አላህን ብትጠይቀው ይሻላል» ይህንን ሲለኝ ከቁም ነገር አልቆጠርኩትም፡፡ ፈጣሪ ይቅር ይበለኝ፡፡ ጥቁር ወይም ነጭ ጥምጣም ራሳቸው ላይ ያጠለቁትን የብዙ ጊዜ ስግደት ምልክት ግንባራቸው ላይ የሚታየውን ክብራቸውንና መልኮቻቸውን አጉልቶ ከሚያሳየው በሽቶ የራሱ ጢሞቻቸውን ጋራ ሽማግሌዎችን እመለከታቸው ነበር፡፡ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ልክ ወደ መቅደሱ እንደገባ ማልቀስ እንደሚጀምር ተረዳሁ፡፡ እኔም እራሴ እንዲህ በማለት ጠየቅኩት «ይህ ሁሉ እንባ የውሸት ሊሆን ይችላል?» እነዚህ ሁሉ ትላልቅ ሽማግሌዎች ተሳስተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ባየሁት ነገር ተገርሜና ግራ ገብቶኝ ከዚያ ወጣሁ፡፡ ጓደኛዬም ለመቅደሱ ጀርባውን ላለመስጠት ሲል የኋሊዮሽ እየተራመደ ወጣ፡፡ «ያ የማን ደሪህ (መቃብር) ነው?» ብዬ ጠየቅኩት፡፡

«የኢማም ሙሳ አል-ካዚም ነው፡፡» አለኝ፡፡

«ሙሳ አል-ካዚም ማነው?» ብዬ ጠየቅኩት፡፡

«ሱብሀነላህ! እናንተ የሱኒ ወንድሞቻችን አስኳሉን ትታችሁ ቅርፊቱን ነው የያዛችሁት» አለኝ፡፡

«አስኳሉን ትታችሁ ቅርፊቱን ነው የያዛችሁት ስትል ምን ማለትህ ነው?» አልኩት፡፡

እንደ ማረጋጋት አደረገኝና እንዲህ አለኝ፡፡

«ወንድሜ! ኢራቅ ከመጣህ ጀምሮ ስለ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ ከማውራት አልተቆጠብክም፡፡ ለመሆኑ ማን ናቸው አብዱልቃድር አል-ጂላኒ? እንዴት ይህን ያህል ትኩረትህን ሊስቡ ቻሉ?»

በዚህን ጊዜ በኩራት እንዲህ በማለት መልስ ሰጠሁ፡፡

«ከነብዩ የዘር ሐረግ ከሆኑት ሰዎች አንዱ ናቸው፡፡ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ነብይ ቢኖር ኖሮ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ ይሆኑ ነበር፡፡»

ከዚያም «ወንድም አል-ሰማዊ! ኢስላማዊ ታሪክን ታውቃለህ?» ብሎ ጠየቀኝ፡፡

ያለምንም ማመንታት «አዎ! በእርግጥ ከኢስላም ታሪክ የማውቀው ጥቂቱን ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም መምህሮቻችን ብዙም እንዳንማር ይከለክሉን ነበር፡፡ መጥፎና የጨለማ ታሪክ ስለሆነ መማሩ አስፈላጊ አይደለም ይሉን ነበር፡፡ ለምሳሌ የአረብኛ መምህራችን «ነህጁል በላጋህ» ከሚሰኘው መጽሐፍ በዓሊ የተነገረውን «አል-ሽቅሽቂያህ» የተሰኘውን መነባነብ ሲያስተምሩን እኔና ሎሎችም ተማሪዎች በጣም ይገርመን ነበር፡፡» እኔ ግን የሚከተለውን ጥያቄ ለመጠየቅ ድፍረቱን አግኝቼ ነበር፡፡

«እነዚህ አባባሎች በዕውነቱ የዓሊ ቃላት ናቸው?»

«ይህም የላቀና የመጠቀ የአነጋገር ችሎታ ያለዉ ሌላ ማን ሊሆን ይችላል? እኒህ ቃላት የእሳቸው ባይሆኑ ኖሮ የግብጽ ሙፍቲ ሼክ መሐመድ አብዱህና የመሳሰሉት የሙስሊም ምሁራን ለምን ሊተረጉሟቸው በቁ» ሲል መለሰልኝ፡፡ እኔም ቀጠል አድርጌ «ኢማም አሊ አቡበክርንና ዑመርን የኻሊፋነት ሥልጣን መብቴን ዘርፈውኛል በማለት ከሰዋቸዋል» አልኩት፡፡

አስተማሪውም ክፉኛ ተቆጥቶ ገሠፀኝና ከክፍል እንደሚያባርረኝ ካስፈራራኝ በኋላ አክሎም የሚቀጥለውን ተናገረ «እኛ የምናስተምረው የአረብኛ ቋንቋ አነጋገር ዘይቤን እንጂ ታሪክን አይደለም፡፡ በሙስሊሞች መካከል ደም ስላፈሰሰው ስለጨለማው ታሪክ ምንም የሚያገባን ነገር የለም፡፡ አላህ ጎራዴዎቻችንን ከደማቸው እንዳነፃ ሁሉ እኛም እነሱን ባለማውገዝ ምላሳችንን እናንፃ»

በአነጋገሩ ምንም አልረካሁም፤ እንዲያውም በዚህ አስተማሪ ላይ ጥላቻ አደረብኝ:: በብዙ አጋጣሚዎች እስላማዊ ታሪክን ለማጥናት ብሞክርም የማነባቸው በቂ መፃህፍት ለማግኘትም ሆነ ለመግዛት አቅሙ ስላልነበረኝ አልተሳካልኝም:: ከተማሩት ሰዎች መካከል እንኳ በዚህ የትምህርት ዓይነት ላይ ፍላጎት ያላቸውን ላገኝ አልቻልኩም:: እንዲያው ሁሉም ነገሩን ጠልቶ ላለማየት ጭራሹንም ለመርሳት የተስማሙ ይመስላል:: በዚህም ምክንያት የተሟላ የታሪክ መጽሐፍ ያለው ሰው አልነበረም::

እናም ጓደኛዬ ስለ ታሪክ እውቀቴ ሲጠይቀኝ እንዲያው ልቃወመው ስለፈለግሁ ብቻ አወንታዊ መልስ ሰጠሁት:: ሆኖም መልሴ «በህዝብ አመጾች፣ አሻጥሮችና ቅራኔዎች የተሞላ የጭለማ ታሪክ ነው» እንደማለት ነበር:: እሱም «አብዱልቃድር አል-ጂላኒ መቼ እንደተወለዱ ታውቃለህ?» ሲል ጠየቀኝ «ወደ ስድስተኛውና ሰባተኛው ምዕተ ዓመት ነው» ሲል መለስኩለት:: «በአላህ መልዕክተኛና በእሳቸው መካከል ስንት ምዕተ ዓመታት አልፈዋል?» ሲል ጠየቀኝ «ስድስት ምዕተ ዓመታት» አልኩት:: «በአንድ ምዕተ ዓመት ሁለት ትውልድ ነበር ብለን ብንወስድ በአብዱልቃድር አል-ጂላኒና በመልዕክተኛው መካከል እንግዲህ ቢያንስ አስራ ሁለት ትውልድ ነበር ማለት ነው» አለኝ::

እኔም በዚህ ተስማማሁ፤ እሱም ቀጠል በማድረግ «ይህ ሙሳ ኢብን ጃዕፋር ኢብን መሐመድ ኢብን አሊ ኢብን አል-ሁሴይን ኢብን ፋጢማ አል-ዛህራ ነው:: በእሳቸውና ቅም አያታቸው በሆኑት በአላህ መልዕክተኛ መካከል አራት ትውልዶች ብቻ ነበሩ:: የተወለዱትም በትክክል በሁለተኛው ሂጅራ

ምዕተ ዓመት ነበር፡፡ እና ታዲያ ለአላህ መልዕክተኛ ቅርብ የነበሩት ሙሳ ናቸው ወይስ አብዱልቃድር?» በማለት ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡

ምንም ሳላስብ «በእርግጥ ሙሳ ናቸው ግን ለምንድን ነው እኛ ልናውቃቸው ያልቻልነው ወይም ሰዎች ስለእሳቸው ሲያወሩ ያልሰማነው?» አልኩ፡፡ «ዋናው ነጥብ እዚህ ላይ ነው በፊትም ያልኩህ ይህንን ነው፡፡ አሁንም እንድደግመው ፍቀድልኝ አስኳሉን ችላ ብላችሁ ቅርፊቱን ብቻ ተቀብላችኋል፤ እናም እባክህን እኔን አትውቀሰኝ ይቅርታም አድርግልኝ» አለኝ፡፡ ብዙ ተጨዋወትን፣ በዐቂዳ ላይ የሚወያዩ መምህራንና ተማሪዎች ካሉበት ሥፍራ ስንደርስ ጎራ አልን፡፡ እዛም ገብተን ቁጭ እንዳልን ጓደኛዬ ልክ ቀደም ያለ ቀጠሮ እንዳለው ሁሉ ሰው ለማግኘት በዓይን መፈለግ ይጀምራል፡፡
አንድ ሰው ወደ እኛ ቀረብ ብሎ ሠላምታ ከሰጠን በኋላ ከጓደኛዬ ጋር መነጋገር ጀመረ፡፡ ከንግግራቸውም እንደሰማሁት በዩኒቨርስቲ ውስጥ አብረው እንደሚሰሩ አወቅሁ፣ ሌላም የሥራ ባልደረባቸው አሁን ወደዚሁ ሥፍራ እንደሚመጣም ተረዳሁ፡፡ ጓደኛዬም ወደ እኔ ዞር ብሎ እንዲህ አለኝ «እዚህ ቦታ ያመጣሁህ በባግዳድ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ፕሮፌሰር ከሆነ የታሪክ ምሁር ጋር ላስተዋውቅህ ነው፡፡ የዶክትሬት ማዕረጉን ለማግኘት ያበቃው ጽሁፍ ስለ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ ነው፡፡ ከአላህ እርዳታም ጋር ይህ ምሁር ለአንተ ብዙ ሳይጠቅምህ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም እኔ በታሪክ የጠለቀ ዕውቀት የለኝም» የታሪኩ ሰው እስኪመጣ ድረስ ቀዝቃዛ ጭማቂ እየጠጣን ቆየን፣ እንደደረሰም ተዋወቅንና ጓደኛዬም በአብዱልቃድር አል-ጂላኒ ላይ አጠር ያለ ታሪካዊ ማብራሪያ እንዲሰጠኝ ምሁሩን ጠየቀው፡፡ ቀዝቃዛ መጠጡን ከደጋገምን በኋላም ለእራሴ ስለ አገሬና ስለ ስራዬ

ጥያቄዎችን ካቀረበልኝ በኋላ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ ቱኒዚያ ውስጥ ስለ እሳቸው ዝና እንዳጫውተው ጠየቀኝ፡፡

ይህን በተመለከተ ብዙ ነገር ነገርኩት፡፡ በሚዕራጅ ምሽት ወቅትም ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰባተኛው ሰማያት ያረጉበት ምሽት ጅብሪል እቃጠላለሁ ብሎ ፈርቶ በዘገየበት ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ እሽኮኮ እንዳደረጓቸው የቱኒዚያ ህዝብ ይናገራል፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሏቸው «እግሮቼ በአንተ አንገት ላይ ናቸው፤ ያንተም እግር እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በሁሉም ቅዱሳን አንገት ላይ ይሆናል»

ያልኩትን በሰማ ጊዜ የታሪክ ምሁሩ ከት ብሎ ሳቀ፡፡ ነገር ግን የሳቀዉ በነገርኩት ታሪክ ይሁን ወይም ፊት ለፊቱ በቆመው ቱኒዚያዊ መምህር ሊገባኝ አልቻለም፡፡

ስለቅዱሳንና ሃይማኖታዊ ሰዎች አጭር ውይይት ካደረግን በኋላ ስለእሳቸው ለሰባት ዓመታት ምርምር እንዳካሄደ ነገረኝ፡፡ ለዚሁም ተግባር ስለ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ የተፃፉ ጹሁፎች አሉ ወደተባሉበት አገሮች ፓክስታን ውስጥ ወደሚገኘው ለሆር፣ ቱርክ፣ ግብጽና እንግሊዝ ወደ ሌሎችም መጓዙን ነገረኝ፡፡ ጹሑፎቹንም በደንብ መመርመሩንና ፎቶግራፍ እንዳነሳቸው ገለጸልኝ፡፡ ይሁን እንጂ አብዱልቃድር አል-ጂላኒን ከመልዕከተኛው የትውልድ ሀረግ ጋር የሚያገናኝ ምንም ማረጋገጫ እንዳላገኘ ነገረኝ፡፡ ያገኘው ነገር ቢኖር አብዱልቃድር አል-ጂላኒ፣ ለአንዱ ልጃቸው በፃፉት ግጥም አዘል ፅሁፍ ውስጥ ቅድመ አያቴ የአሏህ መልዕክተኛ ነበር» ይህም ምናልባትም «እኔ የእያንዳንዱ ሃይማኖታዊ ሰው ቀደምት አባት ነኝ»

ለሚለው የነቢዩ አነጋገር አንዳንድ ምሁራን የሚሰጡት ትርጓሜ ይሆናል፡፡ በቅርብ የተካሄደ የታሪክ ጥናታዊ ምርምር አብዱልቃድር አል-ጂላኒ ኢራን ውስጥ ከሚገኝ ጂላን ከተባለ ትንሽ ከተማ የመጡ የፋርስ ሰው እንጂ አረብ እንዳልነበሩ አረጋግጧል በማለት አጫወተኝ፡፡ እሳቸውም ወደ ባግዳድ መጥተው ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ አስከፊ የሞራል ብልሹነት በሰፈነበትም ወቅት ማስተማር መጀመራቸው ነገረኝ፡፡ ፈሪሃ አላህ ያደረባቸው ሰው ስለነበሩም ሰው ሁሉ ይወዳቸው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ እሳቸው ከሞቱ በኋላ በማንኛውም የሱፊ ጠሪቃ መምህር ተከታዮች እንደሚደረገው ሁሉ፣ ለሳቸው መታሰቢያነት ሲሉ የቃድሪያህ ሱፊን ጠሪቃ መሰረቱላቸው፡፡ በማከልም «እውነቴን ነው የምልህ ይህን ሁኔታ በተመለከተ አረቦች በሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ ነዉ ያሉት» አለኝ፡፡

የወሃቢይ ቁጣም በጭንቅላቴ ውስጥ ቱግ አለና «ለካስ ዶክተር በአስተሳሰብህ ወሀቢይ ነህ፡፡ አሁን አንተ እንደምትለው ነው የሚያምኑት፤ እነሱም ቅዱሳን የሚባል ነገር የለም ብለዉ ያምናሉ» በማለት ተናገርኩት፡፡ እሱም «ፍፁም እኔ የወሀቢይ እምነት ተከታይ አይደለሁም፡፡ ሙስሊሞች ወደማጋነን ማዝመማቸውና ክርር ያሉ አመለካከቶችን መቀበላቸው ያሳዝናል፡፡ በትክክለኛ አስተሳሰብም ሆነ በመደበኛ ህግ ላይ ያልተመሰረቱ አፈ- ታሪኮችንና ተረቶችን ወይ ሙሉ ለሙሉ አምነው ይቀበላሉ፣ አልያም ሙሉ ለሙሉ ይክዳሉ፤ ሌላው ቀርቶ ከእነሱ የአስተሳሰብ መንገድ ጋራ ስለማይጣጣም የነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ) አባባሎችና ታምራቶችን እንኳ ይክዳሉ» አለኝ፡፡

ለምሳሌ ሱፊዎች አብዱልቃድር አል-ጂላኒ በአንድ ጊዜ ወይም በተመሳሳይ ሰዓት እንበል ባግዳድም ቱኒዝም ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ያምናሉ፡፡ ቱኒዝ

ውስጥ አንድ የታመመ ሰው እያዳኑ በዛው ሰዓት ባግዳድ ውስጥ አንድ በቲግሪስ ወንዝ ውስጥ የሰጠመን ሰው ከውሃው በማውጣት ያድናሉ ይላሉ፡፡ ይህ ፍፁም ማጋነን ነው፡፡ ወሃቢዮች ደግሞ ሁሉንም ነገር በመካድ ለሱፊ አስተሳሰብ ወይም እምነት የመልስ ምት ለመስጠት ብለው የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አማላጅነት እንኳን ከአንድ አምላክ በላይ በብዙ አምላኮች ማመን(ሽርክ) ነው ይላሉ፡፡ ይህ አጉል ቸልተኝነት ነው፡፡ ነገሩ እንዲህ አይደለም ወንድሜ? እኛ አላህ በታላቁ መጽሐፍ ውስጥ እንደተናገረው «***በሰዎች ላይ መስካሪዎች ትሆኑ ዘንድ እንዲሁ መካከለኛ ህዝብ አደረግናቸሁ፡፡***» **(ቅዱስ ቁርአን 2:143)**

ያለውን በሙሉ በደንብ ወደድኩት፡፡ ለዚህም አመሰገንኩት፡፡ በውይይቱ ካነሳቸው ሃሳቦች ውስጥ አሳማኝ የሆኑትን ጠቀስኩለት፡፡ የያዘውን ቦርሳ ከፈተና ስለ አብዱልቃድር አል-ጂላኒ የፃፈውን መጽሐፍ አውጥቶ ስጦታ አበረከተልኝ፡፡ ከዚያ ወደ ቤቱ እንድሄድ ሲጋብዘኝ እንደማልችል ነግሬው ይቅርታ ጠየቅኩት፡፡ ጓደኛዬም እስኪመጣ ድረስ ስለ ቱኒዝና ሰሜን አፍሪካ ስንጨዋወት ቆየን፡፡ ሙሉውን ቀን እየዞርን ጓደኞቻችን ስንጠይቅና ስንወያይ ውለን ከጓደኛዬ ጋር ተያይዘን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡

በጣም ድቅቅና ድክም ስላልኩ ቀጥታ ወደ መኝታዬ አመራሁ፡፡ በጠዋት ተነስቼ ስለ አብዱልቃድር ህይወት የሚያወሳውን መጽሐፍ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ ጓደኛዬ ከእንቅልፍ በተነሳበት ጊዜ መጽሐፉን አጋምሼው ነበር፡፡ ቁርስ እንድበላ በተደጋጋሚ ቢጠይቀኝም እኔም መጽሐፉን ካልጨረስኩ አሻፈረኝ አልኩ፡፡ ከጥርጣሬ መንፈስ ውስጥ ከከተተኝ መጽሐፍ ጋር ተጣብቄ ቀረሁ፡፡

## ጥርጣሬና ጥያቄ

በጓደኛዬ ቤት ውስጥ ለሦስት ቀናት ተቀመጥኩ። ከእኔ ጋር ከተገናኙትና ጨረቃ ላይ የሚኖሩ መስለው ከታዩኝ ሰዎች የሰማሁትን ሁሉ በነዚህ ቀናት ውስጥ አረፍ ብዬ በጥንቃቄ አሰላሰልኩ። ለምንድን ነው ሰው ሁሉ ሁሌም ስለነሱ መጥፎ ነገሮች የሚነግረን? እኔስ ስለነሱ ምንም ሳላዉቅ ለምንድን ነዉ የምንቃቸዉና የምጠላቸዉ? ምናልባትም ይህ ሁሉ ሊመነጭ የቻለው እነሱ አሊን ነው የሚያመልኩት ኢማምቻቸውን እንደ አምላክ ነው የሚቆጥሯቸው፣ የሞተ ሰው ተመልሶ እንደሚወለድ ያምናሉ፣ አላህን ትተው በድንጋዮች ያመልካሉ እየተባለ ከሚናፈሰው መሰረተ-ቢስ ወሬ ነው። አባቴም ከመካ (ከሐጅ) እንደተመለሰ እኒህ ሰዎች በነቢዩ መቃብር ላይ ቆሻሻ ሲወረውሩ በሳውዲዎች ተይዘው የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው...ወዘተ ብሎ ነገሮኝ ነበር። ሌላው ሙስሊም ይህን ሰምቶ ሺአዎችን ቢጠላና ቢኮንን አልፎም ቢገድል አያስደንቅም። አሁን ግን በዓይኖቼ ካየሁና በጆሮዎቼም ከሰማሁ በኋላ እንዴት እነዚህን መሰረተ-ቢስ ወሬዎች ማመን ይቻለኛል?

ከእነዚህ ሰዎች መሀል ከሳምንት በላይ በኖርኩበት ጊዜ ውስጥ ከትክክለኛ አስተሳሰብ (ሎጂክ) ጋር የማይጣጣም ምንም ነገር አላየሁም ወይም አልሰማሁም። እንዲያውም አዲህን የሚያመልኩበትን መንገድ ወደድኩት። ሰላታቸውን፣ ስነ-ምግባራቸውን፣ ለተማሩት ሰዎቻቸው ያላቸውን አክብሮት ሁሉ ወድጄ ከእነሱ አንዱ ለመሆን ተመኘሁ። ራሴን እንዲህ በማለት መጠየቁን ተያያዝኩት «የአላህን መልዕክተኛ ይጠሏቸዋል። የሚባለው እውነት ነውን?» ብዙ ጊዜ እነሱን ለመፈተን ሲል የእሳቸውን ስም በማነሳበት ጊዜ «አላህ ሆይ! በሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ ሰላትና ሰላም

አውርድ» በማለት ከልባቸው ይጮሃሉ:: በመጀመሪያ ላይ አስመሳዮች ናቸው ብዬ አሰብኩ:: ቆየት ብዬ ግን በእኛ ፅሁፍ ያላገኘሁትን በተለይም ለመልዕክተኛው ታላቅ አክብሮትንና ፍርሃትን በብዛት ያገኘሁባቸውን የነሱን አንዳንድ መፃህፍትን ካነበብኩ በኋላ በእነሱ ላይ ያለኝን መጥፎ አስተሳሰብ ለወጥኩ:: ለምሳሌ:- ከተልዕኮአቸው በፊትም ሆነ በኋላ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከስህተት ፍፁም የጠሩ መሆናቸውን ያምናሉ:: እኛ ሱኒዎች ግን ከስህተት ፍፁም የጠሩት ቁርአን በሚያስተላልፉበት ወቅት ብቻ እንጂ ከዚያ ውጭ ስህተት ሊሰሩ የሚችሉ አንደኛ የሰው ፍጡር ናቸው ብለን እናምናለን:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይሳሳቱ እንደነበርና የቅርብ ጓደኞቻቸውም እንደሚያርሙአቸው የሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎች አሉን:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስህተት ሊሰሩ ይችላሉ የሚለውን ነገር ሺአዎች ፍፁም አይቀበሉትም:: እንዴት ነው ከዚህ በኋላ የአላህን መልዕክተኛ ይጠሏቸዋል የሚባለውን ለማመን የምችለው? እንዴት ይቻለኛል? አንድ ቀን ከጓደኛዬ ጋር ስንወያይ ሳይደብቀኝ በግልጽ እንዲመልስልኝ ተማጸንኩት:: ውይይታችንም እንደሚከተለው ነበር::

- አላህ ይውደዳቸዉና፣ አላህ ክብር ይስጣቸውና አሊን ከነቢዮች እኩል ቦታ ትሰጥዋቸዋላችሁ ምክንያቱም ስማቸው ሲጠራ በሰማሁ ቁጥር «አለይሂ ሰላም (ሰላም በሳቸው ላይ ይሁን)» ትላላችሁ፤
- ይህ ትክክል ነው የታማኞቹን አለቃ (አሚሩል ሙእሚኒን) የኢማም አሊ ወይም ከእሳቸው ከተገኙት ኢማሞች አንዱ ስም ሲጠራ «ዐ.ሰ» እንላለን:: ይህም እነሱ ነቢዮች ናቸው ማለት አይደለም፤ ሆኖም ግን ከነቢዩ የትውልድ ሐረግ የተገኙ ስለሆኑና አላህም በነርሱ ላይ ሰላምን እንድናወርድ አዞናል:: ለዚህም ነዉ «የአላህ በረከትና ሰላም በነርሱ ላይ ይዉረድ» ማለት የተፈቀደልን፤

- አየህ ወንድሜ! በነቢዩ መሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከሳቸው በፊት በመጡት ነቢያት በስተቀር ለሌላ ለማንም «ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም» አንልም። አላህ በሁሉም ይደሰትና ይህ አሊን ወይም የሳቸውን ትውልድ አይመለከትም፤
- ሀቁን በሚገባ እንድትረዳው ብዙ እንድታነብ ልጠይቅህ እወዳለሁ፤
- ወንድሜ! የትኞቹን መፃህፍት ላንብብ? አንተው ራስህ አይደለም እንዴ የአህመድ አሚን መፃህፍት በሺአ ላይ እንደ ማስረጃነት ሊቀርቡ አይችሉም ያልከኝ? እንደዚሁም ደግሞ የሺአ መፃህፍት በእኛ እምነት ላይ ዋቢ ሆነዉ መቅረብ ስለማይችሉ አንቀበላቸውም። የክርስቲያኖችን መጻህፍት አልተመለከትክም? ኢየሱስ «እኔ የአላህ ልጅ ነኝ» ብሎ ተናግሯል ብለው የሚያቀርቡትን አባባል ፍጹም የሆነውን እውነት የሚናገረው ታላቁ ቁርዓን ግን ኢየሱስ እንዲህ አለ ብሎ ይጠቅሰዋል «***እኔ ለእነሱ ምንም አልተናገርኩም አንተ ካዘዝከኝ በስተቀር፣ ያም የእኔንና የእናንተን አምላክ አላህን እንዲያመልኩ***»
- በትክክል አስቀምጠህዋል፣ እንደዚያ ብያለሁ እኔ ከአንተ የምፈልገው ሙስሊም እስከሆንክ ድረስ አዕምሮህን ትክክለኛ አስተሳሰብህን (ሎጂክህን) እንድትጠቀም ብሎም ክርክርህ በታላቁ ቁርዓንና በነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ነው። ከአይሁድ ወይም ከክርስቲያን ጋር ቢሆን የምንነጋገረው ክርክራችን በሌላ ነገር ላይ የተመሰረተ ነበር።
- ደህና! እውነት የማገኘው የትኛው መጽሐፍ ውስጥ ነው? ሁሉም ፀሐፊ፣ ሁሉም ቡድን ሁሉም እምነት የእኔ ነው ትክክል ይላል።
- አቋምና ቡድን ሳይለይ ሁሉም ሙስሊሞች የሚስማሙበት አንተ ግን የማታውቀው አንድ ተጨባጭ ምሳሌ እሰጥሃለሁ።

- አምላክ ሆይ! ተጨማሪ እውቀት ስጠኝ! በል፡፡
- በሚቀጥለው የቁርዓን ጥቅስ ላይ የተሰጠውን አስተያየት አንብበሃል? «***አላህና መላዕክቱ፣ ነቢዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ፣ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፣ የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ***» **(ቅዱስ ቁርዓን 33:56)**

ይህ ከላይ የተጠቀሰው የቁርዓን ጥቅስ የወረደላቸው የነብዩ የቅርብ ጓደኞች እሳቸው *ጋር* ቀርበው «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርስዎን እንዴት በማክበር ሠላምታ ሰላም እንደምንል እናውቃለን፣ ሆኖም ግን በእርስዎ ላይ እንዴት ሰላት እንደምናወርድ አናውቅም» ማለታቸውን የሺአም የሱኒም አስተያየት ሰጭዎች ይስማማሉ፡፡

ይህን የሰለዋት አደራረግ አስመልክቶ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰሃቦቻቸው እንደሚከተለዉ አስተምረዋል፡፡ እንዲህም አሏቸዉ፡-
«እንዲህ በሉ፡- «አሏህ ሆይ! በነብዩና በቤተሰቦቹ ላይ ሰላት አዉርድ፡፡ በኢብራሂም እና በቤተሰቦቹ ላይ እንዳወረድክ ሁሉ አንተ የምትመሰገንና ሀያል ጌታ ነህ!»

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አክለዉም እንዲህ አሉ፡- «ጎደሎ ሰለዋት (አል-በትራ) በኔ ላይ አታዉርዱ፡፡» «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጎደሎ ሰለዋት ምንድን ነው?» «ለምንድን ነው አላህ በመሐመድ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያውርድ ብላችሁ የምታቆሙት? አላህ እኮ እንከን የለሽ ነው፣ የሚቀበለውም እንከን የለሹን ነው» ከዚህ በኋላ የነቢዩ ተከታዮች እሳቸውን ትዕዛዝ በመከተል ሙሉ ሰለዋትን ያደርጉ ጀመር፡፡

ለነሱ አክብሮት ሲሉ ኢማም አል-ሻፊዒ የአህሉል ቤይት ውዴታን አስመልክተው የሚከተለውን ስንኝ ቋጥረዋል፡፡

*የነቢዩ ቤተሰቦች ውዴታ*
*በቁርአን የወረደ ነው ክዔታ*
*በትዕዛዝ የመጣ ነው ፍቅራችሁ*
*ልባችን ውስጥ ቀዳሚ ቦታ ልንሰጣችሁ*
*የታላቅነታችሁ መገለጫ ምስክሩ*
*በየሰላታችን ውስጥ ልትዘከሩ*
*በናንተ ላይ ሰለዋት ያላወረደ በየሰላቱ*
*ሶላቱ ብላሽ ነው የማይጠቅም ከንቱ፡፡*

የተናገረውን ሁሉ በጥሞና አዳመጥኩት፣ ቃላቶቹም ወደልቤ ሰርፀው በመግባት በአወንታዊነት አስተጋቡ፡፡ በእርግጥ እሱ የተናገራቸውን ሁሉ አርዕስታቸውን ባላስታውሰውም አንዳንድ መፃህፍት ላይ እንብቤአቸዋለሁ፡፡ ሰለዋትን በነቢዩ ላይ ስናወርድ ቤተሰቦቻቸውንም ተከታዮቻቸውንም እንጨምራለን፡፡ ግና ሺአዎች እንደሚያደርጉት በማክበር ሠላምታ ውስጥ አሊን ለይተን አንጠቅስም ስል ተናገርኩ፡፡

«ስለ አል-ቡኻሪ ምን አስተያየት አለህ?» በማለት ጠየቀኝ፡፡ «የታወቁ የሱኒ ኢማም ናቸው፡፡ የእሳቸውም መጽሐፍ ከአላህ መጽሐፍ (ቁርዓን) ቀጥሎ በጣም አስተማማኝ የሆነ መጽሐፍ ነው» ስል መለስኩለት፡፡ ከዚያም ብድግ አለና ወደ መጽሐፍ መደርደሪያው ሄደ፡፡ «ሰሂህ አል-ቡኻሪ»ን ሳብ አድርጎ አውጥቶ ገለጥ ገለጥ አደረገና አንድ ገጽ ላይ ሲደርስ እንደነበረው ሰጠኝ፡፡ ከእከሌ እከሌ እንደተወራው አሊ (ሰላም በርሱ ላይ ይሁንና)...» ፍፁም ዓይኔን ላምነው አቃተኝ በጣም ከመገረሜ የተነሳ መጽሐፉ «ሰሂህ አል-ቡኻሪን» ላይሆን ይችላል ብዬ እስከማሰብ ደረጃ ደረስኩ መጽሐፉን

እያገላበጥኩ ማየት ጀመርኩ፡፡ የጥርጣሬ አመለካከቴን የተረዳው ጓደኛዬም መጽሐፉን ከእጄ ተቀብሎ ሌላ ገጽ አውጥቶ ሰጠኝ፡፡ «አሊ ኢብን አል-ሁሴን (ሰላም በርሱ ላይ ይሁንና) ...» የሚል በድጋሚ አነበብኩት «ጥራት ለአላህ የተገባ ነው» ከማለት ሌላ ምንም መልስ ልሰጠው አልቻልኩም፡፡ ጓደኛዬም በመልሴ በመርካት እዚያው ክፍል ውስጥ ጥሎኝ ወጣ፡፡ ያነበብኩትን መልሼ በመደጋገም መጽሐፉም በግብጽ ውስጥ በአል-ሀለቢና ልጆቹ ኩባንያ እንደታተመና እንደተሰራጨ ተመልክቼ እዚያው ቁጭ ብዬ ማሰላሰሉን ቀጠልኩ፡፡

አምላክ ሆይ! በጣም ከምናምናቸው መፃህፍት አንዱ በሆነው ላይ ተንተርሶ ተጨባጭ ማስረጃዎች ከሰጠኝ በኋላ ለምንድን ነው እብሪተኛና ግትር የምሆነው? አል-ቡኻሪ በጭራሽ ሺአ አልነበሩም እንዲያውም የሱኒ ኢማምና ምሁር ነበረ፡፡

«ሰላም በርሱ ላይ ይሁን» የሚለው ክብር ለአሊ ይገባቸዋል ብዬ ልመናቸው? ነገር ግን ለዚህ ጉዳይ እጅ ከሰጠሁ ሌሎችን መቀበል ያሉብኝን ነገሮች ስለሚያስከትል እዉነት ብዬ መቀበሉን ፈራሁ፡፡

ቀደም ሲል ሁለት ጊዜ በጓደኛዬ ተሸንፌአለሁ፡፡ መጀመሪያ የአብዱልቃድር አል-ጂላኒን ቅዱስ አለመሆን ስቀበል ሁለተኛው ደግሞ ሙሳ አል-ካዚም ከአል-ጂላኒ መብለጣቸውን መቀበሌ ነበር፡፡ እንግዲህ በተጨማሪ ደግሞ «በርሱ ላይ ሰላም ይሁን» የሚለው ክብር ለአሊ ይገባቸዋል ስል ተሰማማሁ፡፡ ግና ሌላ ሽንፈት እንዲደርስብኝ አልፈለግሁም፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል እኔ ራሴ ከብዙ ምሁራን አድናቆትን አትርፌ ነበር፡፡ በግብጽ ዉስጥ በዕዉቀት የተካንኩ መሆኔን ስለገለጹልኝና የአል አዝሀር ምሁራን

ሲያወድሱኝ የልብ ልብ አግኝቼ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ ተረትቼና ተሸንፌ ተገኘ ሁ፡፡ ግን በማን? በፊትም አሁንም የተሳሳቱ ናቸው ብዬ በማስባቸውና እራሱ «ሺአ» የሚለውን ቃል እንደ ስድብ አድርጌ በምቆጥራቸው ሰዎች፡፡ ይህ እብሪትና ራስ ወዳድነት ነው፡፡ ይህ ግትርነትና ጠባብነት ነው፡፡ እባክህ ጌታዬ ግልጽነትንና ቀጥተኝነትን ለግሰኝ፡፡ ምንም እንኳ መራራ ቢሆንም ሀቁን እንድቀበል እርዳኝ፡፡ እባክህ አምላኬ ዓይኖቼን ገለጽልኝ፣ ማስተዋልንም ለግሰኝ፡፡ በአንተ ጎዳና ላይም ምራኝ፡፡ የተነገሩትን ሁሉ አዳምጠው ምርጡን ከሚከተሉት አንዱ አድርገኝ፡፡

አሏህ ሆይ! ሀቅ ሀቅ መሆኑን አሳየን፣ ሀቁን የመከተል ጥብብንም ቸረን፣ ስህተትንም ስህተትነቱን ግልጽ አድርግልን፣ ከስህተት የመራቅ ጥበብንም ለግሰን፡፡

ከጓደኛዬ ጋር ተያይዘን ወደቤት ከተመለስን በኋላ ከላይ የጠቀስኩትን እየደጋገምኩ አላህን መማፀኔን ቀጠልኩ፡፡ ጓደኛዬም ፈገግ ብሎ የሚከተለውን ጠቀሰ «እኛንም፣ አንተንም ሁሉንም ሙስሊሞች አላህ በትክክለኛው ጎዳና ላይ ይምራን፣ አላህም በመጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ብሏል፣ ***«እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን፣ አላህም በእርግጥ ከበጎ ሰሪዎች ጋር ነው»*** (ቅዱስ ቁርዓን 29:6)

ትግል (ጂሃድ) የሚለው ቃል በቁርዓን አንቀጽ ውስጥ ወደ እውነቱ ለመድረስ የሚደረግ ሰይንሳዊ ጥናት የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡ እውነትን በመሻት የሚፈልግን ሁሉ አላህ ወደ እውነቱ ይመራዋል፡፡

## በአል-ነጀፍ የተደረገ ጉብኝት

አንድ ምሽት ላይ ጓደኛዬ የአላህ ፈቃድ ከሆነ በሚቀጥለው ቀን ወደ አል-ነጀፍ እንደምንሄድ ነገረኝ፡፡ «አል-ነጀፍ ምንድን ነው?» ብዬ ጠየኩት እሱም «የትምህርት ማዕከል ነው፡፡ የአሊ ኢብን አቢ ጣሊብም መቃብር የሚገኘው በዚያው ከተማ ነው» አለኝ፡፡ የኢማም አሊ መቃብራቸው ተለይቶ የሚታወቅ በመሆኑ እጅግ ገረመኝ ምክንያቱም የኛ ሼኮች ሁሉ የአለቃችን አሊ መቃብር አይታወቅም ይላሉ፡፡ ወደ አል-ኩፋ በአውቶብስ ተጉዘን ስንደርስ እጅግ ከሚደነቁት እስላማዊ ህንፃዎች አንዱ የሆነውን የአል-ኩፋ መስጊድን ለመጎብኘት ቆምን፡፡ ጓደኛዬ ሁሉንም የታሪክ ቦታዎች አሳየኝ፡፡ ወደ ሙስሊም ኢብን አቂልና ወደ ሀኒእ ኢብን ኡርዋ ወሰደኝ፡፡ እነሱም እንዴት መስዋዕት እንደሆኑ ባጭሩ አጫወተኝ፡፡ ኢማም አሊ ሰማዕት ወደ ሆኑበት ሚህራብ ወሰደኝ፡፡ እዛም ኢማም አሊ አለቆቻችን ከሆኑት ከሁለቱ ልጆቻቸው አል-ሀሰንና አል-ሁሴይን ጋራ ይኖሩበት የነበረውን ቤት ጎበኘን፡፡ ለመጠጥነትና ለዉዱእ የሚጠቀሙበትን ዉሃ የሚቀዱበት ጉድጓድ ወዳለበት ክፍልም ወሰደኝ፡፡

ለጥቂት ደቂቃዎች ቢሆንም ዓለምን እርስት አድርጌ በመንፈሳዊ ህይወት ዉስጥ ጭልጥ አልኩ፡፡ ምንም እነኳ የአማኞች አዛዡና ቅኑን መንገድ ከተመሩት አራቱ ከሊፋዎች አንዱ ቢሆንም ኢማሙ ለዚች ዓለም ደንታ እንደሌላቸዉና የላቀ ትህትናቸዉን ቆም ብዬ አሰብኩ፡፡

የኩፋን ሰዎች የእንግዳ ተቀባይነት ምርጥ ባህልና መልካም ሥነ-ምግባራቸውን ሳላወሳ ማለፍ የለብኝም፡፡ ሰብሰብ ብለው በሚገኙ ሰዎች

አጠገብ ስናልፍ ብድግ በማለት ሰላምታ ይሰጡናል፡፡ ጓደኛዬን አብዛኛውን ሰዎች የሚያውቃቸው መስሎኝ ነበር፡፡ ካገኘናቸው ሰዎች መካከል አንደኛው የአል-ኩፋ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ነበር፡፡ ይህ ሰው ወደ ቤቱ ጋብዞን ከልጆቹ ጋር እየተጫዋወትን ደስ የሚል ምሽት አሳለፍን፡፡ ከቤተሰቦቼና ከአብሮ አደጎቼ ጋር የተቀላቀልኩ ያህል ነበር የተሰማኝ፡፡ ስለሱኒዎች ባወሩ ቁጥር «ሱኒ ወንድሞቻችን» እያሉ ነበር የሚያወጉት፡፡ አነጋገራቸውን ስለወደድኩት ምን ያህል ከልባቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ ብዬ ጥቂት ጥያቄዎችን አቀረብኩላቸው፡፡

ጉዞአችንን ከአል-ኩፋ አሥር ኪሎሜትር አካባቢ ርቃ ወደምትገኘው እስከ አል-ነጀፍ አደረግን፡፡ እዚያ ስንደርስ ከወርቅ የተሰራ ቁባ ያከበቡትን ወርቃማ ሚናራዎች ሳይ ባግዳድ ውስጥ የሚገኘው የካዚሚያህ መስጂድ ትዝ አለኝ፡፡ በሺአዎች ልማድ መሰረት ሁሌም እንደሚደረገው ለመግባት ፈቃድ ከጠየቅን በኋላ ወደ ኢማሙ ሀረም ገባን፡፡ ሀረሙ ውስጥ የሙሳ አል-ካዚም መስጂድ ውስጥ ካየኋቸው ነገሮች የበለጠ የሚያስገርሙ ነገሮችን አየሁ፡፡ መቃብሩ የያዘው የኢማም ዓሊ ሰውነት ያረፈበት ስለመሆኑ እየተጠራጠርኩ እንደተለመደው ፋቲሃ ቀራሁ፡፡ አል-ኩፋ ውስጥ ያየሁት በጣም ቀላልና አነስተኛ ቤት ቀልቤን ስቦት ነበር፡፡ ብዙ ሙስሊሞች በዓለም ላይ በብዙ ቦታዎች በረሃብ እየተሰቃዩ ኢማም ዓሊ ይህንን ሁሉ የወርቅና የብር ጌጥ የሚቀበሉ አይመስለኝም ብዬ አሰብኩ፡፡ በተለይም ደግሞ ብዙ ሰዎች በየጎዳናው ላይ ለልመና እጃቸውን እየዘረጉ ሳይ ለራሴ እንዲህ አልኩኝ፡፡

«ሺዓዎች ሆይ! ትክክል አይደላችሁም፡፡ ቢያንስ ይህን ስህተት መቀበል መቻል አለባችሁ! የአላህ መልዕክተኛ ዓሊን አንዴ የላኩት መቃብሮችን እንዲያጠፋ ነበር፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ የወርቅና የብር መቃብር ምንድን ነው?

ይህ እንዲያው ሽርክ እንኳ ካልሆነ ቢያንስ ኢስላም የማይቀበለው የተከለከለ ነገር መሆን አለበት፡፡»

ጓደኛዬ አንዲት ትንሽ ሽክላ ከሰጠኝ በኋላ ሰላት ማድረግ እፈልግ እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ቆጣ ብዬ «መቃብሮች ላይ አንሰግድም» አልኩት፡፡ «እሺ እኔ ፀሎት እስካደርግ ጠብቀኝ» አለኝ፡፡ እሱን በመጠበቅ ላይ እያለሁ መቃብሩ ላይ ተጽፎ የተሰቀለውን አነበብኩ፡፡ በመቃብሩ ዙሪያ በታጠሩት የወርቅና የብር ብረት ዘንጎች መካከል ወደ ውስጥ ስመለከትም በመቃብሩ ሥፍራ ስም ለተቋቋሙት የእርዳታ ስራዎች የሚውሉ በጎብኝዎች የተወረወሩ በጣም ብዙ ሳንቲሞችና የተለያዩ ዋጋ ያላቸው የወረቀት ገንዘቦችን ተመለክትኩ፡፡ እዚያ ያየሁት የገንዘብ መጠን ከፍተኛ ስለነበር ለወራት ሲወረወሩ የከረሙ መስሎኝ ነበር፡፡ ጓደኛዬ ግን ገንዘቡ ከማታው ሰላት በኋላ ሁልጊዜ እንደሚሰበሰብ ነገረኝ፡፡

በዚህ ባየሁት ነገር በጣም እየተገረምኩ ጓደኛዬን ተከትዬ ወጣሁ ከዛ ሁሉ ገንዘብ ጥቂቱን ቢሰጡኝ ወይም ለድሃው ህዝብ ቢያከፋፍሉት ስል ተመኘ ሁ፡፡ በጣም ከፍታ ባለው ግንብ ዙሪያውን የተከበበውን ቦታ እየዞርኩ ተመለከትኩ፡፡ ሰዎች በጀመዓ ሆነው ሲሰግዱም ተመለከትኩ፣ ሌሎች ደግሞ መድረክ ላይ ቆመው ደዕዋ የሚያደርጉ ሰዎችን ያዳምጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ ተናጋሪዎችም ጮኸው የሚያለቅሱ ይመስላሉ፡፡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ እያለቀሱ ደረታቸዉን ሲደልቁ ተመልክቼ ለምን እንዲህ እንደሚያደርጉ ጓደኛዬን ልጠይቀው ሲል አንድ አስከሬን ባጠገባችን አልፎ ጥቂት ሰዎችም ከሜዳው መሀል ላይ በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ አስከሬኑን ለማሳረፍ አንድ የአብነበረድ ጥርብ ብድግ ሲያደርጉ ተመለከትኩ፡፡ ስዎቹም የሚያለቅሱት ለሞተው ግለሰብ ነው ብዬ ገመትኩ፡፡

## ከአል-ኡለማ (ምሁራን) ጋራ የተደረገ ስብሰባ

ከመቃብሩ ሥፍራ ቀጥሎ ከሚገኝ ወለሉ ሙሉውን በምንጣፍ የተሸፈነና ሚህራቡም ዙሪያውን ውብ በሆነ የእጅ ጹሁፎች በተፃፉ የቁርዓን ጥቅሶች የተከበበ አንድ መስጊድ ጓደኛዬ ወስዶኝ ከሚህራቡ አጠገብ መጽሐፍ የያዙና የጠመጠሙ ጥቂት ወጣቶች ተቀምጠው ተመለከትኩ።

ባየሁት ነገር ተደሰትኩ። ምክንያቱም በአስራ ሶስትና በአስራ ስድስት ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሼኮችን አይቼ ስለማላውቅ ውብ መስለው እንዲታዩ ያደረጋቸው አለባበሳቸው ነበር። ጓደኛዬም ስለአለቃው «አል-ሰይድ ጠየቃቸዉና ሰላት እያስገደ መሆኑን ነገሩት፣ «አል-ሰይድ» ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም። ምናልባት ከኡለማዎቹ አንዱ ይሆናል ብዬ ገመትኩ። ወደ ኋላ ላይ ግን የአካባቢው የሺዓ ህብረተሰብ መሪ «አል-ሰይድ አል-ኩኢ» መሆኑን ተረዳሁ።

«ሰይድ» (አለቃ) የሚለው የክብር ስም ለአንድ ሺአ የሚሰጠው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰብ የትውልድ ሀረግ ለሆኑ ሰዎች ነዉ። «ሰይዱም» ተማሪም ይሁን አሊም (የተማረ ሰው) ጥቁር ጥምጣም ይጠመጥማል። ሌሎች ኡለማዎች ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚጠመጥሙት ነጭ ጥምጣም ነው። የክብር መጠሪያቸውም «ሼክ» ነው። ኡለማ ያልሆኑ አል-አሽረፍ የሚባሉም አሉ። እነሱ የሚጠመጥሙት ደግሞ አረንጓዴ ጥምጣም ነው።

ጓደኛዬ አል-ሰይድ ጋር ሄዶ እስኪመለስ ድረስ እኔ ከእነሱ ጋር መቀመጥ እችል እንደሆነ ወጣቶቹን ጠየቅኳቸው። እነሱም አስቀምጠውኝ ግማሽ ክብ ሰርተው በዙሪያዬ ቁጭ አሉ። የዋህነትና ንጽህና የሞላውን ፊታቸውን

ተመለከትኩና የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አባባል ትዝ አለኝ፡፡ ይኸውም፡- «*የሰዉ ልጅ በተፈጥሮ (እምንት) ይዞ ይወለዳል፡፡ነገር ግን ወላጆቹ የአይሁድ እምነት ተከታይ ወይም ክርስቲያን ወይም ደግሞ መጁሲ ያደርጉታል፡*» እኔ ደግሞ ጨምሬ በልቤ ወይም ሺዓ ያደርጉታል አልኩ፡፡

ከየት አገር እንደመጣሁ ጠየቁኝና ከቱኒዚያ መሆኑን መለስኩላቸው «የሃይማኖት ት/ቤቶች አሏችሁ?» ብለው ሲጠይቁኝ «ዩኒቨርስቲዎችና ትምህርት ቤቶች አሉን» አልኳቸው፡፡ የጥያቄ መዓት ከየአቅጣጫው ዘነበብኝ፡፡ ጥያቄዎቹ ሁሉ የሰሉና የበሰሉ ነበረ፡፡ የእስልምናው ዓለም የህግን ፍልስፍና እስላማዊ ህግን፣ የእስልምና መርሆንና የቁርዓን ትርጉም ከሚያስተምሩ ሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች የተሞላ ነው ብለው ለሚያስቡት ለኒህ ንፁሀን ምን ማለት ይቻላል፡፡ በሰለጠነው የእስልምና ዓለም ውስጥ የቁርዓን ትምህርት ቤቶችን በክርስቲያን መነኩሴዎች በሚተዳደሩ መዋዕለ ህፃናት እንደለወጥናቸው አያውቁም፡፡ ታዲያ እኛ እነሱን እንደኋላቀር አድርገን እንደምንወስዳቸው ልግለጽላቸው? ከልጆቹ መካከል አንዱ «በቱኒዚያ ውስጥ የትኛውን መዝሀብ (የሀይማኖት አስተምህሮ) ነው የምትከተሉት?» ሲል ጠየቀኝ «የማሊኪን መዝሀብ» ስል መለስኩለት፡፡ ጥቂቶቹ ሲስቁ ተመለከትኩ ግና ብዙም ትኩረት አልሰጠሁትም፡፡
«የጃዕፈሪን መዝሀብ አታውቀውም?» አለኝ፡፡ «ምንድን ነው ይሄ አዲስ ስም፤ እኛ የምናውቀው አራቱን መዝሀቦች ብቻ ነው፤ ከእነሱም ሌላ እስልምና ውስጥ አልተፃፈም» አልኩት፡፡

እሱም ፈገግ አለና «የጃዕፈር መዝሀብ የእስልምና አስኳል ነው፡፡ ኢማም አቡ ሃኒፋህ ከኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ ስር ሆነው መማራቸው

አታውቅም? አቡ ሃኒፋም «እነዛ ሁለቱ አመታት ባይኖሩ ኖሮ አል ኑዕማን በጠፋ ነበር» ማለታቸውንስ ታውቃለህ?» በማለት ጠየቀኝ፡፡ ከዚህ በፊት ሰምቸው የማላውቀው ስም በመስማቴ መልስ ሳልሰጠው ዝም አልኩ፡ ግና የእነሱ ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ የኢማም ማሊኪ መምህር ስላልነበሩ አላህን አመሰገንኩት፡፡ እኛ ማላኪዎች እንጂ ሃናፊዎች አይደለንም አልኩት «አራቱ መዝሀቦች ከርስ በርሳቸዉ ነዉ የተወራረሱት፣ አህመድ ኢብን ሀንበል ከአል-ሻፊዒ ወሰዱ፤ አልሻፊዒ ደግሞ ከማሊክ፣ ማሊክ ከአቡ ሃኒፋ፣ አቡ ሃኒፋ ደግሞ ከጃዕፈር አል-ሳዲቅ ወሰዱ፡፡ እነኚህ ሁሉ የአላህ መልዕክተኛ በሆኑት አያቱ መስጊድ ውስጥ የእስላማዊ ዩኒቨርስቲ የከፈቱት የመጀመሪያው ሰው ጃዕፋር ኢብን ሙሐመድ ተማሪዎች ነበሩ፡፡ በእሳቸው ስር ከአራት ሺ የማያንሱ የህግ ፍልስፍና ተማሪዎችና የሃዲስ ሊቆች ትምህርት ተከታትለዋል፡፡ የተናገረው ነገር ልክ፣ አንድ ሰው ከቁርዓን ሱራህ እንደሚቀራዉ ዓይነት ነው፡፡ በዚያ ወጣት ልጅ አውቀትም ተደነቅኩ፡፡ የታሪክ መፃህፍትን ምዕራፋቸውንና ቅጻቸዉን እየጠቀሰልኝ ሲናገርም የበለጠ ደነቀኝ፡፡ ልክ አስተማሪ ተማሪን እንደሚያስተምር ዓይነት ውይይቱን ቀጠለ፡፡ እውነት ለመናገር ከእሱ ፊት የኔ ደካማነቴ ተሰማኝ፡፡ እንዲያውም ከእነዚህ ወጣቶች ጋራ እዚህ ከመቆየት ምነው ከጓደኛዬ ጋር በሄድኩ ኖሮ አሰኘኝ፡፡ ከህግ ፍልስፍናና ከታሪክ ጋር አዛምደዉ የሚጠይቁኝን ጥያቄዎች መመለስ አልቻልኩም፡፡

«ከኢማሞች ውስጥ ማንን ነው የምትከተለው?» በማለት ጠየቀኝ «ኢማም ማሊክ» አልኩት «በአንተና በእሳቸው መካከል የአስራ አራት ምዕተ አመታት ልዩነት ያለውን ከዚህ ዓለም በሞት የተለየን ሰው እንዴት ትከተላለህ? የወቅቱን ጉዳዮችን በተመለከተ ጥያቄ ልታቀርብላቸው

ብትፈልግ ይመልሱልሃልን?» ሲለኝ ትንሽ አሰብ አደረኩና «የናንተም ጃፈር የሞቱት እኮ እንዲሁ ከአስራ አራት ምዕተ ዓመታት በፊት ነው እና ማንን ነው አንተ የምትከተለው?» ስለው እሱና ሌሎቹም ልጆች ፈጠን ብለው እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ «እኛ የምንከተለው ኢማማችን የሆኑትን ሰይድ አል-ኩኢን ነው» ከፍ ያለ ዕውቀት ያላቸው ሰይድ አል-ኩሃኢ ይሁኑ ጃፋር አል-ሳዲቅ አላወቅሁም፡፡ በተቻለኝ መጠን አርዕስቱን ለመቀየር ስል «የአል-ነጀፍ የህዝብ ብዛት ስንት ነው? አል-ነጃፍ ከባግደድ ምን ያህል ይርቃል? ከኢራቅ ሌላ ሌሎች አገሮችን ታውቃላችሁ...» የመሳሰሉትን ጥያቄዎች አቀርብላቸው ጀመር፡፡ ከእነሱ እውቀት ጋራ አለመመጣጠኔ ተሰምቶኝ ጥያቄ እጠይቃቸዋለሁ፡፡ ምንም እንኳ መሸነፌን በውስጤ ብቀበልም በግልጽ ግን አላወጣሁትም፡፡ በተለይ ከእነዚህ ወጣቶች ጋራ ከተገናኘሁ በኋላ በግብጽ ውስጥ የነበሩት የምሁርነትና የግነት ቀናት ከውስጤ ተሟጠጡ፡፡ ይህም የሚከተለውን የጠቢብ አነጋር አስታወሰኝ፡፡ በፍልስፍና ዕውቀት አለኝ የሚል ሰው እንዲህ በለው «አንድ ነገር አውቀሃል፣ ይሁንና አሁንም ገና የማታዉቃቸው ብዙ ነገሮች አሉ፡፡» የእነዚህ ወጣት ልጆች አእምሮ አል-አዝሃር ውስጥ ካገኝኋቸዉ ሼኮችና ቱኒዚያ ውስጥም ካሉት ሼኮች ይበልጣሉ ብዬ ገመትኩ፡፡

አል-ሰይድ አል-ኩኢ ከሌሎች ኡለማዎች ጋራ ሆነው እኛ ወዳለንበት ሲገቡ ልጆቹ በሙሉ ከመቀመጫቸው ብድግ ሲሉ እኔም አብሬ ተነሳሁ፡፡ ከዚያም እያንዳንዱ ልጅ ወደእሳቸው ቀርቦ እጃቸውን ሲስም እኔ ግን ባለሁበት ቆሜ ቀረሁ፡፡ ሁሉም ተቀምጦ ካበቃ በኋላ አል-ሰይድ ተቀመጡና ከሁሉም ጋራ አንድ በአንድ ሠላምታ ከተለዋወጡ በኋላ የእኔ ተራ ደርሶ እንደሌሎች ሁሉ ሠላምታ ተለዋወጥን፡፡ ጓደኛዬ ከአል-ሰይድ ጋራ በሹክሹክታ ከተነጋገረ በኋላ ወደእሳቸው እንድቀርብ በጣቱ አመልክቶኝ ስቀርብ በቀኛቸው በኩል

አስቀመጡኝ፡፡ ደግመን ሠላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ጓደኛዬ እንዲህ አለኝ፡፡ «ቱኒዚያ ውስጥ ስለሺዓ የምትሰማውን ነገሮች ለአል-ሰይድ ንገራቸው» እኔም «ወንድሜ ከዚህም ከዚያም የምንሰማቸውን ወሬዎች እንርሳቸው፣ እኔ እራሴ ሺዓ የሚለውን መስማት ስለምፈልግ አሁን ላሉኝ ጥያቄዎች በግልጽ ቀጥተኛ መልሶችን እፈልጋለሁ፡፡» አልኩት፡፡ ስለ ሺዓ ያለህን አስተያየት ለአል-ሰይድ መግለጽ አለብህ ብሎ ጓደኛዬ ድርቅ አለ፡፡ «ከክርስቲያኖችና ከአይሁዲዎች ይልቅ ሺአዎች እስልምናን ይጫናሉ እንላለን፡፡ ከክርስቲያኖችና ከአይሁዲዎች አላህን ይገዛሉ በሙሳ መልዕክት (0.ሰ) ያምናሉ፡፡ ነገር ግን የምንሰማው ሺአዎች አሊን ያመልካሉ፣ ሌላው ክፍል ደግሞ አሊን ከአላህ መልዕክተኛ ጋራ እኩል ያስቀምጣቸዋል፡፡» አልኳቸውና በማከልም እነሱ እንደሚሉት ጅብሪል የታዘዘውን ሳያከብር መልዕክቱን ለአሊ መስጠት ትቶ ለመሐመድ (ሰ.0.ወ) ሰጣቸው የሚለውን ታሪክ ነገርኳቸው፡፡

አል-ሰይድ አንገታቸውን ደፋ አድርገው ለትንሽ ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ ቀና ብለው ተመልክተውኝ እንዲህ አሉ፡፡

«ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን መሐመድም (ሰ.0.ወ) የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውና አሊ ደግሞ የአላህ አገልጋይ መሆናቸውን እናምናለን» ወደ ሌሎቹ ዞር ብለው እኔን እያመለከቱ «ተመልከቷቸው እኒህን ሰዎች እንዴት አእምሮአቸው በሀሰት ወሬ እንደተለወጠ፡፡ ከሌሎች ሰዎች ከዚህ የበለጠ ስለሰማሁ አያስገርምም፣ ከሀያሉና ታላቁ አላህ ውጭ ምንም ሃይልና ጉልበት የለም እንላለን፡፡» ከዚያም ወደ እኔ ዞር ብለው «ቁርዓንን አንብበሃል?» ሲሉ ጠየቁኝ፡፡ «አስር ኣመት ሳይሞላኝ ነው ግማሹን በቃሌ መቅራት የቻልኩት» በማለት መለስኩላቸው፡፡ እሳቸውም «ሁሉም የእስልምና ቡድኖች ክፍፍሉን ወደጎን እንተወውና በቁርዓን ላይ እንደሚስማሙ ታውቃለህ?» አሉኝ፡፡ «አዎን ይህን አውቃለሁ» አልኳቸው፡፡

ከዚያም «እጅግ ለላቀው ለሱ ምስጋና ይድረሰውና የአላህን ቃላቶች አላነበብክም?» «*መሐመድ ከበፊቱ መልዕክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልዕክተኛ እንጅ ሌላ አይደሉም*» (ቅዱስ ቁርዓን 48:29) «*መሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም የአላህ መልዕክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው*» (ቅዱስ ቁርዓን 33:40)

«እነዚህን ሁሉ የቁርዓን ጥቅሶች አውቃቸዋለሁ» አልኳቸው «አሊ ታዲያ የት አሉ? ቁርዓናችን መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልዕክተኛ ነው ካለ ታዲያ ይህ ውሸት ከየት መጣ?» በማለት አፋጠጡኝ።
ምንም መልስ ማግኘት ስላልቻልኩኝ ዝም አልኩ። «የጅብሪልን ክህደት በተመለከተ አላህ ይሰውረንና መጀመሪያ ካልከው የበለጠ አሳዛኝ ነው። ምክንያቱም አላህ ጅብሪልን ወደ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሲልካቸው ያኔ የአርባ ዓመት ሰው ነበሩ። አሊ ደግሞ ገና ስድስት ወይም ሰባት ዓመታቸው ነበር። ታዲያ እንዴት ነው ጅብሪል ከመሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጎልማሳውና ከአሊ ወጣቱ መለየት አቅቶት ስህተት የፈፀመው?» አሉና ለረጅም ጊዜ ዝም አሉ።

ትክክለኛ አስተሳሰብና ምክንያት ላይ የተመረኮዘው ይህ አነጋገር አእምሮዬ ላይ ተቀርፆ ዝም ብዬ ማሰላሰል ጀመርኩ። እኔም ለምንድን ነው ምርመራችንን በትክክለኛ አስተሳሰብና ምክንያት ላይ የማንመሰርተው ስል ራሴን ጠየኩት።

አል-ሰይድ አል-ኩኢም አክለው እንዲህ አሉ «ከሁሉም እስልምና ቡድኖች መካከል በነቢዮችና በኢማሞች ስህተት አልባነት (መዕሱም መሆን) የሚያምነው የሺአ ቡድን ብቻ መሆኑን ልገልጽልህ እወዳለሁ። ስለሆነም ኢማሞቻችን አላህ ሰላም ይስጣቸውና እንደ እኛው ሰው ሆነው ነገር ግን

ስህተት አልባ ከሆኑ እንዴት ነው ታዲያ በአላህ ዘንድ በጣም የሚወደደው፣ አላህም «ታማኙ መንፈስ» ብሎ የሚጠራው መላኢካ የሆነው ጅብሪል ነው ስህተት የፈፀመው?»

«እኒህ ሁሉ መሰረተ-ቢስ ውሸቶች ከየት መጡ?» ስል ጠየቅኳቸው:: «ሙስሊሞችን በቡድን ከፋፍለው እርስ በእርሳቸው እንዲዋጉ ከሚፈልጉ የእስልምና ጠላቶች ነዉ። ነገር ግን ሙስሊሞች ሁሉ ሺአም ይሁኑ ሱኒ ሁሉም ወንድማማቾች ናቸው:: ሁሉም ከአላህ ጋራ ሌላ አምላክ ሳይደብሉ አላህን ብቻ ያመልካሉ:: ሁሉም አንድ ቁርዓን አንድ ነቢይ እንዲሁም አንድ ቂብላህ (ሙስሊሞች በሚፀልዩበት ጊዜ ወደ መካ የሚዞሩት አቅጣጫ) ብቻ ነው ያላቸው:: በሱኒ ውስጥ የሚገኙት መዝሀቦች እርስ በርሳቸው እንደሚለያዩ ሁሉ ሺአና ሱኒዎች ፊቂሂን አስመልክተው በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ነው የሚለያዩት። ማለትም ልክ ማሊክ እስከ መጨረሻው ድረስ ከአቡ ሀኒፋ ጋር፣ አቡ ሀኒፋ ደግሞ ከአል ሻፊዒ ጋር እንዳልተስማሙ ዓይነት... ወዘተ»

እንዲህ አልኩ «እናም በእናንተ ላይ የተወሩት ነገሮች ሁሉ ተራ ውሸቶች ናቸው» «አንተ ለአላህ ምስጋና ይድረሰውና አስተዋይ ሰው ነህ፤ ነገሮችን መረዳት ትችላለህ፤ ከዚህም በተጨማሪ የሺአ አገሮችን ተመልክተሃል፤ በውስጣቸውም ተጉዘዋል፤ እናም ከእነዚህ ውሸቶች ጋራ የተዛመደ አየህ ወይስ ሰማህ?» በማለት ጠየቁኝ «አይ ጥሩ ነገሮችን እንጂ አንድም መጥፎ ነገር አላየሁም፤ አልሰማሁም:: ከወንድም ሙኒም ጋር መርከብ ላይ ለመገናኘት ዕድሉን የሰጠኝን አላህ አመሰግነዋለሁ። ኢራቅ ውስጥ የመገኘቴ ምክንያትም እሱ ነው:: ከዚህ በፊት የማላውቀውን ብዙ ነገር በእርግጥ አሁን ተምሬአለሁ» ስል ተናገርኩ::

ጓደኛዬ ሙኒምም በፈገግታ እንዲህ አለ «የኢማም አሊ መቃብር መኖሩንም ጭምር» እኔም ጠቀስኩትና «በእውነት ከእነዚህ ወጣት ልጆች እንኳ ብዙ አዲስ ነገሮችን ተምሬአለሁ። እንዲያውም ከዚህ የሃይማኖት ትምህርት ቤት እንደነሱ ገብቶ የመማር ዕድሉን ተመኝቼው ነበር» አልኩ።

አል-ሰይድም «በደስታ እዚህ ለመማር ከፈለግህ ትምህርት ቤቱ ለአንተ ክፍት ቦታ ይኖረዋል» አሉኝ ይህን አባባላቸውን ሁሉም በደስታ ተቀብለው በተለይ ጓደኛዬ ሙኒም ፊቱ በደስታ ተሞላ «እኔ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነኝ» ስል ተናገርኩ። እሳቸውም ቀጠል አድርገው «ምግብና መኖሪያህን ሌላም የምትፈልገውን ሁሉ እኛ እንችልሃለን። ግን ዋናው ቁም ነገር መማሩ ላይ ነው» አሉኝ

ለጥቂት ጊዜ አሰብኩና ለራሴ እንዲህ አልኩት «በአስተማሪነትና በትምህርት አዘጋጅነት አምስት ዓመታት ካሳለፉ በኋላ ተመልሶ ተማሪ መሆን ተቀባይነት የሚኖረው አይመስለኝም፤ በችኮላም ውሳኔ ላይ መድረስ ቀላል አይደለም።»

አል-ሰይድ አል-ኩኢን ስለ ሃሳባቸው አመስግኜ ከዑምራ ስመለስ ስለ ጉዳዩ በደንብ እንደማስብበት ነግሬአቸው ሆኖም ግን ጥቂት መጻህፍት እፈልጋለሁ አልኳቸው። አል-ሰይድም «መጽሀፎች ስጡት!» ሲሉ አዘዙ። ብዙ የተማሩ ሰዎች ብድግ ብለው ወደየመጽሀፉ መደርደሪያዎች ሄዱና ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በመመለስ እያንዳንዳቸው አንዳንድ መጽሀፍ አበረከቱልኝ። ከሰባ በላይ መጽሀፍት አገኘሁ። በተለይ ወደ ሳውዲ አረቢያ ስለምሄድ እኒህን ሁሉ መፃህፍት ይዤ መሄድ እንደማልችል ተገነዘብኩ። የሳዑዲ ባለስልጣናትም አገራቸው ውስጥ አዳዲስ አስተሳሰቦች በተለይ ከእነሱ እምነት ጋራ የማይስማማውን ስለማይፈልጉ ወደ አገራቸው የሚገባውን ማንኛውንም መጽሀፍት ሳንሱር ያደርጋሉ። ይሁን እንጂ በህይወቴ ሙሉ

አይቼው የማላውቀውን እኒህን መጽሀፍ ለመውሰድ ያገኘሁትን እድል ላጣው አልፈለግኩም፡፡ ከፊቴ ረጅም ጉዞ ይጠብቀኛል፡፡ በደማስቆ አድርገ ዮርዳኖስ ከዚያም ወደ ሳውዲ አረቢያ ስመለስ ደግሞ ጉዞው ይበልጡን ይረዝማል፡፡ በግብጽ አቋርጩ ወደ ሊቢያ ከዚም ወደ ቱኒዚያ ከመፃህፍቱ ክብደት በላይ ደግሞ አብዛኞቹ አገሮች እኒህ መፃህፍት ወደ ግዛታቸው እንዳይገቡ ከልክለዋል፡፡

አል-ሰይድም «አድራሻህን ትተህልን ሂድ፤ መፃህፍቱን እኛ እንልክልሃለን» አሉኝ፡፡ ሃሳቡን ደገፍኩና የቱኒዝ አድራሻዬን የያዘውን የግል ካርዴን ሰጠሁ፡፡ ስለ ደግነታቸውም አመስግኜ ልሄድ ስዘጋጅ ብድግ አሉና እንዲህ አሉኝ «ወደ ቅድመ አያቴ የአሏህ መልዕክተኛ መቃብር ጎራ ካልክ ሰላምታዬን አቅርብልኝ» ሁሉም ሰው እኔም ጭምር አል-ሰይድ በተናገሩት ልባችን ተነካ፡፡ አይናቸው በእንባ እየተሞላ ሲሄድ ተመለከትኩ፡፡ ከዛም ለራሴ እንዲህ አልኩ «እንዲህ አይነቱ ሰዉ የተሳሳተ ዉሸታም ነዉ ማለት ዘበት ነዉ፡፡ ሞገሱ ታላቅነቱና ጨዋነቱ በትክክል ከነቢዩ የትውልድ ሀረግ የመጣ መሆኑን ይገልፃሉ»፡፡ እሳቸዉ አይሆንም ቢሉም እጃቸውን ይገፔ ከመሳም አልተቆጠብኩም፡፡ ለመሄድ ስነሳም ሁሉም ብድግ ብለው ተሰናበቱኝ፡፡ አንዳንዶቹ ወጣት ልጆችም ተከትለውኝ በመውጣት ወደፊት ሊጽፉልኝ እንዲችሉ አድራሻዬን ጠየቁኝና ሰጠኋቸው፡፡

አቡ ሽባር ከሚባል ከሙኒም ጓደኛ በተደረገልን ግብዣ መሠረት ወደ አል-ኩፋ ተመልሰን ሄድን፡፡ እዚያም በርከት ካሉ ወጣት ምሁራን ጋራ ስንጨዋወት ሌሊቱን ሙሉ አሳለፍን፡፡ ከነዚህ ወጣቶች መካከል የአል-ሰይድ ሙሐመድ አል-ሰድር ጥቂት ተማሪዎች ነበሩ፡፡ እነሱም ከመምህራቸው ጋር እንድንገናኝ ሃሳብ አቅርበውልኝ በሚቀጥለው ቀን

ከእሳቸው ጋራ የቃለ መጠይቅ ፕሮግራም እንደሚይዙልን ቃል ገቡ፡፡ ጓደኛ ዬ ሙኒም ሀሳቡን ቢወደውም ባግዳድ ውስጥ ቀደም ብሎ የተያዘ ቀጠሮ ስላለው ሊገኝ ባለመቻሉ ይቅርታ ጠየቀ፡፡ ሙኒም ከባግዳድ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ እኔ ከአቡ ሸባር ቤት ለሦስት ወይም ለአራት ቀናት ኑሬ ልጠብቀው ተስማማን፡፡

ሙኒም ከሱብሂ ሰላት በኋላ ተነስቶ ሲሄድ እኛ ተኛን፡፡ ከእነዚህ ተማሪዎች ብዙ ነገሮችን ቀሰምኩ፡፡ በሚያጠኗቸዉ ኃይማኖታዊ ርዕሰ ጉዳዮች ብዛት ተገረምኩ፡፡ ፊቂህ፣ ሸሪዓ፣ ተዉሂድና የመሳሰሉትን ኢስላማዊ ጥናቶች በተጨማሪም ኢኮኖሚክስ፣ ሶሲዮሎጂ፣ ፖለቲካ፣ ታሪክ፣ ቋንቋዎች፣ አስትሮኖሚና ሌሎችንም ይማራሉ፡፡

## ከአል-ሰይድ መሀመድ ባቂር አል-ሰድር ጋራ መገናኘት

ወደ አል-ሰይድ መሀመድ ባቂር አል-ሰድር ቤት ከአቡ ሸባር ጋራ ሄድን፡፡ በመንገዳችን ላይም አክብሮት እያሳየኝ ስለሺህ ስመጥር ዓሊምና ስለተቅሊድ (የሙጅተሂድን ህጋዊ ውሳኔ መቀበል) እና ስለመሳሰሉት አጫወተኝ፡፡ ደርሰን ወደቤቱ ዘልቀን ስንገባ አል-ሰይድ አል-ሰድር በርከት ባሉ በጠመጠሙ ወጣት ተማሪዎች ተከበው አገኘናቸው፡፡ አል-ሰይድ ብድግ ብለው ሠላምታ ሰጡን፡፡ ከዚያም ከእሳቸው ጋራ ተዋውኩና ሞቅ አድርገው ተቀበሉን፡፡ ከአጠገባቸው አስቀመጡኝ፡፡ ከዚያም በኋላ ስለቱኒዚያ፣ አልጄሪያ፣ አል-ከድር፣ ሁሴይንና አል-ጣሂር ኢብን አል-ሹርን ስለመሳሰሉ ስመጥር ኡለማዎች ይጠይቁኝ ጀመር፡፡ ንግግራቸው ጣመኝ፡፡ ምንም እንኳ

ተማሪዎቻቸው የሚሰጡአቸውን አክብሮትና ያሉበትንም ከፍተኛ ስልጣን ብመለከትም ምንም አልከበዱኝም፡፡ እንዲያውም ከዚህ በፊት እንደማውቃቸው አድርጌ ነው የተሰማኝ፡፡

ከተማሪዎቹ የሚሰነዘሩትን ጥያቄዎችና ከእሳቸውም የሚሰጡትን መልሶች በጥሞና በማዳመጤ ብዙ ነገሮችን ለማግኘት ቻልኩ፡፡ ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች በቀጥታና በግልጽ መመለስ የሚችልን የህያው ኡለማ ውሳኔ የመቀበሉን ሃሳብ አደነቅሁት፡፡ ሺአዎች አንድ አምላክን ብቻ የሚያመልኩና በነቢያችን መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት የሚያምኑ መሆናቸውን አምኜ ተቀበልኩ፡፡ በመጀመሪያ ጊዜ የማየውን ሁሉ ሲያስመስሉ ነው ብዬ ብዙ ተጠራጠርኩ ወይም ምናልባት እነሱ ተቂያ (የማያምኑትን ማሳየት) ብለው የሚጠሩት ይሆናል ብዬ ገመትኩ፡፡ ግን እነዚህ ጥርጣሬዎቼ ወዲያውኑ ጠፉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ በመቶዎች የሚቆጠሩ ህዝቦች የማስመሰል ድርጊቶቻቸውን እንዲህ ማቀናጀት መቻላቸው አሳማኝ ባለመሆኑና ማስመሰልስ ለምን ያስፈልጋቸዋል ብዬም በማሰቤ ጭምር ነበር፡፡ ከዚህም በኋላ ደግሞ እኔስ ማን ነኝና ነው ተቂያን እስከመጠቀም ደረጃ የሚደርሱት፡፡ መፃህፍቶቻቸው ሁሉ ከምዕተ ዓመታት በፊትም የተፃፉት ሆነ አዲሶቹም ጭምር የአላህን አንድነት የሚመሰክሩና መልዕክተኛው መሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የሚያወድሱ ናቸው፡፡ (በኢራቅ ውስጥም ሆነ ውጭ ስመጥር የሃይማኖት ሊቅ በሆኑት በአል-ሰይድ መሐመድ ባቂር አል-ሰድር ቤት ውስጥ ነበርኩ፡፡ የመሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስም በተነሳ ቁጥር እዚያ የሚገኘው ሰው ሁሉ በአንድ ድምጽ «የአላህ ሰላትና ሰላም በመሐመድና በቤተሰባቸው ላይ ይውረድ» ብለው በሚያስተጋቡበት ቤት፡፡

የሰላት ሰዓትም በደረሰ ጊዜ ከቤታቸው አጠገብ ወደሚገኘው መስጂድ ሄድን፡፡ እዚያም አል-ሰይድ መሐመድ አል-ሰድር የቀትርና ድህረ ቀትር ሰላት መሩ፡፡ እኔም ከነቢዩ የቅርብ ጓደኞች መካከል እንደኖርኩ መስሎ ተሰማኝ፡፡ ምክንያቱም ከመሀላቸው አንድ የሚያባባ ድምጽ የነበረው ሰው ጥልቅና እውነተኛ የተማጽኖ ፀሎት ያደርግ ነበር፡፡ እሱም ፀሎቱ እንዳበቃ «አላህ በመሐመድና በቤተሰቦቻቸው ላይ የአክብሮት እዝነትን ያውርድ» በማለት ሁላችንም በአንድ ድምጽ ጮህን፡፡ ፀሎቱ በመሠረቱ ታላቁን ንጉሥ አላህን ለማመስገንና ለማወደስ ቀጥሎም የመሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ከርክሰት ሁሉ የጠሩትን ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች ለማወደስ ነዉ፡፡

ከሰላቱ በኋላ አል-ሰድር በሚህራቡ ውስጥ ተቀመጡ፡፡ ሰዎችም ወደ እሳቸው እየቀረቡ ሠላምታ ሰጧቸው፡፡ አንዳንዶቹ የግል ጥያቄዎች ሲያቀርቡላቸው ሌሎች ደግሞ አጠቃላይ የሆኑ ጥያቄዎችን አቀረቡላቸው፡፡ ለሁሉም እንደየአመጣጡ መልስ ሰጡ፡፡ አንድ ሰው ለጥያቄው መልስ ሲያገኝ የአል-ሰይድን እጅ ይስምና ከዛ ቦታ ወጥቶ ይሄዳል፡፡ የእነሱን ኑሮ የሚኖርና ለችግሮቻቸውም መፍትሄ የሚሰጥ ሞገስ ያለው የተማረ ኢማም በማግኘታቸው ምንኛ የታደሉ ሰዎች ናቸው፡፡

አል-ሰይድ ያደረጉልኝ ከፍተኛ እንክብካቤና ደግነት ቤተሰቤንና ጎሳዬን እስከማስረሳት ደረጃ አደረሰኝ፡፡ ከእሳቸው ጋራ ለአንድ ወር ብኖር ለምግባራቸው፣ ለጨዋነታቸውና ለደግነታቸው ወደ ሺአነት እንደምለወጥ ተሰማኝ፡፡ እሳቸው ጋራ ለአራት ቀናት አብሬአቸው ለመኘታ ካልሆነ በስተቀር ለአንድ አፍታም ተለይቼያቸው አላውቅም፡፡ እሳቸውን ለማግኘት ሰዎች ከመላው ዓለም ይመጡ ነበር፡፡ ከሂጃዝ የሳውዲ ሺአዎች፣ ሌሎች ከባህሬን፣ ኳታር ከተባበሩት የአረብ ኢሚሬቶች፣ ከሊባኖስ፣ ከሶሪያ፣

ከኢራን፣ ከአፍጋኒስታን፣ ከቱርኮና ከአፍሪካም ይመጡ ነበር። አል-ሰይድም እያዳንዳቸውን አነጋግረው ለችግሮቻቸው መፍትሔ ይሰጡዋቸዋል። ሰዎቹም ተደስተውና ተፅናንተው ይመለሳሉ። እዚህ ላይ እኔ ከጎናቸው በነበርኩበት ጊዜ ለአል-ሰይድ ቀርቦላቸው የነበረን አንድ ጉዳይ ለማንሳት እፈልጋለሁ። ለዚህም የሰጡት መፍትሔ በእጅጉ አስደነቀኝ። ይህንንም የምገልፀው ሙስሊሞች የአላህን ህግ በመተዋቸው ያጡትን ሁሉ እዲገነዘቡት የሚያስችል አበይት ታሪካዊነት ስላለው ነው።

በአነጋገራቸው ምናልባት የኢራቅ ሰዎች ናቸው ብዬ የገመትኳቸው አራት ሰዎች ከአል-ሰይድ መሐመድ ባቂር አል-ሰድር ጋራ ለመገናኘት ይመጣሉ። አንደኛው ሰው ከጥቂት ዓመታት በፊት ከሞቱት አባቱ የወረሰውን አንድ ቤት እዚሁ ከሱ ጋር ላለ አንድ ሰው ሽጦታል። ሽያጩ ከተከናወነ ከአንድ ዓመት በኋላ ሁለት የሻጩ ወንድሞች ብቅ ብለው የሟቹ ህጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። አራቱም ሰዎች ከአል-ሰይድ ፊት ተቀምጠው እያንዳንዳቸው ወረቀቶችንና የንብረት ማስረጃዎችን አቀረቡ። አል-ሰይድ የቀረቡላቸውን ሁሉ አንብበው ከሰዎቹም ጋራ ለጥቂት ደቂቃዎች ከተነጋገሩ በኋላ ፍትሃዊ የሆነ ውሳኔ አስተላለፉ። ለገዥው የቤቱን ሙሉ የባለቤትነት መብት ሰጡት። ሻጩን ደግሞ ከሽያጩ ያገኘውን ገንዘብ ለሁለቱ ወንድሞቹ ድርሻቸውን እንዲሰጣቸው በየኑ። ከዚህ በኋላ ሰዎቹ ብድግ ብለው አል-ሰይድን እጅ ከሳሙ በኋላ እርስ በርሳቸው ተቃቀፉ። በተፈፀመው ድርጊት እጅግ በመገረም አቡ ሽባርን «ጉዳዩ እልባት አገኘ ማለት ነው?» በማለት ጠየኩት «አዎን አላህ ምስጋና ይግባውና እያንዳንዱ ድርሻውን አግኝቷል።» ሲል መለሰልኝ። እንዲህ ዓይነት ጉዳይ በጣም በአጭር ጊዜ ማለትም በጥቂት ደቂቃዎች መፍትሔ አገኘ። በኛ ሀገር ቢሆን ኖሮ እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ በአስር ዓመትም እልባት አያገኝም ነበር። የዚህ ዓይነት ተመሳሳይ ጉዳይ አንዳንድ ተከሳሾችም ይሞቱና ክርክሩን ልጆቻቸው ይቀጥሉታል። አብዛኛውን ጊዜ ለክርክሩ የሚወጣው ገንዘብ ከቤቱ ዋጋ ይበልጣል።

ጉዳዩም ከተራ ፍርድ ቤት አልፎ ወደ ይግባኝ ሰሚ ከዚያም ወደ አጣሪ ፍርድ ቤት ይደርሳል፡፡ በሰዎችና በጎሳዎች መካከልም ጥላቻ ከተፈጠረ በኋላ የትኛውም ወገን ሳይረካ ጉዳዩ ያልቃል፡፡

«ከዚህ የከፋ ባይሆንም እኛም ተመሳሳይ አካሄድ አለን» በማለት አቡ ሸባር አስተያየቱን ሰጠኝ፡፡ እኔም «እንዴት?» ስል ጠየኩት «ሰዎች ጉዳያቸውን ወደ መንግስት ፍርድ ቤት ከወሰዱ አሁን አንተ የገለጽካቸዉ ዓይነት ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፡፡ የሃይማኖትን የበላይነት ተከትለው ራሳቸውን ለእስላማዊ ህጎች ተገዥ ካደረጉ ልክ አሁን እንዳየኸው ጉዳያቸውን እሳቸው ጋር አቅርበው ችግሩ በጥቂት ደቂቃዎች ይፈታል፡፡ ለሚገባቸው ሰዎች ከአላህ ህግ የተሻለ ምን ሊኖር ይችላል? አል-ሰይድ አል-ሰድር እነዚህን ሰዎች ቤሳ አላስከፈሉአቸዉም፡፡ ወደ መንግስት ችሎት ሄደው ቢሆን ግን ከፍተኛ ወጭ ባወጡ ነበር»፡፡

«ለአላህ ምስጋና ይግባው! ያየሁትን አሁንም ማመን አልቻልኩም፡፡ እንዲያው በዓይኖቼ ባላየው ኖሮ ፍፁም አላምንም ነበር» አልኩት «ከሌሎች ደምን (ነፍስን) ከሚመለከቱ ጉዳዮች ጋራ ሲወዳደር ይህ ትንሽ ጉዳይ ነው፣ እና ለማመን ይቸግረኛል አትበል ወንድሜ፡፡ ያም ሆኖ ግን የሃይማኖት ባለስልጣኖች ትንሽ ጉዳይ ነው ብለው አይተውትም፤ ይመለከቱታል ውሳኔም ለመስጠት ጥቂት ደቂቃዎች ይወስድባቸዋል» አለኝ፡፡ እኔም በመገረም «ሰለዚህ በኢራቅ ዉስጥ ሁለት ዓይነት መንግስት አለ ማለት ነዉ? ኢስላማዊ መንግስትና ሌላዉ መንግስት» ብዬ ጠየቅኩ፡፡ እሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ «አይደለም! ያለን መንግስት አንድ ብቻ ነዉ ነገር ግን የኃይማኖት አባቶችን የሚከተሉ የሺዓ መዝሀብ ሙሲሊሞች ከመንግስት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸዉም ምክንያቱም ኢስላማዊ

መንግስት ሰላልሆነ ነዉ። ዜጎች ስለሆኑ በቀረጥና በመሳሰሉት ምክንያቶች ብቻ በመንግስት ስር ይውላሉ። ለምሳሌ አንድ ሀቀኛ ሙስሊም እስልምናን በደንብ ከማይከተል ሙስሊም ጋር ክርክር ቢኖርበት ጉዳዩ ወደ መንግስት ችሎት መቅረብ ይኖርበታል። ምክንያቱም ያኛው ሙስሊም የሃይማኖት ባለስልጣናት የሚሰጡትን ውሳኔ አይቀበልም። ሆኖም ግን በሁለት ጽኑ ሙስሊሞች መካከል ክስ ቢነሳ ምንም ችግር አይፈጠርም። ምክንያቱም ሁለቱም ወገኖች የሃይማኖት ባለስልጣኖች የሚወስኑትን ማንኛውንም ውሳኔ ይቀበላሉ። ስለሆነም በሃይማኖት ባለስልጣኖች የሚታዩ ጉዳዮች ሁሉ እለቱኑ ውሳኔ ሲያገኙ ወደ መንግስት የተመሩት ግን ለወራትና ለዓመታት ሲጓተቱ ይከርማሉ።»

ይህ አጋጣሚ ሃያል የሆነው ጌታ ምስጋና ይድረሰውና በአላህ ህግ እንድንረካ አደረገኝ። ብሎም በታላቁ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የአላህን ቃላት በሚገባ እንድረዳቸው ጠቀመኝ።

«...***አላህም ባወረደው ነገር ያልፈረደ ሰው እነዚያ ከሐዲዎቹ እነርሱ ናቸው***» (ቁርአን 5፡44) «...***አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው እነዚያ በደለኞቹ እነርሱ ናቸው***» (ቁርአን 5፡45) «...***አላህም ባወረደው ነገር የማይፈርድ ሰው እነዚያ አመጸኞች እነርሱ ናቸው***» (ቁርአን 5፡47)

ያ አጋጣሚ፣ የአላህ ፍትሐዊ ህጎችን ኢ-ፍትሐዊ በሆኑት ሰው ሰራሽ ህጎች በለወጡዋቸው ሰዎች ላይ የቁጣና የጥላቻ ስሜት አነሳሳብኝ። እኒህ ሰዎች መረን በመልቀቅ ብልግናና አሸሙር በተሞላበት አነጋገር የእስልምና ህግ ገደብ ስለሚያበጅ የሌባን እጅ ስለሚቆርጥ፣ ዝሙተኞችን በድንጋይ ስለሚያስወግርና ነፍስ ገዳይን በሞት ስለሚቀጣ እኒህን መለኮታዊ ህጎች አረመኔያዊና ኢ-ሰብአዊ ናቸው በማለት ይኮንኗቸዋል። ታዲያ ለእኛና ለባህላችን እንግዳ የሆኑት አዳዲስ ንድፈ ሀሳቦች ከየት መጡ? እነሱ ሌቦች

ከሃዲዎች፣ ዝሙተኞች፣ ወንጀለኞችና ነፍሰ ገዳዮች ስለሆኑ፣ የአላህ ህጎች ሲተገበሩ የእነሱ መጥፋት አይቀሬ ነው። አዳዲሶቹ ንድፈ ሃሳቦች የመጡት ያለጥርጥር ከምዕራቡ ዓለምና ከእስልምና ጠላቶች ነው።

በእነዚህ ቀናት ውስጥ ከአል-ሰይድ አል-ሰድር ጋር በርከት ያሉ ውይይቶችን አደረግሁ። ስለእምነታቸው ካስረዱኝና ስለነቢዩ የቅርብ ጓደኞቹ ስላገኘሁት ዕውቀትና ስላልተስማማሁባቸው ሌሎች ነጥቦችም ሁሉ አል-ሰይድን ጠየቅኳቸው። ኢማም አሊን በተመለከተ «የአላህ ወሊይ» (የአላህ ጓደኛ) ናቸው ብለው በአዛን (የሰላት ጥሪ) ውስጥ ለምን እንደሚመሰክሩላቸው ጠየቅኳቸዉ። ይህን ጥያቄዬን በሚከተለው መንገድ መለሱልኝ።

«የአማኞች አዛዥ የሆኑት አሊ፣ የአላህ ሰላትና ሰላም በሳቸው ላይ ይውረድና፣ ከነቢያችን በኋላ አላህ መርጦዋቸው ስለመልዕክቱ የሃላፊነትን ክብር ከሰጣቸው የአላህ አገልጋዮች አንዱ ነበሩ። እያንዳንዱ ነቢይ ወኪል እንዳለው ሁሉ እኒህ አገልጋዮችም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወኪሎች ነበሩ በመሆኑም አሊ ኢብን አቢ ጣሊብ የመሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወኪል ናቸው። ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቅርብ ሰሀባዎች የበለጠ የምንወዳቸው አላህና ነቢዩም እንዲሁ ስለሚወዷቸው ነው። ለዚሁም በርከት ያሉ ማረጋገጫዎች አሉን። አንዳንዶቹ ማረጋገጫዎች ከትክክለኛ የአስተሳሰብ ዘዴ (ሎጂክ) የመጡ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በቁርዓንና በአል-ሱናህ (የነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ውስጥ) ይገኛሉ። እኒህ ማረጋገጫዎች ደግሞ ሊጠረጠሩ አይችሉም፡ ፡ ምክንያቱም በእኛ ምሁራን (በርዕሱ ላይ ብዙ መፃህፍትን በፃፉት) እና በሱኒ መዝሐቦች በደንብ ተብላልተው ትክክለኛነታቸው ተረጋግጧል። የኡመያዎች አገዛዝ ይህን ሃቅ ለመሸፈን ብዙ ጥሮ አሊና ልጆቻቸው ላይ ጦርነት በመክፈት ገደላቸው። ይህ አገዛዝ ሰዎች አሊን እንዲያወግዟቸው

ትዕዛዝ አስተላልፎ አንዳንዱም በሃይል አስገድዷል፡፡ በመሆኑም »የአላህ ሰላትና ሰላም በሁሉም ላይ ያውርድ« የሚለው በተከታዮቻቸው የተሰጣቸው ክብር የአላህ ወሊይ መሆናቸውን ያረጋግጥ ጀመር፡፡ ክብር የተሞላበት ውደሳ ለአላህ መልዕክተኛውና ለመላው አማኞች በመሆኑ አንድም ሙስሊም የጨካኝ ገዥዎችን ትዕዛዝ ተቀብሎ የአላህን ወዳጅ አያወግዝም፡፡ ይህም በትውልዶች ውስጥ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ከፍቶ የአሊን አላማ ትክክለኛነትና የጠላቶችን የተሳሳተ ድርጊት እንዲገነዘቡት አደረገ፡፡ ስለሆነም የተማሩ ሰዎች በፀሎት ጥሪያቸው(አዛን) ውስጥ አሊ የአላህ ወዳጅ መሆናቸውን መመስከሩ ተገቢ ስለሆነ ቀጠሉበት፡፡ «በኃይማኖታዊ ነክ ጉዳዮችም ሆነ በዕለት ተዕለት የኑሮ እንቅስቃሴ ዉስጥ የሚበረታቱ (የሚደገፉ) (ሱናዎች) አሉ፡፡ እነዚህን ጉዳዮች መፈጸም ሽልማት ቢኖረዉም ሳይሰራ ሲቀር ግን ቅጣትና ወቀሳ የሌላቸዉ ናቸዉ፡፡» ለምሳሌ፡- ሙስሊም ሁሉ፣ ከአል-ሸሃዳህ በኋላ (ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ የሱም መልዕክተኛ መሐመድ ነው) እኛ ጀነት እንዲሁም ጀሃነም ሀቅ (እውን) መሆናቸውንና አላህ የሞተን ከመቃብር እንደሚያስነሳ እመሰክራለሁ ማለቱ ተገቢ ነው፡፡

«የእኛ ኡለማዎች ለኸሊፋነቱ ቅድሚያ የሚሰጠዉ ለመሪያችን ለአቡበከር አል-ሲዲቅ፣ ቀጥሎም ለአለቃችን ኡመር አል-ፋሩቅ፣ ቀጥሎም ለአለቃችን ኡስማን ከዚያም ለአለቃችን አሊ (አላህ ሁሉም ሰላትና ሰላም ያውርድና) እንደሆነ አስተምረውናል» አልኳቸው፡፡ አል-ሰይድም ለጥቂት ጊዜ ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ እንዲህ አሉ «የፈለጉትን ይበሉ፡፡ ግን ህጋዊ መሠረትን አስይዘው ለማረጋገጥ አይቻላቸውም፡፡ ከዚህም ሌላ ከሰው ሁሉ ምርጥ የሆኑት አቡበከር ናቸው፡፡ ከዚያም ኡስማን ናቸው ይሉና አሊን ግን ተራ ሰው በማድረግ ሳይጠቅሷቸው ያልፋሉ፡፡ ሆኖም ግን በቅርብ ጊዜ የነበሩ

የታሪክ ሰዎች በትክክለኛ መንገድ የተመሩ ኻሊፋዎችን ለመጥቀስ ሲሉ እሳቸውንም ያገሏቸዋል፡፡ እናም እነሱ የሚናገሩት ራሱ ከመፃህፍቶቻቸው ጋር ይቃረናል»

ከዚህ ቀጥዬ ደግሞ «አል-ቱርባህ አል-ሁሴኒያ» ብለው የሚጠሩትን በሚሰግዱበት ጊዜ ግንባራችን ሥር የሚያስቀምጡት ትንሽ ሸክላ ጠየቅኳቸው፡፡ «ሃያል ለሆነው ለሱ ምስጋና ይግባውና ስግደት ለአላህ ብቻ ነው፣ አንዳንድ ሰዎች ሺአዎች ለአቧራው ነው የሚሰግዱት እንደሚሉት ሳይሆን እኛ የምንሰግደው በአቧራው ላይ ነው፡፡ እኛ የምንሰግደው በጣም አመቺ ከሆነ መስገጃ መሬትና ከመሬትም በሚገኝ ከማይበላ ነገር መሆኑን፣ ሆኖም ግን ከነዚህ ውጭ በሆኑ ነገሮች ላይ መስገድ ስህተት እንደሆነ በእኛ ሰዎችና በሱኒዎችም ጭምር በሚገባ የታወቀ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በአቧራ ላይ ቁጭ ብለው ይሰግዱበት የነበረ አንድ ከገለባ ጋር ተደባልቆ የተሰራ ሸክላ ነበራቸው፡፡ የቅርብ ጓደኞቻቸውንም አላህ በእነሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያውርድ መሬትና ድንጋይ ላይ እንጂ በሽሚዞቻቸው ጠርዞች ላይ እንዳይሰግዱ አስተምረዋቸዋል፡፡ እኛም እነዚህን ድርጊቶች አስፈላጊና ዋነኛም አድርገን እቆጥራቸዋለን፡፡

ኢማም ዘይን አል-ኢቢዲን አሊ ኢብን አል-ሁሴይን (ዐ.ሰ) ከአባቶቻቸው ከአቡ አብዱላህ መቃብር አጠገብ ቱርባህ (ትንሽ ሸክላ) ወሰዱ፡፡ ምክንያቱም የዋናው ሰማዕት ደም ተረጭቶበት ስለነበር እዚያ ያለው አፈር የተባረከና ንጹህ ሆኗል፡፡ በዚህም ምክንያት የሳቸው ተከታዮች ይህን ልምድ እስከዛሬ ድረስ ቀጥለውበታል፡፡

እኛ ስግደት፤ በቱርባህ ላይ ካልሆነ አይፈቀድም አላልንም፡፡ የምንላቸው «ስግደት በተባረከ ቱርባህ ወይም ድንጋይ ላይ ቢሆን ትክክል ይሆናል ነው፡፡

ከዘንባባ ቅጠሎች ወይም ተመሳሳይ ከሆነ ነገር በሚሰራ ምንጣፍ ላይ መስገድም ትክክል ነው»

አለቃችን አል-ሁሴይንን (ዐ.ሰ) በተመለከተ እንዲህ ስል ጠየቅኳቸው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል «ጉንጮቹን የሚጠፈጥፍና ልብሶቹን የሚቀዳድና የአል-ጃሂሊያ ጥሪ የሚከተል የእኛ ሰው (ተከታይ) አይደለም»፡፡ ታዲያ ለምንድን ነው ሺዓዎች እያለቀሱ ጉንጮቻቸውን እና ሌሎች የሰውነት ክፍሎቻቸውን ደም እስኪፈሳቸው ድረስ የሚደበድቡት? ይህም ነቢዩ እንዳሉት በእስልምና የተከለከለ ነው፡፡
አል-ሰይድም እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ «የተባለው ትክክል ነው ለዚህም ምንም ጥርጣሬ የለም፡፡ ይህ ግን በአቡ አብዱላህ የለቅሶ ስነ-ስርዓት ላይ አይሰራም፡፡ ምክንያቱም የአል-ሁሴይንን ደም ለመበቀል ጥሪ የሚያደርግና የሳቸውን መንገድ የሚከተል የእሱ ጥሪ የጃሂሊያ አይደለም፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ ሺአዎች ሰዎች ናቸው፡፡ ከእነሱም መካከል የተማሩም ያልተማሩም ታገኛለህ ሰዎች ናቸውና የሚሰማቸው ስሜት አላቸው፡፡ አቡ አብዱላህ ስማዕት የሆኑበትን ቀን በሚያከብሩበት ወቅት በስሜት ቢዋጡ፣ ግን ደግሞ በሳቸው ላይ የደረሰው ትዝ ይበልህ እንዴት ቤተሰቦቻው ከውርደት ወደ እስር በመጨረሻም ለመገደል እንደበቁ፣ እናም ሺአዎች በስሜት ተውጠው እንዲያ ቢያደርጉ ለጥሩ አላማዎቻቸው ይሸለማሉ፡፡ ምክንያቱም እኒህ አላማዎቻቸው ሃያል ለሆነው ለሱ ምስጋና ይግባውና ለአላህ ፍቅር ሲሉ ያሳዩዋቸው ናቸው፡፡ አላህም ደግሞ ሰዎችን ዓላማዎቻቸውን ተረድቶ ይሸልማቸዋል፡፡

ከጀማል አብዱል ናስር ሞት በኋላ ስለተከሰቱት እራስን በራስ የማጥፋት ድርጊቶች ከግብጽ መንግስት የተሰጡትን ይፋ ዘገባዎች ባለፈው ሳምንት አንብቤያለሁ፡፡ እራሳቸውን ከህንፃዎች በመወርወርና ከሚከንፉ ባቡሮች ስር

በመግባት ራሳቸውን ያጠፉ የስምንት ሰዎችና ሌሎችም ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ዜና ተነግሮ ነበር፡፡

ይህ እንዲህ በትክክል የሚያስቡ ሰዎች በስሜት ተውጠው ምን ዓይነት እርምጃ እንደሚወስዱ የሚያሳይ ምሳሌ ነው፡፡ ተፈጥሮአዊ በሆነ ምክንያት ለሞተው ጀማል አብዱል ናስር ሲሉ ራሳቸውን ያጠፉት ሙስሊሞች ናቸው፡፡ እኛ ታዲያ እኒህን ሱኒዎች ብናወግዛቸውና ስህተት ሰርተዋል ብለን ብንደመድም ትክክል አንሆንም፡፡
በሌላ በኩል ደግሞ ሱኒዎች ሺአ ወንድሞቻቸው ለዋና ሰማዕታቸው በማልቀሳቸው ስህተት ሰርተዋል ቢሉ ትክክል አይሆኑም፡፡ እኒህ ሰዎች በአል-ሁሴይን አሳዛኝ ፍፃሜ ውስጥ ኖረዋል እስከዛሬዋ ዕለትም ይኖራሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) በልጃቸው አል-ሁሴይን ሞት አልቅሰዋል ጂብሪልም አልቅሷል፡፡

ሌላ ጥያቄ አቀረቡኩላቸው «በእስልምና የተከለከለ ሆኖ ሳለ ለምንድን ነው ሺአዎች የቅዱሳኖቻቸውን መቃብር በወርቅና በብር የሚያስጌጡት?» አል-ሰይድ አል-ሰድር እንዲህ ሲሉ መለሱልኝ «ሺዓዎች ብቻ አይደሉም እንዲህ የሚያደርጉት የተከለከለም ነገር አይደለም፡፡ በኢራቅ፣ በግብጽ፣ በቱርክ ወይም በሌላው የእስላም ዓለም ውስጥ የሚገኙትን የሱኒ ወንድሞቻችንን መስጂዶች ተመልከት፤ ሁሉም በወርቅና በብር አጊጠዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአላህ ቤት በአል-መዲናህ፣ አል-ሙነዋራህ እናም በካባ በተቀደሰው መካ የሚገኝ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ በሚያወጣ በወርቅ በተለበጠ ጨርቅ ይሸፍናል፡፡ እናም ይህ ዓይነቱ ድርጊት በሺአ ብቻ የተወሰነ አይደለም፡፡»

«የሳውዲ ኡለማዎች፣ መቃብሮችን እየነካኩና ቅዱሳንን የማክበር እዝነትን አውርዱልን እያሉ መማፀንን ከአንድ አምላክ ሌላ ማምለክ ነው ይላሉ፣ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?» ስል ጠየቅኳቸው፡፡ የእሳቸውም መልስ እንደሚከተለው ነበር፡፡

«መቃብሮችን መነካካትና የሞቱትንም መጣራት ጉዳት ያደርሳሉ ወይም ጥቅም ይሰጣሉ በሚል ግንዛቤ ከሆነ በትክክል ከአንድ አምላክ ሌላ ማምለክ ይሆናል፡፡ ይህ ጥርጣሬ የለውም፤ ሙስሊሞች በአንድ አምላክ አማኞች ናቸው፤ ጉዳትን የሚያደርሰው ወይም ጥቅምን የሚሰጥ አንድ አላህ ብቻ መሆኑን ያውቃሉ፤ ነገር ግን ቅዱሳንና ኢማሞችን (ዐ.ሰ) መጣራት ለአላህ እንደ አማላጅ ይሆናል በሚል ግንዛቤ ከሆነ ሽርክ አይሆንም፡፡ ሁሉም ሙስሊሞች ሱኒዎችም ሺዓዎችም መልዕክተኛው ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በዚህ ነጥብ ላይ ሲስማሙ፣ ወሃቢዮቹ የሳውዲ ኡለማዎች ግን በአዲሱ የእምነት አንቀፃቸው ሙስሊሞችን ሁሉ ይቃረናሉ፡፡ በሙስሊሞች መካከል ከፍተኛ ረብሻዎችን ፈጥረዋል፡፡ ሃይማኖቱንም አጉድፈዋል ሲሉ ከሰዋቸዋል «አቤቱ የአላህ መልዕክተኛ ሰላም ለእርስዎ ይሁን» በማለታቸው ብቻ መካ ውስጥ ወደሚገኘው የአላህ ቤት ለፀሎት የሄዱትን የአዛውንት ምዕመናን ደም በድብደባ አፍስሰዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛን የተባረከ መቃብር አንድም ሰው እንዲነካው አይፈቅዱም፡፡ ከእኛ የተማሩ ሰዎች ጋራ በርካታ ክርክሮችን አካሂደዋል፡፡ ሆኖም ግን በግትርነታቸውና በእብሪተኛነታቸው ላይ ፀንተዋል፡፡

አል-ሰይድ ሸረፈዲን የተባሉ ስመጥር የሺአ ምሁር በአብዱል አዚዝ ኢብን ሰዑድ ጊዜ ወደ አላህ ቤት ለሐጅ ሄደው ነበር፡፡ በአገሩ ወግ መሰረትም የኢድ አል-አድሃን በዓል ከንጉሱ ጋራ ለማክበር ወደ ንጉሱ ቤተ-መንግስት ከተጋበዙት ኡለማዎች አንዱ ነበሩ፡፡ የንጉሱን እጅ የመጨበጡ ተራ

በደረሳቸው ጊዜ ሰይድ ሸረፍ አል-ዲን ለንጉሱ በቆዳ የተለበጠ ቁርዓን በስጦታ አበረከቱላቸው:: ንጉሱም ቁርዓኑን ተቀብለው ግንባራቸውን ካስነኩ በኋላ ሳሙት:: አል-ሰይድ ሸረፈዲንም እንዲህ አሏቸው:: «ንጉስ ሆይ! በፍየል ቆዳ ብቻ የተሰራውን ሽፋን ስመው ይህን ያህል ክብር የሰጡት ለምንድን ነው?» ንጉሱም «ለቅዱስ ቁርዓን ታላቅ ክብር ለመስጠት ብዬ እንጂ ለፍየል ቆዳው ስል አይደለም» በማለት መለሱ:: አል-ሰይድ ሸረፈዲንም «ንጉስ ሆይ! መልካም ብለዋል እኛም የመልዕክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር መስኮቱን ወይም በሩን ስንስም ይህንኑ በማሰብ ነው፤ በብረት የተሰራና ጉዳትም ሊያስከትል፣ ጥቅምም ሊያመጣ እንደማይችል እናውቃለን፡፡ ከብረቱና ከእንጨቱ ጀርባ ያለውን በማሰብ ነው፤ እርስዎ ከፍየል ቆዳ የተሰራውን ሽፋን ሲስሙ ለቁርዓኑ ብለው እንደሆነው ሁሉ እኛ የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ታላቅ ክብር ለመስጠት ስንል ነው በሩንና መስኮቱን የምንስመው» በማለት መለሱላቸው::

ከዚያ የተሰበሰበው ሁሉ አል-ሰይድ በተናገሩት በመነካት «ትክክል ነህ» አሏቸው ንጉሱም ሓጃጆቹ ከነቢዩ ቅርሶች በረከትን እንዲለምኑ ለመፍቀድ ተገደዱ:: ግና ትዕዛዙ በንጉሱ ወራሽ ተቀለበሰ:: ጉዳዩ ሌሎችን ከአላህ ጋራ የሚያገናኙ ሰዎችን መፍራት ሳይሆን ሙስሊሞች ላይ ስልጣናቸውን ለማጠናከር ሲሉ ሙስሊሞችን በማጋጨትና በመግደል ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ጉዳይ ነው:: ለዚህም በሙስሊሙ ህዝብ ላይ የፈጸሙት ድርጊት ታሪክ ራሱ ምስክር ነው» ስለ ሱፊ ጠሪቃ ጥያቄ አቅርቤላቸው እንዲህ ሲሉ በአጭሩ መለሱልኝ «በእነሱ ላይ አዎንታዊና አሉታዊ አቅጣጫዎች ይገኙባቸዋል:: አዎንታዊ አቅጣጨዎቹንም የግል ስነ-ስርዓት፣ ልቅ ያልሆነ አኗኗር፣ አለማዊ ደስታዎችን ማግለልና እራስን ወደ መንፈሳዊው ዓለም ከፍ ማድረግ ይጨምራሉ፣ አሉታዊ አቅጣጫዎቹ ደግሞ ራስን ማግለል

ሃይማኖትን እንደ ማምለጫ መንገድ መጠቀምና በጽሁፍ ቁጥሮችና በተለያዩ ሌሎች ነገሮች የአላህን ስም መጥራቱን መወሰን ናቸው፡፡ እስልምና እንደሚታወቀው ሁሉ አዎንታዊ አቅጣጫዎችን ሲቀበል አሉታዊዉን ውድቅ ያደርጋል፡፡ የእስልምናም መርሆዎችና ትምህርቶች ሁሉ አዎንታዊ ናቸው እንላለን፡፡»

## ጥርጣሬና መምታታት

አል-ሰይድ አል-ሰድር መልሶች ግልጽና አሳማኝ ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ ለእንደኔ ዓይነቱ ሰዉ ለመረዳት አስቸጋሪ ነበር፡፡ ሃያ አምስቱ የህይወቴ ዘመናት ተመስርተው የነበሩት የነቢዩን ቅርብ ጓደኞችን በተለይም በትክክለኛው መንገድ የተመሩትን ኻሊፋዎች በማመስገኑና በማክበር ሃሳብ ላይ ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ በተለይ የአቡበከር አል-ሲዲቅንና የዑመር አል-ፋሩቅን ትምህርቶች እንድከታተል አዘውናል፡፡ ግና የኒህን ሰዎች ስም ኢራቅ ውስጥ ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ ሲነሳ ሰምቼም አላውቅም፡፡ ከዚህ በፊት ሰምቻቸው የማላውቃቸው እንግዳ ስሞች ሰማሁ፡፡ አስራ ሁለት ኢማሞች የነበሩ መሆኑንም ሰማሁ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም ከመሞታቸው በፊት ኢማም አሊ እንዲተኩዋቸው ተናግረው እንደነበረም ሰማሁ፡፡ ይህን ሁሉ ታዲያ እንዴት ልመን? ሁሉም ሙስሊሞች ብሎም ከሰዎች ሁሉ ምርጥ የነበሩት የነቢዩ ቅርብ ጓደኞች ከነቢዩ ህልፈት በኋላ አሊን (ዐ.ሰ) ተቃውመው በአንድነት ሊቆሙ ተስማሙ? ከልጅነታቸው ጀምሮ ደግሞ የነቢዩ ቅርብ ጓደኞች አሊን ያከብሯቸዉ ነበር፡፡ ምን ዓይነት ሰው እንደነበሩም ጠንቅቀው ያውቁ ነበር እያሉ አስተምረውናል፡፡ የፋጡማ አል-ዛህራ ባለቤትና የሀሰንና የሁሴይን አባት እንዲሁም የእውቀቱ ከተማ በር እንደነበርም ጠንቅቀው

ያውቃሉ፡፡ ከሁሉም በፊት ሙስሊም ስለሆኑትና በሃያሉ አላህ በቁርዓን ውስጥ ነቢዩን እስከዋሻው ድረስ መሸኘታቸው ስለተጠቀሰውና የአላህ መልዕክተኛም በታመሙ ጊዜ ሰላት የመምራቱን ሃላፊነት ስለሰጧቸው ስለእሳቸውም እንዲህ ስላሉት «አንድ የቅርብ ጓደኛ አብሬ ይገኔ የምሄድ ብሆን ኖሮ አቡ በከርን በመረጥኩ» ስለተባለላቸው አቡ በከር አል-ሲዲቅ አለቃችን አሊ በደንብ ያውቁ ነበር፡፡ በነዚህ ሁሉ ምክንያት ሙስሊሞች ኻሊፋቸው እንዲሆኑ መርጠዋቸዋል፡፡ አላህ ከእስልምና ጋር አብሮ ከፍተኛ ቦታ ስለሰጣቸውና የአላህ መልዕክተኛም አል-ፋሩቅ ትክክለኛነትን ከስህተት የሚለዩ ብለው ስለሚጠሩዋቸው አለቃችን ኡመር፤ ኢማም አሊ በሚገባ ያውቃሉ፡፡ በተጨማሪም የአሏህ መላኢካዎች የሚያፍሯቸዉ የሆኑና የአል-ኡስራ ሰራዊትን ያደራጁ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «ዙል አል-ኑረይን» «የሁለት ብርሀን በለቤት» የሚል ስያሜ የተሰጠዉን ኡሰማንንም ዓሊ ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ታዲያ ለምን ይሆን የሺዓ ወንድሞቻችን ይህን ሁሉ ችላ ያሉት ወይም ችላ ያሉ የሚመስሉትና እኒህን ታላቅ ሰዎች ዓለማዊ ለሆኑ ሀላፊ ሀሳቦች ተገዥ የሆኑ ተራ ሰዎች አድርገው የሚያዩዋቸው ብሎም ከነቢዩ ህልፈት በኋላ የእሳቸውን ትእዛዛት እንዳላከበሩና ከትክክለኛው መንገድም እንዳፈነገጡ አድርገው የሚስማሙት፡፡ ይህ ደግሞ ፈጽሞ የማይታሰብ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ምንጊዜም ቢሆን የመልዕክተኛውን ትዕዛዛት ለማስፈፀም ግንባር ቀደም ነበሩና፡፡ ለእስልምና ከፍተኛ ቦታና ለመጨረሻው ድሉ ሲሉ ልጆቻቸውን፤ አባቶቻቸውንና የጎሳቸውን አባላት ሳይቀር ገድለዋል፡፡ ለአላህና ለመልዕክተኛው ሲል የራሱን አባትና ልጅ የሚገድል ሰው የአላህ መልዕክተኛን ትዕዛዛት ወደጎን ትቶ ለአለማዊና ለአላፊ ምኞቶች ራሱን ተገዥ አያደርግም፡፡

ምንም እንኳ በብዙ ነገሮች እንዳምን ብደረግም በእነዚህ ምክንያቶች ግን ሺዓዎች የሚሉትን ሁሉ ላምን አልቻልኩም፡፡ በጥርጣሬና በተምታታ ሁኔታ ውስጥ ቆየሁ፣ የሺዓ የተማሩ ሰዎች (ኡለማዎች) በነገሩኝ ስሜት የሚሰጡ ትክክለኛ የአስተሳሰብ ዘዴ የተከተሉ ሆነው ባገኘኋቸው ነገሮች ስጠራጠር የነቢዩ የቅርብ ጓደኞች አላህ ሁሉንም ይባርካቸውና በመልዕክቱ ብርሃን ሳይቀረጹ ወይም በመሐመድ ህዳሴ ሊያገኙ ሳይችሉ በሞራል አቋማቸው ዘቅጠው እንደ እኛ ተራ ሰው ሆኑ የሚለውን ማመን ስላልተቻለኝ ተምታታብኝ፡፡ አቤቱ ጌታዬ! ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የነቢዩ የቅርብ ጓደኞች በሺአዎች በተነገረው ደረጃ ላይ ሊሆኑ ይችላሉን? ዋናው ነገር ጥርጣሬና መምታታት የድክመት መጀመሪያ መሆኑና እውነቱ ላይ ከመድረሱ በፊት ብዙ ድብቅ ጉዳዮች መኖራቸውን መገንዘቡ ነው፡፡

ጓደኛዬ መጣና ተያይዘን ወደ ከርበላ ተጓዝን፡፡ እንደ የኢማም አል-ሁሴይን ተከታዮችና ወዳጆች እኔም የኢማሙን አሳዛኝ ህይወት በከርበላ ኖርኩ፡፡ ያኔ ብቻ ነው ተራ ሞት እንዳልሞቱ የተገነዘብኩኝ፡፡ ልክ አል-ሁሴይን አሁን ሰማእት እንደሆኑ ሁሉ ሰው መቃብራቸውን ዙሪያውን እንደንብ ከቦ ከዚህ በፊት ጭራሹን ባላየሁት ሁኔታ በከፍተኛ የሀዘን ስሜት ይለቀስ ነበር፡፡ ተናጋሪዎች በለቅሶና በዋይታ ታጅበው ከርባላ ላይ ስለተፈፀመው ድርጊት ያደረጉት ንግግር የሰውን ስሜት ቀስቅሰው ወዲያው አድማጩ ስሜቱን መቆጣጠር ተስኖት እየተዝለፈለፈ ይወድቃል፡፡ እኔም ዓለም እንደተደፋብኝ አልቅሼ አልቅሼ ከዚህ በፊት ተሰምቶኝ የማያውቅ እፎይታ ተሰማኝ፡፡ ከአል-ሁሴን ጠላቶች ወገን በቅጽበት ለሳቸው ሲሉ ራሳቸውን መስዋዕት እንዳደረጉት ተከታዮቻቸው እንደ አንዱ የተቀየርኩ መስሎ ተሰማኝ፡፡

ተናጋሪው አል-ሁሴይንን ከሚወጉት አዛዦች አንዱ በጦር ሜዳው መሃል ላይ ቆሞ እንደ ቅጠል ይርገፈገፍ ስለነበረው ስለአል-ሁር ታሪክ ሲናገር አንዱ ጓደኛው አል-ሁርን እንዲህ ሲል ጠየቀው በማለት ቀጠለ፡፡ «ትፈራለህ እንዴ?» አል-ሁርም «አይ! በአላህ እምላለሁ፤ ፈርቼ አይደለም፡፡ ከጀነትና ከጀሃነም እየመረጥኩ ነው» ሲል መለሰለት፡፡ ፈረሱን ኮርኩሮ ወደ አል-ሁሴይን ገስግሶ በመሄድ እንዲህ ሲል ጠየቃቸው «የአላህን መልዕክተኛ ልጅ ሆይ! ተውበት ይኖረኝ ይሆን?» አላቸው፡፡
ይህን በሰማሁ ጊዜ ራሴን መቆጣጠር ተስኖኝ ተዝለፍልፌ መሬቱ ላይ ወድቄ አለቀስኩ፡፡ ልክ «የአላህ መልዕክተኛ ልጅ ሆይ! ተውበት ይኖረኝ የሆን? የአላህ መልዕክተኛ ልጅ ሆይ! ይቅር በሉኝ» እያልኩ በመወትወት ልክ ሁር በነበረበት ሁኔታ ውስጥ የገባሁ መስሎ ተሰማኝ፡፡ የተናጋሪው ድምጽ በጣም አሳዛኝ ከመሆኑም የተነሳ ሰው ሁሉ ያለቅስና ዋይ ዋይ ይል ነበር፡፡ ጓደኛዬም የእኔን ለቅሶ ሰምቶ ልክ እናት ልጇን እንደምታቅፍ ዓይነት እቅፍ አድርጎኝ «አቤት ሁሴይን አቤት ሁሴይን» እያለ ማልቀስ ጀመረ፡፡

የለቅሶን ትርጉም የተማርኩባቸውና እንባዎቼም ልቤንና ከውስጥ ጀምሮ ሰውነቴን ሲያጥቡ የተሰማኝ ወቅቶች ነበሩ፡፡ ከዚያም በኋላ መልዕክተኛው እንዲህ ሲሉ የተናገሩት ትርጉሙ ገባኝ «እኔ የማውቀውን አውቃችሁ ቢሆን ኖሮ ጥቂት ስቃችሁ ብዙ ባለቀሳችሁ ነበር»

ምንም እንኳ ጓደኛዬ ለስላሳ መጠጦች እየጋበዘ ሊያዝናናኝ ቢጥርም የመጠጥና የምግብ ፍላጎቴ ሙሉ ለሙሉ ጠፍቶ ስለነበር ቀኑን ሙሉ

ከፍቶኝ ዋልኩኝ፡፡ የአል-ሁሴይንን ሸሂድ መሆን ታሪክ ደግሞ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት፡፡ የእኛ የሃይማኖት መሪዎች የእስልምና ጠላት የሆኑት አለቆቻችንን ኡመርን ኡስማንና አሊን እንደገደሏቸው እነዚያው ጠላቶች አለቃችንን አል-ሁሴንን እንዲሁ እንደገደሏቸው ከነገሩን በስተቀር ሌላ ምንም የምናውቀው ነገር የለም፡፡ በእርግጥ አሹራን እንደማንኛውም የእስልምና በአል እናከብረዋለን፡፡ ለድሃ እንመጸውታለን ልዩ ልዩ ምግቦች እናዘጋጃለን፡፡ ወጣት ልጆችም ወደ ትላልቆቹ ይሄዱና ጣፋጮችና መጫወቻዎች የሚገዙበት ገንዘብ ይሰጧቸዋል፡፡

ይሁንና በአሹራ ወቅት በጥቂት መንገዶች አንዳንድ ባህሎች ይታያሉ፣ ሰዎች እሳት አያነዱም፤ ምንም ዓይነት ሥራ አይሰሩም፡፡ በዚህ ወቅት ሰዎች ጋብቻ አይፈጽሙም፡፡ ምንም ዓይነት የደስታ ስርዓት አያከብሩም፡፡ እኛም ሁኔታውን ዝም ብለን ተቀብለንዋል፡፡ ሊያስረዳንም የሚሞክር አልነበረም፡፡ በጣም እንግዳ የሆነው ነገር ደግሞ የሃይማኖት መሪዎቻችን የአሹራን ታላቅነትና የተባረከ መሆኑን በደፈናው ይነግሩናል፡፡

ከዚህ በኋላ የአል-ሁሴይን ወንድም የሆኑት የአል-አባስን መቃብር ሄደን ጎበኘን፡፡ ማን እንደነበሩ አላውቅም ነበር፡፡ ጓደኛዬ ግን ስለጀግንነታቸው አጫወተኝ፡፡ ስማቸውን በዝርዝር የማላስታውሰው በርከት ካሉ መንፈሳዊ የሃይማኖት መሪዎች ጋራ ተገናኘን፡፡ ሆኖም ግን የመጨረሻ ስማቸውን አስታውሳለሁ፡፡ ባህር አል-ኡሉም አል-ሰይድ አል-ሃኪም፣ ካሺፍ አል-ጊጣእ፣ አል-ያሲን አል-ጠባጠባዒ አል-ፈይሩዛባዲ፣ አሰድ ሀይደርና ሌሎችም ሁሉ አብሬአቸው የመሆንን ክብር ያገኘሁባቸዉ እውነተኛ

መንፈሳዊ የሃይማኖት መሪዎች ናቸው። የሺአ ሰው ሁሉ ስለሚያከብራቸው ከገቢው አንድ አምስተኛውን ለእነሱ ይሰጣል። በነዚህ መዋጮዎችም የሃይማኖት ትምህርት ቤቶችን ያካሂዳሉ። አዲስ ትምህርት ቤቶችን ይከፍታሉ። ጋዜጦች ያሳትማሉ። ከመላው እስልምና ዓለም ወደነሱ የሚመጡትን ተማሪዎች ይደጉማሉ። በምንም መንገድ ከገዥዎች ጋራ ሳይገናኙ ነፃ ሆነው የሚሰሩ ናቸው። የእኛ የሃይማኖት መሪዎች ግን ደሞዛቸውን ከሚከፍሏቸው ከሚሾሟቸውና በፈለጉም ጊዜ ከሚያወርዷቸው ባለስልጣኖች ፈቃድ ውጭ ምንም ነገር ማድረግም ሆነ መናገር አይችሉም።

ይህ ያገኘሁት አዲስ አለም ነበር ወይም በትክክለኛ አነጋገር አላህ ለኔ ያገኘልኝ አዲስ ዓለም ነበር። ቀደም ሲል ገሸሽ ሳደርገው የከረምኩት አሁን ግን እወደው ጀመር። ስቃወመው ኖሬ ቀስ በቀስም የተመሳሰልኩት ዓለም ነበር። ከዚህ አዲስ ዓለም አዳዲስ አስተሳሰቦችን አትርፌአለሁ። ከሚፈለገው እውነታ እስክደርስ ድረስ ለዕውቀትና ለምርምር ጥማት እንዲኖረኝ ገፋፍቶኛል። ይህም የሚከተለውን የነቢዩን አባባል ባነበብኩ ቁጥር ትውስ ይለኛል። «የእስራኤል ልጆች በሰባ አንድ ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር። ክርስቲያኖች ደግሞ በሰባ ሁለት ቡድኖች ተከፋፍለው ነበር። የኔ ሰዎች ደግሞ በሰባ ሦስት ቡድኖች ይከፋፈላሉ። ከእነዚህ ውስጥ ከአንዱ በስተቀር ሁሉም ወደ ጀሃነም ይወርዳሉ።»

ይህ እኛ ትክክለኞች ነን የተቀሩት ግን የተሳሳቱ ናቸው ስለሚሉት የተለያዩ ኃይማኖቶች የምንነጋገርበት ቦታ አይደለም። ይሁንና የነቢዩን አባባል

ባነበብኩ ቁጥር ይገርመኛልም ይደንቀኛልም። የምገረመውም የምደነቀውም በራሱ በአባባሉ ሳይሆን ይህን በሚያነቡትና በንግግራቸው ውስጥም በሚደጋግሙት ነገር ግን ሳይመረምሩት እንዲያው ሽረብ አድርገው በሚያልፉት የትኛው ቡድን እንደሚድኑና የትኞቹም አንደሚጠፉ ለማወቅ ጥረት እንኳ ለማያደርጉት ሙስሊሞች ነው።

የሚገርመው ነገር ደግሞ እያንዳንዱ ቡድን የምድነው እኔ ነኝ እያለ መናገሩ ነው። ከአባባሉ መጨረሻ ላይ የሚቀጥለው ይመጣል «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነማን ናቸው?» እሳቸውም «እኒያ የኔንና የሶሃቦቼን መንገድ የሚከተሉት» በማለት መልሰዋል። በቁርዓንና በሱና የማያምን ቡድን አለን? ከዚህ በተለየ የሚያምንስ የእስልምና ቡድን አለን? ኢማም ማሊክ ወይ አቡ ሀኒፋህ ወይ አል-ሽረፍ ወይ አህመድ ኢብን ሀንበል ቢጠየቁ ሁሉም በቁርዓንና በትክክለኛው ሱናህ ትምህርቶች እናምናለን በማለት አይመልሱልንም?

በአንድ ወቅት አፈንጋጮችና የተወናበዱ ናቸው ብዬ ከምኮንናቸው የሺአ ቡድኖች ሌላ እነዚህ ደግሞ የሱኒ መዝሀቦች ናቸው። የሚናገሩትን ሁሉ ጠንቅቀው ያውቁ በነበሩት በአህሉል በይት (የነቢዩ ቤተሰብ) በኩል ሲወርድ ለመጣው ለትክክለኛ ሱናና ቁርዓን ሁላቸውም ታማኞች ነን ይላሉ። ታዲያ እነሱ እንደሚሉት ሁሉም ትክክለኞች ሊሆኑ ይችላሉ? ይህ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም አባባሉ ሆን ተብሎ ተፈጥሮ ካልሆነ በስተቀር የነቢዩ አባባል የሚያሳየን ተቃራኒውን ነው። በሌላ በኩል አባባሉ በሺአዎችም በሱኒዎችም ተቀባይነት ስላለው ምንም ትርጉም ላይኖረው

ይችል ይሆን? ይህም ሊሆን አይችልም፡፡ የእሱ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከአንደበታቸው የሚወጡት በጥበብ የተሞሉ ቃላቶች ብቻ እየሆኑ አላህ ይሰውረንና ትርጉም የለሽና መልዕክት አልባ የሆኑ አባባሎችን ሊናገሩ አይችሉም፡፡ ስለሆነም አንድ ሊሆን የሚችል ድምዳሜ ላይ እንደርሳለን፡፡ ይህም በትክክለኛው ጎዳና ላይ የሚገኘው አንድ ቡድን ሲሆን የተቀረው ግን የተሳሳተ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አባባሉ በአንድ በኩል አንድን ሰው ግራ ወደማጋባትና ወደ ማምታታት አዝማሚያ ሲወስድ በሌላ በኩል ደግሞ ለመዳን የሚሹትን ሁሉ እንዲማሩና እንዲመራመሩ ያበረታታል፡፡

በዚህም ምክንያት ከሺአዎች ጋራ ከተገናኘሁ በኋላ ግራ የመጋባት መንፈስ አደረብኝ ተጠራጣሪም ሆንኩ፡፡ ግና ማን ያውቃል! የሚናገሩ እውነት ይሆናል! ማንበብና መመራመር አይገባንምን?

እስልምና በቁርዓንና በሱናም እንድማር እንድመራመርና እንዳወዳድር አዞኛል፡፡ ከሁሉም በላይ የሆነው አላህም እንዲህ ብሏል «***እነዚያም በኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን፡፡ አላህም በእርግጥ ከበጎ ሰሪዎች ጋራ ነው***» **(ቁርዓን 24፡69)** «***እነዚያን ንግግር የሚያዳምጡትንና መልካሙን የሚከተሉትን እነዚያ እነርሱ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ እነዚያም እነሱ ባለአእምሮዎቹ ናቸው፡፡***» **(ቁርዓን 39፡ 18)**

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል «እብድ ነው እስከምትባል ድረስ ሃይማኖትህን አጥና» ስለዚህ ሃላፊነት ለሚሰማው ለእያንዳንዱ ሰው መመራመርና ማወዳደር በህግ የተሰጡት ግዴታዎች ናቸው፡፡

ከዚህ ጽኑ ውሳኔ ላይ በመድረስ ለኢራቅ ሺአ ጓደኞቼና ለራሴም ቃል በመግባት በጣም ስለወደድኳቸውና እነሱም ስለወደዱኝ በከፍተኛ ሀዘን ስሜት ተውጬ ሁሉንም አቅፌ ተሰናበትኳቸው፡፡ እነዛን ውድና ታማኝ ጓደኞቼን ትቼ እንደሄድኩ ተሰማኝ፡፡ ምስጋና ይግባውና የአላህን ዉዴታ ለማግኘት በስተቀር እኔ ምንም ነገር ሳይጠይቁ ይህን ሁሉ ያደረጉልኝ በራሳቸው ምርጫ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል «አንድን ሰው በትክክለኛው ጎዳና ላይ እንድትመራው አላህ ከመረጠህ በዚህ ዓለም ላይ ካሉት ሀብቶች ሁሉ የበለጠ ዋጋ ይኖረዋል፡፡»

ከኢማሞችና ከተከታዮቻቸው መሀል ለሃያ አንድ ቀናት ከኖርኩ በኋላ ኢራቅን ለቅቄ ወጣሁ፡፡ ጊዜው አንድ በህልም ውስጥ ያለ ሰው ሊያቋርጠው እንደማይፈልገው ጥሩ ህልም ሆኖ ነው ያለፈው፡፡ የጊዜው ማጠር እያበሳጨኝና እኒህን በአህሉል በይት ፍቅር የተሞሉትን ውድ ጓደኞቼን ትቼ መሄዴም እያሳዘነኝ ከኢራቅ ተነሳሁ፡፡
የአላህን ቤትና የመጀመሪያውና የመጨረሻውን ሰይዳችንን (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ለመዘየር አስቤ ከኢራቅ ተነስቼ ወደ ሂጃዝ አመራሁ፡፡

## የሂጃዙ ጉዞ

ጅዳ ደረስኩና ከጓደኛዬ አል-በሽር ጋራ ተገናኘሁ። እሱም እኔን በማግኘቱ በጣም ተደስቶ ወደ ቤቱ ይዞኝ በመሄድ ደግነት የተሞላበት የእንግድነት አቀባበል አደረገልኝ። በእሱ መኪና በመሆን እየተዘዋወርን ብዙ ቦታዎችን በመጎብኘት ጊዜውን አሳለፍን። የኡምራ ፀሎትም አብረን ካደረግን በኋላ የፀሎትና የሃይማኖት ሥራዎችን በማከናወን ጥቂት ቀናትን አብረን አሳለፍን በኢራቅ ውስጥ ረጅም ቆይታ በማድረጌ ስለዘገየሁ ይቅርታ ጠይቄው ስለ ኢራቁ አዲስ ግኝቴ ወይም ስለ አዲሱ እምነት አጫወትኩት። እሱም ብሩህ አእምሮ ያለውና ብዙም የሚያውቅ ስለነበረ እንዲህ አለኝ «ይህ እውነት ነው ምክንያቱም በጣም የተማሩ ምሁራን እንዳላቸው ሰምቻለሁ፣ ግና በሀጅ ወቅት ከፍተኛ ችግር የሚፈጥሩ አፈንጋጭ ቡድኖችም አሏቸው» እኔም «የሚፈጥሯቸው ችግሮች ምንድን ናቸው?» በማለት ጠየቅኩ፣ «በመቃብሮች ዙሪያ ይሰግዳሉ፤ እያለቀሱና ዋይ ዋይ እያሉ በቡድን በቡድን በመሆን ወደ አል-በቂዕ ይገባሉ። የሚሰግዱበትም ትናንሽ ድንጋዮች ይዘዉ ኡሁድ ውስጥ የሚገኘውን የአለቃችን የአል-ሃምዛን መቃብር ከጎበኙ ደግሞ ልክ አል-ሃምዛ አሁን እንደሞቱ አድርገው ኡኡ እያሉ ደረታቸውን በመደለቅ አዲስ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ያከናውናሉ። በነዚህ ሁሉ ምክንያት የሳውዲ መንግስት መቃብሮችን እንዳይጎበኙ አግዷቸዋል» አለኝ። እኔም ሳቅሁና እንዲህ አልኩት «በዚህ ምክንያት ነው እንዴ ከእስልምና ያፈነገጡ ናቸው ብለህ የፈረድከው?»

«በሱም በሌላም ምክንያቶች የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ለመጎብኘት ይመጣሉ፡፡ በዚያኑ ወቅትም በአቡበክርና በኡመር መቃብሮች ላይ ቆሻሻ ይወረውራሉ» ሲል መለሰልኝ፡፡

እነዚህን ክሶች በሰማሁ ጊዜ አባቴ ከሐጅ እንደተመለሰ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ላይ ቆሻሻ ይጥላሉ ብሎ የነገረኝ ትውስ አለኝ፡፡ ይህን ድርጊት አባቴ ራሱ በዓይኑ ፈጽሞ እንዳላየ አልጠራጠርም፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ብሎኝ ነበር «የሳውዲ ሰራዊት አባላት የነበሩ ጥቂት ወታደሮች ጥቂት ሐጅ አድራጊዎችን በዱላ ሲመቱ አይተን በአላህ ቤት እንዲህ ዓይነት አሳፋሪ ድርጊት በሐጃጆች ላይ መፈፀሙን በተቃወምንበት ጊዜ ወታደሮቹም እነዚህ ሙስሊሞች አይደሉም፤ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ላይ ቆሻሻ ይዘው ለመወርወር የመጡ ሺአዎች ናቸው ባሉን ጊዜ እኛም ረግመናቸው ከተፋንባቸው በኋላ እዛው ትተናቸው ሄድን»

አሁን ደግሞ በአል-መዲና አል-ሙነዋራህ ውስጥ በተወለደው ሳዑዲያዊው ጓደኛ ደግሞ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ለመጎብኘት መጥተው በአቡበክርና በዑመር መቃብሮች ላይ ቆሻሻ ይወረውራሉ የሚለውን ወሬ ሰማሁ፡፡ ሁለቱንም ወሬዎች ተጠራጠርኳቸው፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ለሐጅ በመጣሁበት ጊዜ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ)፣የአቡበክርና የዑመር መቃብሮች የሚገኙበት የተባረከ ክፍል ግጥም ተደርጎ የተቆለፈ በመሆኑ ማንም ወደዚያ ቀርቦ በሩንም ሆነ መስኮቱን ሊነካ ወይም ምንም ነገር ወደ ውስጥ ሊወረውር ስለማይችል ነው፡፡ ይህም ሁለት ምክንያቶች አሉት፣ አንደኛው ምንም ክፍተት ባለመኖሩ ሁለተኛው ደግሞ ፈርጣማ የሆኑ ወታደሮች

ያቀፈ ጥብቅ ጥበቃ በየአንዳንዱ በር ላይ ስለሚካሄድ እያንዳንዱ ወታደርም ወደ ክፍሉ ጥሶ ለመግባት የሚሞክርን ሐጃጅ የሚገርፍበት ጅራፍ በመያዙ ነው። በሺአዎች ላይ ባደረባቸው መሰረተ-ቢስ ጥላቻ ምክንያት አንዳንድ የሳውዲ ወታደሮች ሺአዎችን በዚህ ድርጊት የሚወነጅሉዋቸው በእነሱ ላይ የሚወስዱትን የኃይል እርምጃ ትክክለኛነት ለማሳየት ሲሉ ወይም ደግሞ ሺአዎች የአላህን መልዕክተኛ ስለሚጠሉዋቸው በመቃብራቸው ላይ ቆሻሻ ይጥላሉ የሚለውን ወሬ ሌሎች ሙስሊሞች በየአገሮቻቸው እንዲያራቡና እንዲዋጓቸው ለማነሳሳት ይሆናል። ሁለት ወፎች በአንድ ድንጋይ ይላሉ ይህ ነው።

አንድ የማምነው ትልቅ ሰው የሚከተለውን ታሪክ ነገረኝ። የአላህን ቤት በመዞር ላይ ሳለን አንድ ወጣት ሰው ሆዱን ክፉኛ ይታመምና እዚያው ያስመልሰዋል። ጥቁሩን ድንጋይ የሚጠብቁት ወታደሮችም አል-ካዕባን አረከሰው ብለው ይደበድቡት ጀመር። በሚያሳዝን ሁኔታ ከዚያ አውጥተው ይወስዱትና ለፍርድ አቅርበውት በዚያኑ ቀን ይገደላል።

እነዚህ ሁሉ ድራማዎችና መሰል ታሪኮች በአእምሮዬ እየተሽከረከሩ ሳውዲያዊው ጓደኛዬ የሺአ እምነትን ለማጉደፍ ያቀረበውን ማስረጃ ለሰኮንድ አሰላሰልኩት። ይሁን እንጂ ደረታቸውን እየደለቁ ከማልቀስ፣ ድንጋዮች ላይ ከመስገድና በመቃብሮችም ላይ ከመስገዳቸዉ ሌላ ምንም ላገኝባቸው አልቻልኩም። ራሴንም እንዲህ ስል ጠየቅኩት። «ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ መሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) የእሱ አገልጋይና መልዕክተኛ ነው ብሎ የሚያምንን ሰው ስም ለማጉደፍ ይሄ በቂ ነውን? ይሰግዳሉ፣

ይመፀውታሉ፣ ረመዳንን ይፆማሉ፣ ለሐጅ ወደ አላህ ቤት ይሄዳሉ፤ ጥሩ ሥራዎችን ይሠራሉ፤ መጥፎ የሆኑትን ያስወግዳሉ፡፡»

ጓደኛዬን ላለማስቀየምና አላስፈላጊና ጥቅመ-ቢስ ውይይት ውስጥ ላለመግባት ስለፈለግሁ በአጭሩ እንዲህ አልኩት «አላህ ለእነሱም ለእኛም ልብ ይስጠን፣ ወደ ትክክለኛው መንገድም ይምራን የእስልምናን እና የሙስሊሞችን ጠላቶች አላህ የተረገሙ ያድርጋቸው፡፡»

በአል ዑምራህ ወቅት በአላህ ቤት ዙሪያ በዞርክ ቁጥር እንዲሁም ጥቂት ኅብኝዎች ብቻ ባገኘሁበት በተባረከው መካ ባደረግሁት ጉብኝት ወቅት ዓይኖቼን እንዲከፍትልኝና ወደ እውነቱ እንዲመራኝ እየፀለይኩ አላህን ከልቤ ለመንኩት፡፡ በአብርሃም መቆሚያ (መቃሙ ኢብራሂም) ቦታ ላይ ቆሜም ከቁርዓን ውስጥ የሚከተለውን ቀራሁ፡፡ «አላህም ሀይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም፣ የአባታችሁን የኢብራሂምን ሃይማኖት ተከተሉ፣ እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል፡፡ በዚህም (ቁርዓን) መልዕክተኛው በናንተ ላይ መስካሪ እንዲሆን እናንተም በሰዎቹ ላይ መስካሪዎች እንድትሆኑ (ሙስሊም ብሎ ሰይሟችኋል)፡፡ ሰላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ፡፡ ዘካንም ስጡ፣ በአላህም ተጠበቁ፤ እርሱ ረዳታችሁ ነው፤ እሱም ምንኛ ያማረ ጠባቂ ነዉ? ምንኛ ያማረ ረዳት ነዉ?»

ከዚያም በመቀጠል ነብዩ ኢብራሂምን ወይም ቁርዓን ውስጥ እንደሚጠቀሰው አባታችን ኢብራሂምን መጥራት ጀመርኩ፡፡ አቤቱ አባታችን! ሙስሊሞች ብለህ የምትጠራን ልጆችህ ከአንተ በኋላ ሊስማሙ አልቻሉም፡፡ አንዳንዶቹ ይሁዲ ሆኑ፡፡ ሌሎቹ ክርስቲያኖች፤ ሌሎቹ ደግሞ ሙስሊሞች

ሆኑ፣ ይሁዲዎች በሰባ አንድ ቡድኖች ተከፋፈሉ፣ ክርስትያኖች ደግሞ ሰባ ሁለት ቦታ ተከፋፈሉ። ሙስሊሞች ደግሞ በሰባ ሶስት ቡድኖች ተከፋፈሉ። ለልጅህ ለመሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንደነገርካቸው ሁሉም ጨለማ ውስጥ ናቸው፡ ፡ አንዱ ቡድን ግን ለአንተ እምነት ታማኝ እንደሆነ ቆይቷል። እዉን ጽንፈኞች እንደሚያስቡት አሏህ ፍጡራኑ እንዲህ እንዲከፋፈሉ ነዉ የፈለገዉ? እያንዳንዱ ሰዉ ምን መሆን አለበት? አይሁድ፤ ክርስቲያን፤ ሙስሊም፤ ሀይማኖት አልባ፤ የበርካታ አምላኮች አማኝ ...ወዘተ በዕጣ ፈንታ የተወሰነ ነዉ እንደሚባለዉ ነዉ ወይስ ሰዎች ለአለማዊ ኑሮ ብለዉ ከአሏህ ትዕዛዛት ሲያፈነግጡና ጌታቸዉን ሲረሱ እራሳቸዉን እንዲረሱ አደረጋቸዉ?

በተለይም አለቆቻቸዉና መሪዎቻቸዉ የነበሩ ሰሃባዎች ሌሎችን ደካማ አቋም የነበራቸዉን ሰሃባዎች በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስም የተፈለሰፉና የዉሸት ሀዲሶችን በመጠቀም ቀጣዩ ትዉልድ በስልጣን ላይ የነበሩ ሰሃቦችን በተለይም ደግሞ የኸሊፋነት ቦታ ላይ የደረሱትን የዑመያዎችና የአባሲያዎች ባለ ስልጣናት እንዲያወድሱና ጥሩ ገድላቸዉን ብቻ እያወሱ እንዲኖሩ ማድረጋቸዉን ስንረዳ የመሪነቱን ቦታ እንዲቆናጠጡና ሙስሊሞችን እንዲገዙ ያደረጉት ብቸኛ ምክንያት እነሱ መሆናቸዉን እንገነዘባለን። ለዚህ አባባሎች ታሪክ ቀዳሚዉ ምስክር ነዉ።

የሰው ልጅ ዕጣው አስቀድሞ ተወስኗል፤ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚከተለውን ሃይማኖትም አላህ መድቧል የሚባለውን ላምን አልቻልኩም። ይልቁንም አላህ ፈጥሮን የትኛው ትክክልና የትኛው ስህተት እንደሆነ አይተን

እንድንረዳ አነቃቅቶናል፡፡ ለዚህም ትክክለኛውንና ስህተት የሆነውን እንዲያመላክቱን ብሎም ውስብስብ የሆኑ ጉዳዮችን በግልጽ እንዲያስረዱን የእሱን መልዕክተኞች ልኮልናል የሚለውን ለማመን አዘነበልኩ፡፡ የሰው ልጅ ግን በዚህ የሚያማልል ህይወት ተጠላልፎ በመውደቅ፣ በእብሪቱ፣ ራስ ወዳድነቱ፣ በአለማወቁ፣ በጉጉቱ፣ በግትርነቱ፣ በኢ-ፍትሐዊነቱና በጭካኔው ከትክክለኛው መንገድ አፈንግጦ ሸይጣንን ተከተለ፡፡ ከመሃሪው አሏህ ራሱን አራቀ፡፡ በዚህም ምክንያት መንገዱን ሳተ፡፡ ይህንንም በአላህ ቃላት ቅዱስ ቁርዓን ግሩም በሆነ መንገድ ገልፆታል፡፡ «***አላህ ሰዎችን ምንም አይበድልም፣ ግን ሰዎች ነፍሶቻቸውን ይበድላሉ፡፡***» (ቅዱስ ቁርዓን 10:44)

አቤቱ ኢብራሂም አባታችን! መንገዱን እንዲመለከቱ ከተደረገ በኋላ ትክክለኛ ውን ጎዳና ባለመከተላቸው ይሁዲዎችንም ሆነ ክርስቲያኖችን ልንወቅሳቸው አንችልም፡፡ ልጅህን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ህዝብ ልኮ ህዝቡ ከጨለማ ወጥቶ መንፈሳዊ ህዳሴ ያገኛዉንና ከዉድቀት አረንቋ የዳነዉን ይህን ህዝብ ተመልከተዉ፡፡ ምርጥ ህዝብ አደረጉት፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) «አንድ ሙስሊም ከሶስት ጊዜ በላይ ከወንድሙ ሙስሊም ጋር መኮራረፍ የተከለከለ ነው» ብለው ቢያስጠነቅቁዋቸውም ሙስሊሞች ግን እርስ በርሳቸው በሚዋጉ በርካታ ቡድኖች ተከፋፈሉ፡፡

ይህ ህዝብ እንዲህ ብዛት ባላቸው እርስ በእርሳቸው በሚዋጉ ትናንሽ መንግስታት (አንዳንዶቹ እንዲያውም እርስ በርሳቸው አይተዋወቁም) የተከፋፈለው ምን ነክቶት ይሆን አባታችን ኢብራሂም ሆይ! ይህን ህዝብ ምን ነካው? ከአለም ውስጥ ምርጥ ህዝብ ነበር፤ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ

የሚገዛና ለሌሎች ህዝቦችም እውቀትን ያስተዋወቀና መንፈሳዊ ግንዛቤም የሰጠ ነበር፡፡

ዛሬ ግን በታሪኩ ዝቅተኛ ቦታ ላይ ውሏል፡፡ መሬቱ ተደፍሯል፡፡ ህዝቡም ከቀየው ተባሯል፡፡ አል-አቅሷ መስጅድም በጽዮናዊያን ወንበዴዎች ተይዞ ማንም ነፃ ሊያወጣው አልቻለም፡፡ አንድ ሰው አገራቸውን ሄዶ ቢጎበኝ የሚያየው አስከፊ ድህነት፣ ገደብ የለሽ ረሃብ፣ ወደ በረሃነት የተለወጠ መሬት፣ በሽታ፣ መጥፎ ምግባራት፣ የትምህርትና የቴክኒክ ኋላ ቀርነት፣ ጭካኔ፣ጭቆናና ጉስቁልና ብቻ ነው፡፡ በሁለቱ መካከል በንጽህና በኩል ያለውን ልዩነት ለማየት የምዕራብ አውሮፓን መፀዳጃ ቤቶች እኛ አገር ካሉት ጋራ ማነፃፀሩ ብቻ በቂ ነው፡፡ «ንጽህና የእምነት ምልክት ነው፣ ቁሻሻ የሽይጣን ምልክት ነው፡፡» ብሎ እስልምና ቢያስተምረንም እንዲህ ዓይነት ዝቅተኛ የንጽህና ደረጃ ላይ መድረሱ እንቆቅልሽ ነው፡፡ እምነቱ ወደአውሮፓ ገብቶ ሽይጣን ከእኛ ውስጥ ለመኖር ወደ እኛ መጥቶ ይሆን? ሙስሊሞች በአገራቸው ውስጥ እንኳ ስለእምነታቸው በግልጽ ለመናገር የሚፈሩት ለምን ይሆን? ሙስሊሙ የራሱ ፊት ባለቤት እንኳ ሆኖ ፂሙን ማሳደግ የማይችለው ለምን ይሆን? ሃጢአተኞቹ በአደባባይ አልኮል እየተጋቱና አሰቃቂ ነገሮችን ሲፈፅሙ ሙስሊሙ ሊያርማቸውና ትክክለኛውን መንገድ ሊያሳያቸው እንኳ አይችልም፡፡ እራሳቸው ሙስሊሞችም እስላማዊ አለባበስን መልበስ አይችሉም፡፡ እንደ ግብጽ ወይም ሞሮኮ በመሳሰሉት አንዳንድ የእስልምና ሀገሮች ከችግርና ከድህነት የተነሳ ሴት ልጆቻቸው ገላቸውን እንዲሸጡ የሚያደርጉ አባቶችም እንዳሉ ሰምቻለሁ፡፡

አምላክ ሆይ! ለምንድን ነው ይህን ህዝብ የተውከውና ጭለማ ውስጥ የጣልከው? ልክ አይደለሁም አምላኬ! እባክህ ይቅር በለኝ ምክንያቱም ይህ ህዝብ ነው አንተን ትቶ የሽይጧንን መንገድ የመረጠው፡፡ አንተ ደግሞ

በወደር የለሽ ጥበብህና ሃይልህ እንዲህ ብለሃል፡፡ ቃልህ ደግሞ ፍፁም እውነት ነው፡፡ «***ከአል-ረህማን ግሣፄ (ከቁርዓን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን፡፡ ስለዚህ እርሱ ለእርሱ ቁራኛ ነው***» (**ቅዱስ ቁርዓን 43፡36)**

*ሙስሊሙ* ህዝብ ወደዚህ በጣም ዝቅተኛ የሆነ ወደ ተገዥነትና ኋላቀርነት ደረጃ ማሽቆልቆሉ የእሱ ከትክክለኛው *መንገድ* የማፈንገጡ ምልክት *መሆኑ* አያጠራጥርም፡፡ ከሰባ ሶስት ቡድኖች *መካከል* አናሳው ክፍል ወይም አንዱ ቡድን የመላው ህዝብ እጣ ላይ መልካም ለዉጥ ሊያመጣ አይችልም፡፡ የአላህ *መልዕክተኛ* (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡፡ «ጥሩ *ሥራዎችን* እንድትሰሩና የሚነቀፉ ድርጊቶችን እንድታስወግዱ ትዕዛዝ ተላልፎላችኋል፡፡ አለበለዚያም አላህ ጨካኞቹን በእናንተ ላይ ያስቀምጣል፣ ያኔም መልካም የሆኑ ሰዎቻችሁ እየጮሁ ቢለምኑም ማንም የሚሰማቸው አይኖርም፡፡»

*አምላክ ሆይ! ወደእኛ የላክኸውን እናምናለን፡፡ መልዕክተኛውንም እንከተላለን፡፡ ከአመኑት ወገኞች ጋር ትቀላቅለን ይሆን? አምላክ ሆይ! ከአለማወቅ ጨለማ ካወጣኸን በኋላ እባክህ ልቦናችንን አትለውጠው፡፡ እባክህን አምላኬ! አንተ ሁሉን ሰጭ ነህና ምህረትን ስጠን፡፡ አምላክ ሆይ! ራሳችንንም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ነው የያዝነው፡፡ አንተ ይቅርታ ካላደረክልንና ካልራራህልን ከተሸናፊዎች እንደምንደበል እርግጥ ይሆናል፡፡*

ጓደኛዬ አል-በሺር መዲና በምቆይበት ጊዜ አብሬው እንድኖር የሚጠይቅ አንድ ደብዳቤ ለአንድ ዘመዱ ጽፎ ሰጥቶኝ እሱን ይዤ ወደ አል-መዲና አል-ሙነወራ ለመሄድ ተነሳሁ፡፡ ቀደም ሲል በስልክ ነግሮት ስለነበረ እዚያ

እንደደረስኩ በደንብ ተቀብሎኝ ወደ ቤቱ ወስዶ መኖሪያ ሰጠኝ፡፡ ወዲያው እንደደረስኩም ተጣጥቤ የክት ልብሴን ለባበስኩና፣ የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ለመጎብኘት ሄድኩ፡፡ ከሃጅ ወቅት ጋራ ሲነፃፀር ጥቂት ጎብኝዎች ብቻ ስለነበሩ በህዝብ መጨናነቅ የተነሳ በሐጅ ጊዜ ላደርገው ያልቻልኩትን አሁን በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በአቡበከርና በዑስማን መቃብሮች ፊት ለመቆም በቃሁ፡፡ ለበረካ ብዬ በሮቹን ለመንካት ስሞክር አንዱ ዘበኛ ክፉኛ ተቆጣኝ፡፡ ለመዘየርና የልመና ፀሎትም ለማድረስ ረጅም ጊዜ በመቆየቴ ዘበኞቹ እንድወጣ አዘዙኝ፡፡ አንዱን ዘበኛ ለማነጋገር ያደረግሁትም ሙከራ ከሸፈ፡፡

ወደ ተባረከዉ ጓሮ ተመለስኩና ተቀምጬ ቁርአን መቅራት ጀመርኩ፡፡ የአሏህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ያዳምጡኛል ብዬ ስላሰብኩ ደጋግሜ ቀራሁ፡፡ ለራሴም እንዲሁ አልኩ፡፡ መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንደማንኛውም የሞተ ሰው ሞተዋል የሚለው የሚታመን ነውን? ከሆነም ለምንድን ነው ልክ ለእሳቸው እንደምንናገር ዓይነት በፀሎታችን ውስጥ «ታላቁ ነቢይ ሆይ! ሠላም ለዕርስዎ ይሁን፣ የአላህ ራህመትና ሰላት በእርስዎ ላይ ይውረድ» የምንለው? ሙስሊሞች አለቃችንን አል-ከድር አልሞቱም፣ሰላም ለሚሉዋቸው ሁሉ የአፀፋ ሠላምታ ይመልሳሉ ብለው ያምናሉ፡፡ በተጨማሪም የሱፊ ጠሪቃ ተከታዮች ሼኮቻቸው አህመድ አል-ቲጃኒ ወይም አብዱል ቃድር አል-ጂላኒ በህልም ውስጥ ሳይሆን በውናቸው ሊያዩዋቸው እንደሚመጡ ያምናሉ፡፡ ታዲያ ከሰው ዘር ምርጥ ለሆኑት ለአላህ መልዕክተኛ ይህን ክቡር ድርጊት ለማጎናፀፍ ችላ የምንለው ለምንድን ነው? በእርግጠኝነት መናገር የምንችለዉ ግን ከወሃቢያዎች ዉጭ ሙስሊሙ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) በተመለከተ ችላ ብለዉ እንደማያዉቁ ነዉ፡፡ በዚህና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶችም ከዋሃቢዎች መሸሽ ጀመርኩ፡፡

ከእምነቶቻቸው ጋራ የማይስማሙትን ሌሎች ሙስሊሞች ስለሚያጎሳቁሉዋቸው ምግባራቸው ጭካኔ የተሞላበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ የአል-በቂዕን የመቃብር ስፍራ እንደጎበኘሁት የአህሉል ቤት ነፍሶች ላይ ምህረት እንዲወርድ በመጠየቅ ላይ ሳለሁ ከአጠገቤ የቆሙ አንድ አዛውንት ሲያለቅሱ ተመለከትኩና ሺአ መሆናቸውን ልገነዘብ ቻልኩ፡፡ አዛውንቱ ፊታቸውን ወደ ካዕባ አዙረው መስገድ እንደጀመሩ እንቅስቃሴአቸውን ይከታተል የነበረ አንድ ወታደር ከመቅጽበት ወደ እሳቸው ተምዘግዝጎ በመሄድ ልክ እንዳጎነበሱ በእርግጫ መታቸዉ፡፡ አዛውንቱ ህሊናቸውን ስተው ተዘረሩ፡፡ ወታደሩም የእርግማን ዓይነት እያወረደባቸው ይደበድባቸው ጀመር፡፡ የአዛውንቱ ሁኔታ አንጀቴን ስለበላውና የሞቱም ስለመሰለኝ እንዲህ ስል ወታደሩ ላይ ጮህኩበት! «እንዲህ ማድረግ አይገባህም! እንዴት እየሰገዱ እያሉ ትመታቸዋለህ» እሱም በቁጣ «ዝም በል! ጣልቃ አትግባ! አለበለዚያ አንተም እንደሱ አቀምስሃለሁ» አለኝ፡፡ ወታደሩ በጠበኛነት የተካነና ደም የሸተተው መሆኑን ስገነዘብ ትቼው ዞር አልኩ፡፡ ትክክለኛ ያልሆነ እርምጃ የሚወስድባቸውን ሰዎች መርዳት ባለመቻሌ በራሴ ተበሳጨሁ፡፡ የሚቆጣጠራቸውና የሚጠይቃቸው ባለመኖሩ ሰውን እንደፈለጉት በሚያደርጉት ሳውዲዎች ላይም ንዴት አደረብኝ፡፡ ይህን ድርጊት የተመለከቱ ሌሎች ጥቂት ጎብኝዎች ቢኖሩም ሊያደርጉት የቻሉት የሚከተለውን ማለት ብቻ ነበር፡፡ «ሃይልና ጉልበት የአላህ ብቻ ነው፡፡» በተቃራኒው አንዳንዶች ደግሞ «ይገባዋል፣ መቃብሮች ላይ ነበር እኮ የሚሰግደው» ሲሉ ሰማሁ፡፡ ራሴን መቆጣጠር አቃተኝና ይህን የተናገረውን ሰው እንዲህ አልኩት «መቃብሮች አጠገብ መስገድ የለብንም ብሎ የነገረህ ማን ነው?» እንዲህ ሲል መለሰልኝ «ይህ እንዳናደርግ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከልክለውናል» እኔም በቁጣ ስለአላህ መልዕክተኛ ሀሰት እየተናገርክ ነው» አልኩት የሁኔታውን አደገኛነት በመገንዘብና ሌሎች ደግሞ ወታደሩን

ጠርተው ያስደበድቡኛል ብዬ ስለሰጋሁ ለስለስ ብዬ እንዲህ አልኩት «የአላህ መልዕክተኛ በመቃብሮች አጠገብ እንዳንሰግድ ከከለከሉን በመላው የእስልምና ዓለም በሚገኙ መስጂዶችና በተቀደሰው የነቢዩ መስጂድ ውስጥ በሚገኙ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአቡበከርና የዑመር መቃብሮች አጠገብ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ፀሎተኞችና ጎብኝዎች የእሳቸውን ትእዛዝ ጥሰው በመስገድ ሃጢአት መስራታቸው ለምንድን ነው? በመቃብሮች አጠገብ መፀለይ ሃጢአት ቢሆን እንኳ እንዲህ ዓይነት የጭካኔ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል ወይስ ጨዋነት የተሞላበት እርምጃ ወስዶ ድርጊቱን ማስቆም? በአላህ መልዕክተኛ መስጂድ ውስጥ በእሳቸው ፊት ሽንቱን ስለሸናው ግለሰብ ታሪክ እንዳጫውታችሁ ፍቀዱልኝ፡፡ እንዲህ በማድረጉ ከነቢዩ ሰሀቦች አንዳንዶቹ ጎራዴአቸውን መዘው ሊገሉት ሲሉ ነቢዩ አስቆሙአቸው፡፡ እንዲህ አሉዋቸው «ምንም ጉዳት አታድርሱበት! ልቀቁት ይሂድ፡፡ በሸናው ቦታ ላይ ውሃ አፍስሱበት እኛ የተላክነው ነገሮችን ቀላል ለማድረግ እንጂ አስቸጋሪ ለማድረግ አይደለም:: መልካም ቃል ለማስፋፋት ነው እንጂ የተላክነው ሰዎች ከእኛ እንዲርቁ ለማድረግ አይደለም:: የነቢዩ ሰሀቦችም ትእዛዛቸውን አከበሩ፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ሰውየውን ጠርተው ከጎናቸው እንዲቀመጥ ካደረጉት በኋላ በትህትና አነጋገሩት፡፡ ይህ ቦታ የአላህ ቤት መሆኑንና መቆሸሽም እንደማይገባው አስረዱት:: ከዚህ በኋላ ሰውየው የክት የሆኑትንና ንጹህ ልብሶችን ለብሶ ከመስጂዱ በመታየቱ ነጥቡን መረዳቱን ያመለክታል:: ታላቁ አላህ ለመልዕክተኛው እንዲህ በማለት የተናገረው ለዚህ ነበር፡፡» «***አመለ መጥፎና ልበ ደረቅ በሆንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር***» **(ቅዱስ ቁርዓን 3:159)**

ይህን ታሪክ በሰሙ ጊዜ አንዳንዶቹ ጎብኚዎች ልባቸው ተነካ፡፡ ከነሱም አንዱ ወደ ጎን ዘወር አድርጎ ወሰደኝና «ከየት ነው የመጣኸው?» ሲል

ጠየቀኝ «ከቱኒዚያ» አልኩት፡፡ ከዚያም ሠላምታ ሰጠኝና «ወንድሜ ሆይ! በአላህ ራስህን ጠብቅ! በፍፁም እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን እዚህ አትናገር፡፡ ለአላህ ስል ለአንተ የምሰጥህ ምክር ይህ ነው» አለኝ፡፡ ከእነሱ አስተሳሰብ ጋራ የማይጣጣሙትን የነቢዩን አባባሎችን መጥቀስ፣ ከእነርሱ አስተሳሰብ መንገድ ጋራ አብሮ የማይሄድ እምነትን በመያዝ ወይም አስተያየት መስጠት ለማንም የማይፈቅዱትና የአሏህ እንግዶች ላይ እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ድርጊት በፈፀሙባቸው በእኒህ የአል-ሀረሜይን ጠባቂዎች ነን ባዮች ላይ ከፍተኛ ቁጣ አደረብኝ፡፡

ገና ስሙን ካላወቅሁት ወደ አዲሱ ጓደኛዬ ቤት ተመልሼ ሄድኩ፡፡ እሱም እራት አቀረበልኝና ከፊት ለፊቴ ቁጭ ብሎ የት እንደዋልኩ ጠየቀኝ፡፡ ታሪኬን ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ አጫወትኩትና እንዲህ አልኩ «ወንድሜ ወሃቢዮችን መኮነንና ወደ ሺአዎች ማዘንበል ጀምሬአለሁ» ከመቅጽበት ፊቱ ተለዋወጠና እንዲህ አለኝ፡፡ «እንዲህ ዓይነቱን ነገር ሁለተኛ እንዳትናገር አስጠንቅቅሃለሁ» እራቱን እንኳ ሳይጨርስ ብድግ ብሎ ጥሎኝ ሄደ፡፡ እኔም የመኝታ ሰዓቴ እስኪደርስ ቁጭ ብዬ ብጠብቀዉም ሳይመለስ ቀረ፡፡ በሚቀጥለውም ቀን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ አዛን ሲደረግ ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡ የጓደኛዬ ምግብ ምንም ያልተነካ መሆኑንም ባየሁ ጊዜ ጭራሽ ተመልሶ እንዳልመጣ ገባኝ፡፡ ወዲያው ጥርጣሬ ገባኝና ሰውየው ምናልባት የሚስጥራዊ ድርጅት አባል ሊሆን ይችላል ብዬ በመስጋት ፈጠን ብዬ ከቤቱ ወጥቼ ለሰላት ወደ ነብዩ መስጂድ ሄድኩ፡፡ ከዙህር ሰላት በኋላ አንድ ተናጋሪ ለጀመዓው ትምህርት ሲሰጥ አየሁና ወደሱ አመራሁ፡፡ ቆየት ብዬም ትምህርት የሚሰጠው ሰው የአል-መዲናህ ቃዲ መሆኑን ትምህርቱን ከሚከታተሉት አንዱ ተረዳሁ፡፡ አንዳንድ የቁርዓን አንቀፆችን ሲያስረዳ

አዳመጥኩት፡፡ ትምህርቱን ጨርሶ ሊሄድ ሲል አስቆምኩትና እንዲህ ስል ጠየቅኩት «እባክህ ጌታው የሚከተለውን የቁርዓን አንቀጽን ትርጉም በተመለከተ አንዳንድ ነጥቦችን ግልጽ ልታደርግልኝ ትችላለህ?» «***የነቢዩ ቤተሰቦች ሆይ! አላህ የሚሻው ከናንተ ላይ ርክሰትን ሊያስወግድና ማጥራትንም ሊያጠራችሁ ብቻ ነው***» (ቅዱስ ቁርዓን 33:33)

«በዚህ የቁርዓን አንቀጽ ውስጥ አህሉል ቤይት የሚለው ማንን ነው» ስል ጠየቅሁት፡፡ እሱም ፈጠን ብሎ እንዲህ መለሰልኝ «የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶች ናቸው፡፡ አንቀፁም እነሱን በመጥራት ይጀምራል፡፡ «***የነቢዩ ሚስቶች ሆይ ፈጣሪን ከፈራችሁ እናንተ እንደሌሎቹ ሴቶች አይደላችሁም***»

እኔም እንዲህ አልኩት «የሺአ ኡለማዎች ግን አሊን፣ ፋጡማን አል-ሃሰንን እና አል-ሁሴይንን ነው ይላሉ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ ከእነሱ ጋር አልስማማም፡፡ ምክንያቱም የጥቅሱ መጀመሪያ እንዲህ ይላል፡፡ «የነቢዩ ሚስቶች ሆይ!...» ለዚህ ደግሞ እንዲህ ሲሉ መልስ ሰጥተውኛል፡፡ አንቀፅ እነሱን (የነቢዩን ሚስቶች) ማለቱ ከሆነ ሰዋሰዋዊ ይዘቱ እስከመጨረሻው በእንስታይ በሆነ ነበር፡፡ ሃያሉ አሏህ እንዲህ ይላል፡- «...እናንተ (እንደ ሌሎቹ ሴቶች) አይደላችሁም፡፡ ፈጣሪን ከፈራችሁ በንግግራችሁ ሁሉ ለስላሳ አትሁኑ፤ ተናገሩ፡፡ በየቤታችሁ ተቀመጡ፣ አካላችሁን ግልጽ አታውጡ፣ በፀሎታችሁ ግፉበት፣ ምጽዋትን ስጡ፣ ለአላህና ለመልዕክተኛው ታዘዙ፡፡» በአረብኛዉ ሰዋሰዉ በዚህ አንቀጽ ዉስጥ ያሉት ግሶች በሙሉ በብዙ እንስታይ ጾታ የተገለጹ ናቸዉ፡፡ *(ውድ አንባቢ ሆይ! በአማርኛዉ ትርጉም ላይ ግልጽ ሆኖ ላይታይ ስለሚችል ይህንን ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት የአረብኛውን መጽሐፍ ይመልከቱ)*

ከዚያ በኋላ ግን በሚቀጥለዉ አያህ (አንቀጽ) ዉስጥ አህሉል ቤይትን የሚመለከተዉ አንቀጽ የተገለጸዉ በተባዕታይ ጾታ የግስ አጠቃቀም ነዉ። ስለዚህ የሰዋሰዉ ለዉጥ አለ ማለት ነዉ።

መነጽሩን አውጥቶ ተመለከተኝና እንዲህ አለ «እነዚህን መርዛማ ሀሳቦች ተጠንቀቅ። ሺአዎች የአላህን ቃላት እነሱ በፈለጉት መንገድ ይለውጡታል። እኛ የማናውቀው እነሱ ስለ አሊና ስለ ልጆቹ በርከት ያሉ አንቀጾች አሉዋቸው። እንደውነቱ ከሆነ እነሱ ልዩ የሆነ ቁርዓን አላቸዉ። ይህንንም የፋጡማ ቁርዓን ብለው ይጠሩታል። በእነሱ እንዳትታለል አስጠነቀቅሃለሁ»

«አትስጋ ጌታዬ እኔ ራሴን እጠብቃለሁ። ስለነሱም ብዙ አውቃለሁ። እንዲያው ለማወቅ ስል ብቻ ነው» አልኩት «ከየት ነው የመጣኸው?» ብሎ ሲጠይቀኝ «ከቱኒዚያ» በማለት መለስኩለት «ስምህ ማነው?» አለኝ «አል-ቲጃኒ» አልኩት። ትእቢት በተሞላበት መልኩ ሳቅ አለና «ለመሆኑ አህመድ አል-ቲጃኒ ማን እንደነበረ ታውቃለህ?» ብሎ ጠየቀኝ «የሱፊ ጠሪቃ ሼክ ነበሩ» «ስል መለስኩለት። እሱም ቀጠል አድርጎ እንዲህ አለ «የፈረንሳይ ቅኝ ገዥ ባለስልጣን ሰላይ ነበር፣ የፈረንሳይ የቅኝ ገዥነት ስርዓት ባአልጄሪያና በቱኒዚያ ስር ሊሰድ የቻለው በሱ እርዳታ ነው። ፓሪስን የመጎብኘት እድል ካጋጠመህ ናሽናል ቢብሊዩቲክ ከሚባለው ቤተ-መጽሐፍት ሂድና የፈረንሳይ መዝገበ ቃላትን ከፍተህ ኤ በሚለው ፊደል ስር ፈልግ። ይህ ነው የማይባል እርዳታ ላደረገው ለአህመድ አል-ቲጃኒ የፈረንሳይ መንግስት የክብር ኒሻን መሸለሙን እዛ ውስጥ ታገኛለህ።»

በነገረኝ ነገር በጣም ተገርሜ አመሰገንኩትና ተሰናብቼው ሄድኩኝ፡፡ በአል-መዲናህ ሳምንት ሙሉ ስቀመጥ አርባ ሰላቶችን ሰግጃለሁ፡፡ አሉ የተባሉትን ቅዱስ ቦታዎችን ሁሉ ተዘዋውሬ ጎበኘሁ፡፡ እዚያ በነበርኩበት ወቅት በጥንቃቄ ብዙ ነገሮችን በመመልከቴ በወሃቢዮች ላይ ያለኝ ጥርጣሬ እየጨመረ ሄደ፡፡

አል-መዲና አል-ሙነወራህን ለቅቄ በሐጅ ጉዞ ወቅት ተዋውቄአቸው የነበሩትን ጓደኞቼን ለመጠየቅ ወደ ዮርዳኖስ አቀናሁ፡፡ ከእነሱም ጋራ ለሦስት ቀናት አብሬ ኖርኩ፡፡ በነዚህ ቀናት እኚህ ጓደኞቼ ከቱኒዚያ ህዝብ በበለጠ ደረጃ በሺአዎች ላይ ከፍተኛ ጥላቻ እንዳለባቸው ተገነዘብኩ፡፡

የተለመዱት ታሪኮችና መሰረተ-ቢስ ወሬዎች እዚህም ተራብተዋል፡፡ እስቲ ማስረጃ ስጠኝ ብዬ የምጠይቀው ሰው ሁሉ ሲባል ሰማሁ የሚል መልስ ብቻ ነው የሚሰጠኝ፡፡ የሺአ እምነት ካለው ሰው ጋራ የተገናኘ ወይም የሺአ መጽሐፍ ያነበበ አንድም ሰው ላገኝ አልቻልኩም፡፡

ከጆርዳን ወደ ሶሪያ ተጓዝኩ፡፡ በደማስቆ ውስጥም የአለቃችን የአል-ሁሴይን ጭንቅላት ካረፈበት ቦታ አጠገብ የሚገኘውን የኡመያ መስጂድን ጎበኘሁ፡፡ የሰላሀዲን አል-አዩቢንና የእመቤት ዘይነብ ቢንት አሊ ኢብን አቢ ጣሊብን መቃብርም ጎበኘሁ፡፡

ቤይሩት ላይ ቀጥታ ወደ ትሪፖሊ የሚጓዝ መርከብ ላይ ተሳፈርኩ፡፡ ጉዞው አራት ቀናት በመፍጀቱ እኔም በአካልም ሆነ በአእምሮ ተዝናናሁ፣ አረፍኩ፡፡ ያደርግሁትን ጉዞ በአእምሮዬ ውስጥ መልሼ ስመለከተው ወደ ሺአ ማዝመሜና ለነሱም አክብሮት እያዳበርኩ መሆኑን ተረዳሁት፡፡ በአንፃሩም

ወሃቢዮችን መጥላትና ከነሱም መሸሽ መጀመሬን ተገነዘብኩት፡፡ ሁሉን ለሰጠኝና ላደረገልኝ እንክብካቤ አላህን አመሰገንኩት፡፡ ሃያል የሆነዉ ጌታ ከፍተኛ ምስጋና ይግባዉና ወደትክክለኛው መንገድ እንዲመራኝ ለመንኩት፡፡ ቤተሰቦቼንና ጓደኞቼን ለማግኘት ጓጉቼ አቤቱ ደረስኩ፡፡ ሁሉንም በደህና አገኘኋቸው፡፡ ወደ ቤቴ ስገባ ከእኔ ቀድሞ ብዙ መፃህፍት ደርሶ በማግኘቴ እጅግ ተደነቅሁ፡፡ ይህ ሁሉ መጽሐፍ ከየት እንደመጣ አውቄዋለሁ፡፡ ቤቱን የሞሉትን እነዚህን መፃህፍት ስከፍት ቃላቸውን ያላጠፉትን እነዚያን ሰዎች አመሰገንኳቸው፡፡ እንደውነቱ ከሆነ በፖስታ ቤት በኩል የላኩልኝ መፃህፍት በብዛት እዚያ ሳለሁ በስጦታ ከሰጡኝ ይበልጣሉ፡፡

## ጥናትና ምርምሩ ተጀመረ

አደራጆቼ «መፃህፍት ቤት» ብዬ ከጠራሁት ልዩ ቦታ ባስቀመጥኳቸዉ መጻህፍት ተደስቼአለሁ፡፡ ለጥቂት ቀናት እረፍት ካደረግሁ በኋላ የአዲሱን የትምህርት ዘመን ፕሮግራም ተቀበልኩ፡፡ በፕሮግራሙ መሠረት ለሦስት ተከታታይ ቀናት አስተምርና አራቱን ቀናት ነፃ እሆናለሁ፡፡

መጽሀፍቱን ማንበብ ጀመርኩ ፡፡ በመጀመሪያ «ዐቃዒድ አል-ኢማሚያህ» እና «አስል አል-ሺዓ ወ ኡሱልሃ» የሚባሉ መጽሀፍ አነበብኩ፡፡ ከዚያም «አል ሙራጃዓት» የተሰኘዉን የሰይድ ሸረፈዲን አል-ሙሰዊን መጽሐፍ አነበብኩ፡፡ የመጀመሪያዎቹን ጥቂት ገፆች እንዳነበብኩት እጅግ በጣም ስለተመሰጥኩ በጣም አስፈላጊ ካልሆነ አላቋርጠውም ነበር፡፡ እንዲያውም መጽሐፉን ይዤ ወደ ኢኒስቲትዩት እሄድ ነበር፡፡ በአል-አዝሃር ለሚገኙ የሱኒ ምሁራን የተወሳሰቡ መስለው የሚታዩትን ችግሮች ቁልጭ ባለ

መንገድ እንዴት እንደሚፈቷቸው አስደነቀኝ፡፡ የምፈልገውን ነገር መጽሐፉ ውስጥ አገኘሁ፡፡ ያለ ሂስና ያለ ውይይት ደራሲው የፈለገውን ብቻ እንደሚጽፈውና ተራ መጽሐፍ ዓይነት አይደለም፡፡ አል-ሙራጀአት ሁለት የተለያየ መዝሀብ የሚከተሉ ምሁራን በቃል ምልልስ መልክ የሚያደርጉ ክርክር ነዉ፡፡ ሁለቱም ለማስረጃነት የሚያቀርቡት ሁለቱን የሙስሊሞች ሁሉ አስፈላጊ ማጣቀሻዎችን ነዉ፡፡ እነዚህም የአዒህ ኪታብ (ቁርአንና) በሰሂህ አል-ሲታ የተረጋገጡ ትክክለኛ ሱና ላይ ነዉ፡፡ በኔና በመጽሐፉ ሃሳብ መካከል አንድ የጋራ የሆነ ነገር እንዳለ ተረዳሁ፡፡ ምክንያቱም እኔ እውነትን የምፈልግ መርማሪ በመሆኔ በተገኘበት ቦታ ልቀበለው ፈቃደኛ ነበርኩ፡፡ ስለሆነም ይህ መጽሐፍ በጣም ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ታላቅ ባለውለታዬም ሆኗል፡፡

ጥቂት ሰሃባዎች የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ አሻፈረን፣ አንቀበልም ብለው ነበር የተባለዉን ጉዳይ መጽሐፉ ውስጥ ሳገኝ ገረመኝ፡፡ ለዚህ ብዙ ምሳሌዎች መስጠት ይቻላል፡፡ «ራዚያት ያውም አል-ኸሚስ (የሃሙሱ ቀን ሰቆቃ) ጭምር አቅርቧል፡፡ አለቃችን ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ፣ ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዛትን መቃወማቸውና እሳቸውንም በሃጅር (በቅዠት) መወንጀላቸውን ላስበውም አይቻለኝም፡፡ መጀመሪያ ላይ ይህ በሺአ መጽሐፍት ውስጥ ያለ ተራ ታሪክ ነው ብዬ ገመትኩ፡፡ ሆኖም ግን ይህ የሺአ ምሁር ይህን ድርጊት ያገኘው «የአል-ቡኻሪ ሰሂህ» እና «የሙስሊም ሰሂህ» ከሚባሉ መፃህፍት ማግኘቱን ባየሁ ጊዜ እጅግ ገረመኝ፡፡

ወደ ዋናዉ ከተማው ሄጄ፣ ሰሂህ አል-ቡኻሪ፣ ሰሂህ አል-ሙስሊም፣ ሙሰነድ ኢማሙ አህመድ፣ ሙወጠዕ ኢማም ማሊክና ሌሎች ስሙ-ጥር

መጽሐፍት ገዛሁ። እቤት ደርሼ እነዚህን መፃህፍት ማንበቡ አላደርስ ስላለኝ ከቱኒስ ወደ ጋስፋ በምጓዝበት ወቅት አውቶቡስ ውስጥ ቁጭ ብዬ የአል-ቡኻሪን መጽሐፍ እየገላለጥኩ እንዲያው ባላገኝሁት እያልኩ ጣርኩ። ነገር ግን አገኘሁትና ደጋግሜ አነበብኩት ልክ አል-ሰይድ ሸረፈዲን እንደገለፀው ሆኖ አገኘሁት። ይህን ሁኔታ እንዳለ ሙሉ ለሙሉ ልክድ ሞከርኩ። አለቃችን ኡመር እንዲህ አይነት አደገኛ ሚና ተጫውተዋል ብዬ ለማመን ተሳነኝ። ግና በኛ ሲሀህ ማለትም አህለሱናህ በሲሃህ የተጠቀሰውንና በዚያ ውስጥ ያለውን እንድናምን የምንገደደውን እንዴት ብዬ መካድ እችላለሁ። ምክንያቱም የተፃፉትን ብንጠራጠርና እንዳንዶቹንም ብንክድ ሁሉንም እምነቶቻችንን እንደተውን ይቆጠራል። የሺአው ምሁር የእነሱን መፃህፍት ጠቅሶ ቢሆን ኖሮ የተናገረውን ምንም አላምነውም ነበር። ይህን ያገኘው ልንተቸው ከማንችለው ከአላህ መጽሐፍት ቀጥለው ከሁሉም የላቁ እውነተኛ መፃህፍት መሆናቸውን ከምናምንባቸው አል-ሱናህ ሲሃህ ነው። እና ይህ ጉዳይ የሚገታን ነው። ምክንያቱም እነዚህን ሲሃህ ከተጠራጠርን ልንመካበት የምንችል ምንም የእስልምና ህግና ደንብ ላይኖረን ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በአላህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሕግጋትና ደንቦች የተቀመጡት በዝርዝር ሳይሆን ጠቅለል ባሉ ጽንሰ ሃሳቦች መልክ ነው። እኛ መልዕክቱ ከወረደበት ጊዜ በጣም የራቅን ነን። ስለሆነም የሃይማኖታችንን ህግጋት የወረስነው ችላ ልንላቸው በማንችለው በነዚህ ሲሃህ በአባቶቻችንና በአያቶቻችን በኩል ተላልፎ ነው። እኔም ሺአዎችና ሱኒዎች በሚስማሙበት በትክክለኛው ሃዲስ ብቻ ለመመርኮዝ ቃል ገባሁ። በአንዱ ወይም በሌላው ቡድን ብቻ የሚጠቀሱትን አባባሎችም ውድቅ ለማድረግ ወሰንኩ። በዚህ ትክክለኛ ዘዴ ብቻ ነው ከስሜታዊ ምክንያቶች፣ ከጠባብ አክራሪነትና ከብሔርተኝነት አዝማሚያዎች እራሴን መጠበቅ

የምችለው፡፡ እንዲህ በማድረግም በጥርጣሬ ጎዳና አልፌ ሄጄ ወደ እርግጠኛ ነት ተራራ ለመድረስ ይቻለኛል፡፡ ይህም የአላህ ትክክለኛ መንገድ ነዉ፡፡

## የዝርዝር ጥናቱ መጀመር፤

### የነቢዩ ሰሃቦች በሺአና በሱኒዎች እይታ

ከሁሉም ጥናቶች በጣም ዋነኛውና ወደ እውነቱ ለሚመሩን ጥናቶችም መሠረት ነው ብዬ የማምነው በነቢዩ ሰሀቦች ህይወት ላይ ማለትም ስራቸውን፣ ድርጊታቸውንና እምነታቸውን አስመልክቶ የምርምር ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰሃቦች የሁሉም ነገር መሰረቶች በመሆናቸውና እኛም ከእነሱ የሃይማኖታችንን መርሆዎች በመውሰዳችን ነው፡፡ የአላህንም ህግጋት ለማየት እንድንችል ጭለማችንን ገፈውልናል፡፡ ይህንን በማመን በርካታ የሙስሊም ምሁራን  በነብዩ ሰሃቦች አኗኗርና ስራዎች ላይ ጥናት ማድረግ ጀመሩ፡፡ ከሚጠቀሱት መጽሀፍት መካከል በሱኒ ምሁራን የተጻፉ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡- ኡስዱል ጋባህ ፊ ተምይዝ አል-ሰሃባ፣ አል-ኢሳባህ ፊ መዕሪፈት አል-ሰሀባና ሚዛን አል-ኢዕትዳል፡፡

እዚህ ላይ ትንሽ ችግር አለ፡፡ ይኸውም አብዛኛዎቹ የቀድሞ ምሁራን በአህሉል ቤይትና በተከታዮቻቸው ላይ የነበራቸው ተቃውሞ ለታወቁት ለአል-ኡመያድና ለአባሲያ መሪዎች በሚስማማ መንገድ መፃፋቸው ነው፡፡ በመሆኑም የሌሎቹን የሙስሊም ምሁራን መፃህፍት ወደ ጎን ትቶ ከላይ በተጠቀሱት መፃህፍ ብቻ ማተኮር ሚዛናዊነት አይኖረውም፡፡ እኒያ ሥራዎቻቸው ችላ የተባሉባቸው ምሁራን የአህሉል ቤይት ተከታዮች ስለነበሩና በጨቋኞችና በአፈንጋጭ ባለሥልጣናት ላይ የተቀጣጠሉትን

አብዮቶች በመደገፋቸው በኡማያድና በአባሲያ መንግስታት ሲሳደዱ ኖረው በመጨረሻው ተገድለዋል፡፡

ለዚህ ሁሉ ዋና ችግር የነበሩት እራሳቸው ሰሃቦች ነበሩ፡፡ ምክንያቱም እስከ ቂያማ (የፍርድ ቀን) ድረስ በትክክለኛው መንገድ ላይ እንዳሉ እንዲቆዩ የሚረዳቸውን ሰነድ እንዲጻፍላቸው በመፈለግ በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻው ትዕዛዝ ወይም ኑዛዜ እርስ በርሳቸው ያለመስማማታቸው ነበር፡፡ ይህ አለመስማማት የመላው ሙስሊም ህዝብ ልዩ ሞራላዊ ንጽሕና በመግፈፉ ተከፋፍሎና የርስ በርስ ግጭት ውስጥ ተዘፍቆ በመጨረሻም የተዝለፈለፈ ሃይል ሆኖ እንዲቀር ጨለማ ውስጥ ወርውሮታል፡፡

በኺላፋህ (ነቢዩን መተካት) ጥያቄ ላይ ያልተስማሙት እነሱ ነበሩ፡፡ እርስ በርሳቸው በገዥና ተቃዋሚ ፓርቲ በመከፋፈላቸው ህዝቡንም የአሊ ተከታዮችና የሙአዊያህ ተከታዮች በሚል ከፋፈሉት፡፡ በአላህ መጽሐፍና በመልዕክተኛው አባባሎች አተረጓጎም ላይ የተለያዩት እነሱ ነበሩ፡፡ ይህ ደግሞ የተለያዩ እምነቶች፣ ቡድኖችና የቡድኖች ቅርንጫፎች እንዲፈጠሩ አደረገ፡፡ ከእነዚህ ደግሞ በከፍተኛ ፖለቲካዊ ስልጣንና ፍላጎት የተገፋፉ በርካታ የመንፈሳዊ ትምህርት ምሁራን እንዲሁም የአስተሳሰብና የፍልስፍና ትምህርት ቤቶች ተወለዱ፡፡ ሁሉም የተነሱት በአእምሮአቸው ውስጥ አንድ አላማ ይዘው ነበር፡፡ ያም ስልጣን የመጨበጥ አላማ ነበር፡፡

ከዚህ በፊት የተፈጠሩት አለመግባባቶችም ሆነ አሁንም እየተፈጠሩ ያሉት አለመግባባቶች የመነጨት ከሰሀቦች አለመግባባት ነበር፡፡ ሰሃቦች ተግባብተው ቢሆን ኖሮ ሙስሊሞች ባልተከፋፈሉ፣ በሃሳብም ባልተለያዩ ነበር፡፡ አንድ አምላክ፣ አንድ ቁርዓን፣ አንድ መልዕክተኛ እንዲሁም አንድ ቂብላ አለ፡፡ ሁሉም በዚህ ያምናል፡፡ ሆኖም ግን ከመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ

በመጀመሪያው ቀን በበኒ ሰዓዳህ ሰቂፋህ (መጠለያ) ውስጥ በሰሃቦቹ መካከል አለመግባባቱ ተጀምሮ እስካሁን ድረስ ቀጥሏል፡፡ አላህ በቃ እስኪል ድረስም ይቀጥላል፡፡ ከሺአ ምሁራን ጋር ባካሄድኳቸው ውይይቶች በእነሱ አመለካከት ሰሀቦቹ በሦስት መደቦች መከፋፈላቸውን ተረዳሁ፡፡

የመጀመሪያው መደብ አላህንና መልዕክተኛውን በትክክል የሚያውቁና እስከ ህይወታቸው መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ ለመልዕክተኛው ምስጋናና ድጋፍ የሰጡትን ጥሩዎቹን ሰሃቦች ይዟል፡፡ በቃላትም ሆነ በተግባር እውነተኛ ጓደኞቻቸው ሆነው ፍፁም ካጠገባቸው ሳይለዩ በጽናት ከጎናቸው ቆመዋል፡፡ ሃያል የሆነው አላህ በቁርአን ውስጥ አመስግኖአቸዋል፡፡ ሺአዎች እኒህን ሰሀቦች ጥልቅ በሆነ ክብርና ሞገስ ያዩዋቸዋል፡፡ ሱኒዎችም እንዲሁ ጥልቅ በሆነ አክብሮትና ሞገስ ይጠቅሱዋቸዋል፡፡

ሁለተኛው መደብ በምርጫ ወይ በፍርሃት እስልምናን የተቀበሉና የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የተከተሉ ሰሃቦች ናቸው፡፡ ለእስልምናቸውም ሁልጊዜ ለአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ምስጋናቸውን እንዳሳዩ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በአንዳንድ አጋጣሚዎች የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አስቀይመዋል፡፡ የእሳቸውንም ትእዛዛት ሁልጊዜ አይቀበሉም፡፡ እንዲያውም በቁርዓን በኩል አላህ ጣልቃ ገብቶ እስከ መገሰጽና ማስፈራራት ደረጃ እስኪደርስ ድረስ አብዛኛውን ጊዜ ከእሳቸው ጋራ ይሟገታሉ፡፡ ግልጽ የሆኑትን ትምህርቶችንም የራሳቸውን አመለካከት ተንተርሰው ትክክል አይደሉም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡ አላህ በበርካታ የቁርዓን አንቀፆች ውስጥ አጋልጧቸዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲሁ በበርካታ አባባሎቻቸው ውስጥ

አስጠንቅቀዋቸዋል፡፡ ሺአዎች እኒህን ሰሀቦች ጥልቅ የሆነ የአክብሮትን ሳይጨምሩ በሡሩት ሥራ ብቻ ይጠቅሱአቸዋል፡፡
ሦስተኛው መደብ አስመሳዮች የነበሩትና የአላህን መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለማታለል እሳቸውን የሚያጅቡ ሰሀቦች ናቸው፡፡ ሙስሊሞች መስለው በውስጣቸው ግን መላ ሙስሊሞችንና እስልምናን በማጭበርበርና በማጉደፍ ተግባር ተሰማርተዋል፡፡ አላህ ስለ እነሱ በቁርዓን ውስጥ ሙሉ ሱራህ አውርዷል፡፡ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ስለነሱ ጠቅሰው ማስጠንቀቂያዎችንም አውጥተዋል፡፡ ከዚህም በላይ የነዚህን ሰሀቦች ስምና ባህሪያቸውንም ለቅርብ ሰሃቦቻቸው ገልፀውላቸዋል፡፡ እነዚህን ሰሀቦች በመርገሙ ላይ ሺአዎችና ሱኒዎች በአንድነት ይስማማሉ፡፡

ከሰሀቦች ዉስጥ አንድ የተለየ ቡድንም ነበረ፡፡ ይኸዉም በወደር የለሽ ሥነ-ምግባርና መንፈሳዊ ጥንካሬ የተቸሩ ከመሆናቸዉም በላይ ከአሏህ መልእክተኛ ጋር የስጋ ዝምድና ያላቸዉና ማንም ያላገኘዉን ክብር ከአሏህና ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያገኙ ልዩ የሆኑ የሰሃቦች ክፍል ነበሩ፡፡ እነዚህም አሏህ ከርክሰት ሁሉ ያጠራቸዉና ልክ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋት እንደምናወርድ ሁሉ በዚህ ቡድን ላይ እንድናወርድ የታዘዝንባቸዉ አህሉል ቤይት (ሰ.ዐ.ወ) ናቸዉ፡፡ የገቢያችንን አንድ አምስተኛ ለነሱ እንድንከፍልና እያንዳንዱ ሙስሊምም ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት ሽልማት እንዲሆን እነሱን ማፍቀር እንዳለበት ግዴታ አድርጎታል፡፡ አለቆቻችን ስለሆኑ ለነሱ መታዘዝ አለብን፡፡ የቁርአንን አንቀጾች «ሙህከምና ሙተሻብህን» በደንብ ለይተዉ የሚያዉቁ በዕውቀት የተካኑ ናቸዉ፡፡ የአላህ መልዕክተኛ «ሁለቱ የከበሩ ነገሮች»[2] (አል- ሰቀለይን) ብለው በተናገሩት አባባላቸው ከቁርዓን ጋር ያስተካከሉዋቸውና የእነሱም ታማኝ ተከታይ እንድንሆን ያዘዙን አህል አል-

ዚክር የተሰኙ ሰዎች ናቸው፡፡ የአሏህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አህሉል ቤይትን በኑህ መርከብ ይመስላሉ፡፡ ይኸዉም በመርከቧ የተሳፈረ እንደሚድንና ያልተሳፈረ ደግሞ እንደሚጠፋ ሁሉ አህሉል ቤይትን የተከተለ ከሚድኑት ሲሆን እነሱን ያልተከተለ ደግሞ እንደሚጠፋ አስተምረዋል፡፡[3] ሰሀቦች የአህሉል በይትን ማዕረግ በሚገባ በመገንዘባቸው ይፈሩአቸዋል፡፡ እንዲሁም ያከብሯቸዋል፡፡ ሺአዎች አህሉል ቤይትን ከማንኛውም ሰሀቦች በላይ ያስቀምጡአቸዋል፡፡ ለዚህም በርካታ ግልጽ የሆኑ የመጽሀፍ ማስረጃዎች አሉዋቸው፡፡

ሱኒዎች ሰሀቦችን ያከብራሉ፣ ይፈራሉ፡፡ ሆኖም ግን ከላይ የተዘረዘሩትን ምደባዎች አይቀበሉም፡፡ አንዳንዶቹ ሰሀቦች አስመሳዮች ነበሩ የሚባለውን አያምኑም፡፡ ይልቁንም ሰሀቦችን ከአላህ መልዕክተኛ በኋላ የነበሩ ምርጥ ሰዎች አድርገው ነው የሚያዩዋቸው፡፡ ሱኒዎች ሰሀቦችን በምድብ ካላስቀመጥዋቸው በዕድሜ፣ በሰሩት ጥሩ ሥራዎችና ለእስልምና በሰጡት ግልጋሎቶች ነው የሚመድቧቸው፡፡ በትክክል የተመሩ ኻሊፋዎችን (ኹለፋእ አል-ራሺዲን) በመጀመሪያው መደብ ያስቀምጣሉ፡፡ ቀጥለውም ጀነትን እንደሚወርሱ ቃል የተገባላቸውን ከአስሩ ስድስቱን ያስከትላሉ፡፡ በመሆኑም በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለቤተሰባቸው ሰለዋት በሚወርዱበት ወቅት ከእነሱ ጋራ ያለ ልዩነት ሁሉንም ሰሀቦች ያያይዛሉ፡፡

ከሱኒ ምሁራን ያወቅሁት ይህን ሲሆን ሰሀቦችንም ደግሞ በተመለከተ ከሺአ ምሁራን የሰማሁት ያን ነበር፡፡ የሰሃቦችን ጉዳይ በተመለከተ ዝርዝር ጥያቄን እንድጀምር ያደረገኝ ይኸው ነው፡፡ በትክክለኛው መንገድ ከመራኝ ስሜታዊ ከሆነ አድልዎ ራሴን ለማስወገድ እንዲሁም ገለልተኛ ለመሆንና ተጨባጭ የሆኑትን ለመቀበል ሁለቱም ወገኖች የሚሉትን ለማዳመጥና ከዚያም

ድምዳሜዎቼን በሁለት መነሻዎች አስመርኩዤ የተሻለውን ለመከተል ለአምላኬ ቃል ገባሁ፡፡

1. ጠንካራና ትክክለኛ የአስተሳሰብ ዘዴን (ሎጂክ) የተከተለ መነሻ ማለትም የአላህን መጽሐፍ እንዲሁም የነቢዩን ክቡር ሱና ትክክለኛ ክፍሎችን በተመለከተ ሁሉም በሚስማማበት ላይ ብቻ በእምነት አተኩራለሁ፡፡
2. አእምሮ፡- አላህ ለሰው ልጆች፣ ይህን ታላቅ ስጦታ ሰጠን፡፡ አላህም ይህንን ለሰው ልጅ ለግሶ ከሌላው ፍጥረት እንዲለይ አደረገው፡፡ ስለሆነም አላህ አማኞች የሚሰሩትን ሲቃወም በተቻላቸው ሁሉ፤ አእምሮአቸውን እንዲጠቀሙ ያሳስባል፡፡ እንዲህም ይላል «አይገባቸውምን?» «አይረዱምን?» «አያዩምን?» ወዘተ. . .

የእኔ እስልምና በተቀዳሚ አላህን፤ የሱን መላኢካዎች የእሱን መፃህፍትና የእሱን መልዕክተኞች፤ መሐመድ የእሱ አገልጋይና የእሱ መልዕክተኛ መሆኑን የአላህ ሃይማኖት እስልምና መሆኑን ማመን ነው፡፡ ከመልዕክተኛው ጋራ ባለው ዝምድና ይሁን በሹመቱም በየትኛው ሰሀባ ፍፁም አልመካም፡፡ እኔ ኡመያድ ወይ አባሲያ ወይ ፈቲማድ አይደለሁም፡፡ እኔ ሱኒም ሺአም አይደለሁም፡፡ በአቡበከር ወይ በኡመር ወይ በኡስማን ወይ በአሊ ብሎም እስላም እስከሆነ ድረስና የአላህ መልዕክተኛም ይቅርታ እስካደረጉለት ድረስ የዐለቃችን የአል-ሀምዛ ገዳይ በነበረው ዋህሺ ላይ እንኳ፣ ጠላትነት የለኝም፡፡ እውነቱ ላይ ለመድረስ ስል ወደዚህ ጥናት እራሴን ገፋፍቼ እስከገባሁ ድረስ ከቀድሞ እምነቶቼ በትክክል ራሴን ስላፀዳሁ በአላህ በረካ የሰሃቦችን የአእምሮ ሁኔታና ስሜትን ግምት ውስጥ በማስገባት ጥናቴን ለመጀመር ወሰንኩ፡፡

## 1. ሰሃቦቹ በአል-ሁደይቢያህ የሰላም ስምምነት

ታሪኩ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

ከሂጅራ (ነቢዩ ከመካ ወደ መዲና ከተሰደዱ) በኋላ በስድስተኛው ዓመት የአላህ መልዕክተኛ ከአንድ ሺህ አራት መቶ ሰሀቦቻቸው ጋር በመሆን ኡምራ ለማድረግ ወደ መካ ተጓዙ፡፡ «ዚል አል-ሃሊፋህ» ላይ ሰፈሩና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሀቦቻቸው መሳሪያቸውን እንዲያስቀምጡና ኢህራም (በተለይ ለሃጂና ለኡምራ የሚለበስ ነጭ ልብስ) እንዲለብሱ አዘዟቸው፡፡ ከዚያም ለአል-ሀድያ (ለመስዋዕት የሚቀርብ) ነገር በመከፋፈል ቁሬሾች የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጭፍራ ለጦርነት ሳይሆን ኡምራ ለማድረግ መሆኑን እንዲረዱ ለማድረግ ሞከሩ፡፡ ቁሬይሾች ግን በድንቁርናቸው የተነሳ ሌሎች አረቦች መሀመድ ወደ መካ በሀይል መግባቱን ከሰሙ ስማችን (የቁሬይሾች) ይጎድፋል ብለው ፈሩ፡፡

ስለሆነም በሱሄይል ኢብን አምር ኢብን አብድ ወድ አል-አሚሪ የሚመራ ልዑካን ወደ መሀመድ ልከው በአሁኑ ዓመት ወደመጡበት እንዲመለሱና በሚቀጥለው ዓመት ግን መካን ለሦስት ቀናት ለመጎብኘት እንደሚፈቀድላቸው ተነገራቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከበድ የሚሉ፣ ጥቂት ቅድመ ሁኔታዎችንም አስቀምጠው ነበር፡፡ በወቅቱ በነበሩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን በማመንና ከአላህ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስምምነቱን ተቀበሉ፡፡ ጥቂቶቹ ሰሀቦች የነቢዩን ድርጊት ስላልወደዱት በጣም ተቃወሙአቸው፡፡ ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ ወደ እሳቸው ዘንድ ቀርበው

እንዲህ ሲሉ ጠየቁአቸው። «እርስዎ በእውነት የአላህ ነቢይ አይደሉምን?» እሳቸውም «አዎ ነኝ» አሉት፤ «እኛ ትክክለኞች፣ ጠላቶቻችን ደግሞ የተሳሳቱ አይደሉምን?» ሲሉ ዑመር ጠየቁአቸው። «አዎን» በማለት መለሱ። ዑመርም በመቀጠል «ታዲያ ለምንድን ነው ሃይማኖታችንን የምናዋርደው?» ብሎ ጠየቃቸው። የአላህም መልዕክተኛ እንዲህ አሉ? «እኔ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ። ፍፁም የእሱን ትዕዛዝ አልጥስም፣ የእኔም ድጋፍ እሱ ነው» ዑመርም ጠየቃቸው «ወደ አላህ ቤት ሄደን ዙሪያውን እንዞረዋለን አላሉንም?» ነቢዩ መለሱ «አዎን ግን በዚህ ዓመት እንደዚያ እናደርጋለን ብዬ ነግሬአችሁ ነበር?» ዑመርም «አልነገሩንም» ሲል መለሰ። ነቢዩም እንዲህ አሉ «ወደዚያም ትሄዳላችሁ። ዙሪያውኑም ትዞሩታላችሁ» ከዚያም ዑመር ወደ አቡበከር ሄደው እንዲህ ሲሉ ጠየቁአቸው «አቡበከር ሆይ! እሳቸው በእውነት የአላህ ነቢይ አይደሉምን?» አቡበከርም «ናቸው» ሲሉ መለሱ። ዑመርም በማስከተል የአላህን መልዕክተኛ የጠየቁአቸውን ጥያቄዎች ሁሉ አቡበከርንም ጠየቁአቸው። እሳቸውም ነቢዩ የመለሱትን መልስ መለሱላቸውና አክለውም እንዲህ አሉዋቸው «ዑመር ሆይ! እሳቸው የአላህ መልዕክተኛ ናቸው። ድጋፋቸው የሆነውን የአምላካቸውን ትዕዛዝ አይጥሱም እናም በጽናት ተከተላቸው»

ስምምነቱን ፈርመው ከጨረሱ በኋላ ሰሀቦቻቸውን እንዲህ አሏቸው «ሂዱና እርድ (መስዋዕቶች) እረዱና ፀጉራችሁን ተላጩ» ይህንን ሦስት ጊዜ ደጋግመው ቢናገሩም ማንም ብድግ ያለ አልነበረም። ማንም ትዕዛዛቸውን ሳያከብር በቀረ ጊዜ ወደ ክፍላቸው ገቡና ተመልሰው ሲወጡ ማንንም ሳያናግሩ ቀጥታ ሄዱና እራሳቸው በእጃቸው አንድ ግልገል ግመል አረዱ። ከዚያም ፀጉር አስተካካያቸው ፀጉራቸውን እንዲላጯቸው አደረጉ።

ሰሃቦቻቸው ይህንን ሁሉ ባዩ ጊዜ ተነስተው እርድ አረዱና እርስ በርሳቸው ተለጫጩ::[4]

የአል-ሁደይቢያህ የሰላም ስምምነት ታሪክ ባጭሩ ይህ ነው:: ሺአና ሱኒዎች በዚህ ታሪክ ዝርዝር ይስማማሉ:: ይህም ድርጊት አል-ጠበሪ፣ ኢብን አል-አሲር፣ ኢብን ሰአድ፣ አል-ቡኻሪና ሙስሊም በመሳሰሉት የታሪክ ሰዎችና የነቢዩ የህይወት ታሪክ ፀሐፊዎች በደንብ ጠቅሰዋል::

ሰሀቦች በነቢዩ ላይ ባሳዩት ፀባይ የግራሞት ስሜት ሳይሰማኝ ይህን ዓይነት ፅሁፍ ማንበብ ስለማልችል እዚሁ ላይ አቆምኩ:: ሰሀቦች አላህ (ይውደድላቸውና) ሁልጊዜም የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዛት ያከብራሉ፤ ተግባራዊም ያደርጋሉ የሚሉትን የአንዳንድ ሰዎችን አባባል ነገሮችን የሚያመዛዝን ሰው ሊቀበለው ይችላልን? እነዚህ ድርጊቶች እኮ እንደዚያ የሚያወሩትን ሰዎች ውሸቶች ያጋልጣሉ:: ዓላማዎቻቸውንም በአጭር ያስቀሩባቸዋል:: እንዲህ ዓይነት ጠባይ በነቢዩ ላይ ማሳየት ቀላልና ተቀባይነት ያለው ወይም ይቅርታ የሚደረግለት ነው ብሎ ነገሮችን የሚያገናዝብ ሰው ሊገምት ይችላልን? ሃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል::

«***በጌታህም እምላለሁ! በመካከላቸሁ በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍፁም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም (ሙእሚን አይሆኑም)***» **(ቅዱስ ቁርአን 4:65)::**

ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ እጅ ነስተው የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ትዕዛዝ ለመቀበል ምንም ችግር አላጋጠማቸውም? ወይስ የነቢዩን ትዕዛዝ ለመቀበል ፈቃደኛ አልበሩምን? በተለይ እንዲህ ባለ ጊዜ «እርስዎ በእውነት የአላህ ነቢይ

አይደሉምን? ወደ አላህ ቤት ሄደን...? አላልክም?»...ወዘተ ነቢዩ መሐመድ እነዛን ሁሉ አሳማኝ መልሶች ከሰጡአቸው በኋላ ኡመር እጅ ሰጥተው ታዘዙ? በመልሶቻቸው አላመኑባቸውም፣ እንዲያውም እነኛኑ ጥያቄዎች ሄደው አቡበከርን ጠይቀዋቸዋል፡፡ ደግሞ አቡበከር መልስ ከሰጡአቸውና በጽናትም ነቢዩን እንዲከተሉአቸው ሲመክሩዋቸው ተቀብለዋልን? በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በአቡበከር መልሶች ሁሉ አምነው ተቀብለው እንደሆነ አላውቅም፡፡ ደግሞስ ለምንድን ነው፤ ስለራሳቸው እንዲህ ያሉት «ለዚያ ብዙ ነገሮች አድርጌአለሁ...» በዑመር የተደረጉትን ነገሮች አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ፡፡

ከዚያም በላይ የአላህ መልዕክተኛ «ሂዱና እርድ እረዱና (መስዋዕቶች) ፀጉራችሁንም ተላጩ» ሲሉዋቸው ሰሀቦቹ ፈቃደኞች ሊሆኑ ያልቻሉበት ምክንያት አይገባኝም፡፡ ይህን ትዕዛዝ ሦስት ጊዜ ቢደጋግሙት ማንም የሰማቸው አልነበረም፡፡

ሱብሀነላህ! ያነበብኩትን ላምን አልቻልኩም፡፡ ሰሀቦቹ እስከዚህ መልዕክተኛ ውን አሻፈረኝ እስከማለት ደርሰው ነበር፡፡ ይህ ታሪክ በሺአዎች ብቻ የተነገረ ነው ብዬ እወስደው ነበር፡፡ ግና ታሪኩ በጣም የተስፋፋ ሆኖ የሱኒ የታሪክ ሰዎችም ይጠቅሱታል፡፡ በሁለቱም ወገኖች ስምምነት ላይ የተደረገበትን ለመቀበል የወሰንኩ ስለሆነ የተምታታ ሁኔታ ውስጥ ገብቼ ሳላንገራግር ለመቀበል ተገደድኩ፡፡ ምንስ ማለት ይቻለኝ ነበር? ተልዕኮው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ አል-ሁደይቢያ ዕለት ድረስ ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሃያ ዓመታት አብረው ስለቆዩትና የነብይነቱን ተዓምራትና ትምህርቶች ሁሉ በሚገባ ስለተመለከቱት ለእነዚያ ሰሀቦች ምን ዓይነት ማስተባበያ ላገኝላቸው እችላለሁ? ከዚያም በላይ ደግሞ ከመልዕክተኛው ፊት ምን ዓይነት ባህሪ

ማሳየት እንዳለባቸው እንዴትስ ማናገር እንደሚገባቸው ድምፃቸውን ከእሳቸው ድምጽ በላይ ከፍ አድርገው ከተናገሩ እንኳ የሰሩትን ሥራ ሁሉ ውድቅ እንደሚያደርገው አላህ ማስጠንቀቁንም ቁርአኑ ቀን ተሌት አስተምሮአቸዋል፡፡

## 2. ሰሀቦቹና ራዚያት የውም አል-ኸሚስ (የሀሙሱ አሳዛኝ ገጠመኝ)

ታሪኩ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው

ከህልፈታቸው ሦስት ቀናት በፊት ሰሀቦቹ ከመልዕክተኛው ቤት ተሰብስበው ነበር፡፡ እሳቸውም ከትክክለኛው መንገድ እንዳይወጡ የሚያደርጋቸውን መሪ ቃላቸውን በጽሁፍ ሊያስቀምጡላቸው ፈልገው መጣፊያና ማጥቀሻ ቀለም እንዲቀርብላቸው አዘዙ፡፡ ሰሀቦቹ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ተከፋፈሉ፡፡ አንዳዶቹ እንዲያውም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከመቃወማቸውም በላይ «የማይረባ ነገር ይናገራሉ» በማለት ወነጀሉአቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጅግ ተናደው መልዕክቱ ሳይጻፍ ሰሀቦቻቸውን ከቤታቸው አስወጧቸው፡፡

ታሪኩን በጥቂቱ እንዲህ ዘርዘር ላድርገው፡- ኢብን አባስ እንዲህ ብለዋል፡፡ ያቺ የሐሙስ ቀን! ምን ዓይነት ቀን ነበረች?! የነቢዩ ስቃይ በጣም በበረታባቸው ጊዜ እንዲህ አሉ፡፡ «ወደዚህ ቅረቡ ከትክክለኛው መንገድ እንዳትወጡ የሚያደርጋችሁን ሰነድ እጽፍላችኋለሁ» ዑመር ግን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን የተናገሩት በሽታው ሰለጠናባቸውና (የሚሉትን ስለማያውቁ) ነው፡፡ የአላህ ኪታብ በቂያችን ስለሆነ (የሚጻፍ ነገር) አያስፈልግም ብሎ ተናገረ፡፡ ከዚያም በቤትውስጥ የነበሩ ሰዎች በሀሳብ ተለያዩና እርስ

በርሳቸው ተጣሉ፡፡ አንዳንዶቹ ነቢዩ በተናገሩት ሲስማሙ ሌሎቹ ደግሞ የኡመርን ሀሳብ ደገፉ፡፡ ክርክሩም እየጋለ ሲሄድና ጩኸቱም እየጨመረ ሲመጣ የአላህ መልዕክተኛ «ለብቻዬ ተውኝ» አሉዋቸው፡፡ ኢብን አባስ እንዲህ ብለዋል «የሰሀቦች አለመግባባት ያደረሰው ትልቅ ጥፋት መልእክተኛ ው ሰነዱን እንዳይጽፉላቸው ማድረጉ ነበር፡፡»[5]

የዚህ ድርጊት መፈጸሙ ትክክለኛና የማያጠራጥር ነው፡፡ ምክንያቱም የሺአ ምሁራንና የታሪክ ሰዎችም ሆኑ የሱኒ ምሁራንና የታሪክ ሰዎቻቸው በየመፃህፍታቸው ጠቅሰውታል፡፡ ይህን ሁኔታ ጠለቅ ብዬ ለመመልከት ወስኜ ስለነበር የአላህ መልዕክተኛን ትዕዛዝ አስመልክቶ ዑመር ባሳዩት ባህሪ ግራ ተጋባሁ «ህዝቡ ከትክክለኛ መንገድ እንዳይወጣ ለማድረግ» ምንኛ ድንቅ ትዕዛዝ ነበር! ያ ሰነድ ለሙስሊሞች አዲስ ነገር የያዘና ከማንኛውም ጥርጣሬ ነፃ ያደርጋቸው እንደነበረ አያጠራጥርም፡፡

መልዕክተኛው ወራሻቸው አድርገው የአሊን ስም ሊጽፉ ፈልገው ነበር፡፡ ዑመርም ይህንን ስለተረዱት ነገሩን አከሸፉት የሚለውን የሺአዎችን አስተያየት አሁን እዚህ ላይ እንተወው፡፡ ምናልባት መጀመሪያ በዚህ መላምት አያሳምኑም፡፡ ግና ድንጋዮች በእንባቸው እስኪርሱ ድረስ ኢብን አባስን ያስለቀሳቸውና «ታላቁ ጥፋት» ብለው ለጠሩትና መልዕክተኛውንም እጅግ አስቆጥቶ ሰሀቦቹን ከአጠገባቸው እንዲወጡ ብለው እስከማዘዝ ያበቃቸው ይህ አሳዛኝ ክስተት በሚያሳምን መንገድ እንዲህ ሊሆን ነበር ብለን የምናቀርበው ነገር ሊኖር ይችል ይሆን? ሱኒዎች የነቢዩ ህመም እየበረታ መምጣቱን ዑመር በመገንዘባቸው ሊያፅናኑዋቸውና ምንም ዓይነት ጫና እንዳይፈጠርባቸው ፈልገው ነው እንደዛ ያደረጉት ይላሉ፡፡

እንዲህ ዓይነት ሀሳብ እንኳን በምሁራን ቀርቶ ባልተማሩ ሰዎችም ተቀባይነት አያገኝም። ዑመር ለወሰዱት እርምጃ ምክንያት ለማግኘት ተደጋጋሚ ጥረት ባደርግም በዚያ ምሽት ክስተት ዙሪያ የነበሩት ሁኔታዎች ምንም ዓይነት ምክንያት እንዳላገኝ አግደውኛል። ምንም እንኳ «የሀጁሩ» (በቅዠት ነው የሚናገሩት) የሚለው አባባል «ስቃዩ በርትቶባቸዋል» በሚለው ቢተካም ዑመር «ቁርዓን አለላችሁ፣ የአላህ መጽሀፍ በመሆኑም እሱ በቂ ነው» ብለው ለተናገሩት ምንም የትክክለኛነት ማረጋገጫ ላገኝበት አልቻልኩም። ቁርዓኑ ከወረደላቸው ከአላህ መልዕክተኛ ይበልጥ ዑመር ቁርዓኑን ያውቁት ነበር? ወይስ የአላህ መልዕክተኛ እራሳቸው ምን እንደነበሩ ማወቅ ተስኖአቸው ነበርን? ወይስ በሚያስተላልፉት ትዕዛዝ በሰሀቦች መካከል አለመግባባትና ክፍፍል ለመፍጠር ፈለጉ? (አላህ ከዚህ ሁሉ አስተሳሰብ ይሰውረን) ሱኒዎች የሚያቀርቡት ምክንያት ትክክል ቢሆን እንኳ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ተቆጥተው ከቤቴ ውጡልኝ ከሚሉ ዑመር ለእሳቸው ጥሩ ማሰባቸውን ተገንዝበው ለዚህም አመስግነዋቸው እዚያው እንዲቆዩ ባደረጉዋቸው ነበር። እስቲ ይህን ልጠይቃችሁ! ውጡልኝ ብለው ሲያዙዋቸው ተነስተው ከመውጣት ለምን «የማይረባ ነገር ነው የሚናገሩት» ብለው ባሉት አልቆዩም? ወይስ ነቢዩ ሰነዱን እንዳይጽፉት የሸረቡት ሴራ በመሳካቱ የእነሱ እዚያ መቆየት አስፈላጊ ሰላልነበረ ይሆን? ስለሆነም በሁለት ወገን ተከፋፍለው አንዱ የአላህ መልዕክተኛ ሰነዱን ለመፃፋቸው ሲስማማ ሌላው ደግሞ የማይረባ ነገር ነው የሚናገሩት ባሉት ዑመር በመስማማት ጩኸትና አለመግባባት ፈጥረው እናገኛቸዋለን።

ነገሩ የሚመለከተው ዑመርን ብቻ ቢሆን ኖሮ የአላህ መልዕክተኛ የሚናገሩት የማይረባ ነገር አለመሆኑንና ህዝቡ መመሪያና መንገዱን

እንዳይስት በማድረጉ ቁም ነገር ላይ ስቃዩ የማያግዳቸው መሆኑን ዑመርን ባሳመናቸው ነበር:: ሁኔታው ግን በጣም አሳሳቢ ሆኖ መጣ:: ዑመር ቀደም ብለው በአቋም የተስማሙ የሚያስመስላቸው ደጋፊዎች አግኝተው የሃያሉን አላህ ቃላት ረስተው ወይም የረሱ አስመስለው በመካከላቸው ጨኸትንና አለመግባባትን ፈጠሩ:: «*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ድምጻቻችሁን ከነቢዩ ድምጽ በላይ ከፍ አታድርጉ፣ ከፊላችሁም ለከፊሉ እንደሚጮህ በንግግር ለርሱ አትጩሁ:: እናንተ የማታውቁ ስትሆኑ ሥራዎቻችሁ እንዳይበላሹ (ተከልክሉ)::*» (ቅዱስ ቁርዓንን 49:2)

በዚህ ክስተት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ከመናገራቸው ባሻገር አልፈው (የማይረባ ነገር ይናገራሉ) ብለው የአላህን መልዕክተኛ ወነጀሉአቸው:: ቀጥለውም በእሳቸው ፊት የቃላት ጦርነት እስኪነሳ ድረስ ድምጻቸውንና ልዩነታቸውን እያሳደጉ ሄዱ::

አብዛኞቹ ሰሀቦች ከዑመር ጋራ ያበሩ ይመስለኛል:: ለዚህም ነው የአላህ መልእክተኛ ሰነዱን መፃፍ ጥቅመ-ቢስ ሆኖ ያገኙት:: የእሳቸውን ትዕዛዝ እንደማያከብሩና በእሳቸውም ፊት ድምፃቸውን ከፍ አድረገው እንደማይናገሩ ያዘዘውን የአላህን ቃል መጣሳቸውን ተገንዝበውታል:: በአላህ ትዕዛዝ ላይ ካመፁም የእሱን መልዕክተኛ ትዕዛዝም በፍፁም አያከብሩም:: ስለሆነም እንኳን ከህልፈታቸው በኋላ ቀርቶ በህይወትም እያሉ ይህን ያህል ተቃውሞ የተነሳበትን ሰነድ ላለመፃፍ የመልዕክተኛው ጥበባዊ ውሳኔ ነበር::

ነገሩን ለመቀልበስ ያሰቡ ሰዎች ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) «የማይረባ ነገር ነው የተናገሩት» ስላሉ ምናልባትም በህመም ውስጥ ሆነው ያስተላለፉትን ትዕዛዛት በጥርጣሬ ይመለከታሉ ማለት ነው:: ምክንያቱም በዛን ወቅት በዛ

ሁኔታ የሚናገሩት ነገር «ቅዠትና ትርጉም የማይሰጠው ነገር» ነው ብለው ስለሚያስቡ።

አላህን ይቅርታ እጠይቃለሁ፤ በቅዱስ መልዕክተኛም ፊት የተናገሩትን ሁሉ አወግዛለሁ። በአንድ በኩል በቦታው የነበሩ ሰሃቦቻቸውና ሌሎቹም እንባቸው ድንጋይ እስኪያረጥብ ድረስ ሲያነቡና ድርጊቱንም «የሙስሊሞች ክፉ ዕጣ» ብለው ሲሰይሙት፣ ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ ይህን ድርጊት የፈፀሙት በግብዓታዊነት ነው ብዬ እንዴት ነው አእምሮዬን የማሳምነው?

ይህን ድርጊት ለማስረዳት የቀረቡትን ምክንያቶች ሁሉ ውድቅ አድረጌ እንዲያውም ከነአካቴው መፈፀሙን ክጄ ያን አሳዛኝ ሁኔታ በመርሳት እፎይ ለማለት ወሰንኩ። ግና ሁሉም መፃህፍት ይጠቅሱታል። እውነት መሆኑንም ይቀበሉታል። ይሁንና ለድርጊቱ እንዲህ ነው የሚሉት ጠንካራ ማስተማመኛ ማቅረብ ተስኖአቸው ሁኔታውን አስመልክቶ ቀጥተኛና ግልጽ እንዲሁም ትክክለኛ የአስተሳሰብ ዘዴን (ሎጂክን) የተከተለ ሆኖ ስለአገኘሁት የሺአዎች አመለካከት ጋራ ወደመስማማቱ አዘነበልኩ። «ነቢዩ ሊጽፉ የፈለጉትን እናንተ እንደምትሉት አሊን ወራሽ አድርገው መሾምን ከሰሀቦቹ ሁሉ አለቃችን ዑመር እንዴት ሊረዱት ቻሉ?» ብዬ ለጠየቅኋቸው ጥያቄ አል-ሰይድ መሐመድ ባቂር አል-ሰድር የሰጡኝን መልስ አሁንም አስታውሰዋለሁ።

አል-ሰይድ አል-ሰድር እንዲህ አሉ፣ «መልዕክተኛው ሊጽፉት የፈለጉትን ነገር ቀድመው ያወቁት ዑመር ብቻ አልነበሩም። ከዚህ ቀደም የአላህ መልዕክተኛ «ሁለት ሚዛን የደፉ ነገሮችን ትቼላችሁ አልፋለሁ፣ የአላህ

መጽሐፍንና የቤተሰቤ አባላትን (አህሉል ቤይት) እና ከእነሱም የሚወለዱትን፣ እነዚህ ከተከተላችሁ ከእኔ በኋላ ከትክክለኛው መንገድ አትወጡም» በማለት ቀደም ብለው ተናግረው ስለነበር እዚያ የነበሩ አብዛኞቹ ሰዎች ሁኔታውን የተረዱት ልክ ዑመር በተረዱት መንገድ ነበር፡፡ በታመሙበትም ወቅት እንዲህ ብለዋቸው ነበር፡፡ «እስቲ አንድ መልዕክት ልጻፍላችሁ፡፡ ያንን መልዕክት ከተከተላችሁ ከኔ በኋላ ወደ ጥመትና ጥፋት ጎዳና አትገቡም፡፡»

ዐሙርን ጨምሮ እዚያ የተገኙት ሁሉ የአላህ መልዕክተኛ «በገዲር ኩም» ተናግረውት የነበረውን ማለትም የአላህን መጽሐፍና አሊ መሪ የሆኑበትን አህሉል ቤይትን እንዲከተሉ የተናገሩትን መልሰው በጽሑፍ ሊያስቀምጡት እንደፈለጉ ገብቷቸዋል፡፡ ይህም የነቢዩ አነጋገር «ቁርአንና አሊን ተከተሉ» እንደማለት ነው፡፡ በበርካታ የታሪክ ሰዎች እንደተዘገበው በብዙ አጋጣሚዎች ተመሳሳይ ነገሮችን ተናግረዋል፡፡ በወቅቱ አብዛኞቹ ቁሬይሾች አሊን አይወዱትም ነበር፡፡ ምክንያቱም ዓሊ ገና ወጣት ሳለ የቁሬይሽን እብሪተኞች ያንበረከከ፣ ጀግኖቻቸውንም የገደለባቸው ሰው ስለነበረ ነው፡፡ ቢሆንም ግን በሁዴቢያህ ስምምነት ወቅት፣ ለአብደላህ ኢብን አል-ሙናፊቅ ዱዓዕ ባደረጉ ጊዜና በሌሎችም ቦታዎች ላይ እንዳደረጉ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመቃወም አልደፈሩም፡፡

ነቢዩ በታመሙበት ወቅት በሰነዱ መፃፍ ላይ የተነሳው ተቃውሞ እዚያ የነበሩት አንዳንድ ሰዎችን እንዲባልጉና በእሳቸው ፊትም አተካሮ እንዲፈጥሩ ገፋፍቷቸዋል፡፡ ያ መልስም የመጣው አባባሉ ሊያስተላልፍ ከፈለገው መልዕክት አኳያ ነበር፡፡ «ቁርአን አለላችሁ የአላህ መጽሐፍ በመሆኑም እሱ

በቂ ነው» ብለው ዑመር የተናገሩት ግን የአላህን መጽሐፍ የመልዕክተኛ ውን ቤተሰብ (አህሉል ቤይት) እንዲከተሉ ካዘዙአቸው አባባል አኳያ በታሪክ ከተዘገቡት ክስተቶች አንዱ ይህ ጉዳይ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመጻፍ ያሰቡትን መልዕክት መቃወሙ በቦታው የነበሩ አንዳንድ ሰዎችን እንዳስገረመና በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጠገብ ሁከት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ የተሰጠው ምላሽ የጥያቄውን ምንነት ያገናዘበ ነበር፡፡ ነገር ግን «ቁርአን አለላችሁ፡፡ የአላህ መጽሀፍ በመሆኑ እሱ በቂያችን ነው» የሚለው የዑመር አባባል ግን የአላህን መጽሀፍና አህሉል በይትን ተከተሉ የሚለውን ትዕዛዝ ያገናዘበ አይደለም፡፡ የዑመር አነጋገር የሚከተለውን ትርጉም ለመስጠት የታለመ ይመስላል «የአላህ መጽሐፍ አለን፡፡ ለእኛ እሱ ብቻ በቂ ነው፡፡ ስለሆነም አህሉል ቤይት አስፈላጊ አይደለም» የሚል ይመስላል፡፡ ለዚህ ክስተት ደግሞ «ለአላህ ታዘዙ፣ ለመልዕክተኛው አትታዘዙ» ለማለት ተፈልጎ ካልሆነ በስተቀር ሌላ የተለየ ገለጻ መስጠት አልቻልኩም፡፡ ይህም አስተሳሰብ ደግሞ ዋጋ-ቢስና ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ ቀደም ሲል የተቀረፀብኝን ጥላቻዎችና ስሜቶች ወደ ጎን ትቼ ፍርዱን በንፁህ እና ነፃ አእምሮ ላይ በመመስረት ብወስን «የአላህ መጽሐፍ በመሆኑ እሱ ለእኛ በቂያችን ነው» ባሉ ጊዜ ዑመር የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና በመቃወም ከመወቀስ የማይድን የመጀመሪያው ሰው ነው ወደሚለው አዝማሚያ ሳላዘነብል አልቀርም፡፡

ይቃረናሉ በሚል ምክንያት የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና አንቀበልም ያሉ አንዳንድ መሪዎች ኖረውም ከሆነ ከቀደምት የእስልምና ታሪክ ባገኙት ምሳሌ ላይ ተመርኩዘው ነበር ለማለት ያስደፍራል ማለት ነው፡፡ ሆኖም ግን

ለተከሰተው ሁኔታና በህዝቡ ላይም ለደረሰው ውርደት ጥፋቱን በዑመር ላይ ብቻ ለመጫን አልፈልግም፡፡ ሃላፊነቱ በእሳቸውና በአላህ መልዕክተኛ ትዕዛዝ ላይ በተነሳው ተቃውሞ አብረዋቸው በነበሩትና ድጋፍ በሰጡዋቸው ሰሀቦች ላይም መውደቅ አለበት እላለሁ፡፡

«ታላቁ አሳዛኝ እጣ» ብለው ኢብን አባስ የሰየሙት ይህን ድርጊት ሰዎች አንብበው ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ሆኖ ሲሰማቸው እጅግ ይገርመኛል፡፡ ይባስ ብለው የነቢዩን ክብርና ማዕረግ እንዲሁም የእስልምናን መሰረቶች አደጋ ላይ ጥለውም ቢሆን የአንድን ሰሀባ ክብር ለመጠበቅና ስህተቱንም ለማረም በሚጥሩት ላይ እጅግ እገረማለሁ፡፡

ከእኛ የልብ ትርታ (ስሜት) ጋራ አብሮ ካልሄደ ብለን ለምንድን ነው ከእውነቱ አምልጠን ልናድበሰብሰው የምንሞክረው? ለምንስ ነው ሰሀቦቹን እንደኛ ሰዎች እንደነበሩ የራሳቸው የልብ ትርታ ጥላቻና ፍላጎት እንዳላቸውና ስህተቶች ሊሰሩ እንደሚችሉ ብሎም ትክክል ሊሆኑም ላይሆኑም እንደሚችሉ የማንቀበለው? ሆኖም የነብያትን ታሪክና ከህዝቦቻቸው የደረሰባቸውን ተቃውሞ ከቁርዓን ሳነብ አግራምቴ ሁሉ ቀነሰ፡፡ ነብያቱ በርካታ ተዓምራትን ለህዝቦቻቸው ቢያሳዩም ከህዝቡ ተቃውሞና አልታዘዝ ባይነት ለመትረፍ አልቻሉም ነበር፡፡

አምላካችን ሆይ! ቅኑን መንገድ ከመራኸን በኋላ ልቦቻችን ወደ ጥመት ከማዘንበል ጠብቀን፡፡ በምህረትህ አስበን፡፡ አንተ ወደር የለሽ ቸርና ለጋስ ነህና፡፡

እስላማዊው ህዝብ መልዕክተኛው ሊጽፉለት የፈለጉትን ሰነድ ከአጣበት ከ«ራዚያት የውም አል-ኸሚስ» ጀምሮ በእስልምና ታሪክ ውስጥ ለበርካታ አሳዛኝ ድርጊቶች በሃላፊነት ሊከሷቸው ለነበረው ለሁለተኛው ኻሊፍ ሺአዎች ያላቸውን አመለካከት መገንዘብ ጀመርኩ፡፡ የማይካደው ሀቅ ግን ሰዎችን ከማግኘቱ በፊት እውነቱን ያወቀ የሚያገናዝብ ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ ሺአዎች እውነት እንዳላቸው ይገነዘባል፡፡ ነገር ግን ሐቅን በሐቅነቱ ሳይሆን በሰዎች ላይ ተመርኩዘው ፍርድ የሚሰጡትን ሰዎች ለማሳመን የምናደርገው ነገር ሊኖር አይችልም፡፡

## 3. የኡሳማህ በጦር መሪነት መሾምና የሰሀቦቹ ሁኔታ

ታሪኩ በአጭሩ እንደሚከተለው ነው

ከህልፈታቸው ሁለት ቀናት በፊት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሮም የሚዘምት ሰራዊት አደራጁ፡፡ ሁሳማህ ኢብን ዛይድ ኢብን ሃሪሳህ (የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ነበር) የሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ አድርገው በመሾም ከመሀጅሮችም ሆነ ከአንሷሮች እንደ አቡበክር፣ ዑመር፣ አቡ ኡበይዳህና ሌሎች ዕውቅ ሰሀቦችን ያካተተ ሠራዊት እንዲመራ አደረጉ፡፡ ኡሳማህን የሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ አድርገው በመሾማቸው አንዳንድ ሰዎች ነቢዩን ተቹአቸው፡፡ እንዲህ በጣም ወጣት የሆነ ልጅ የእነሱ አዛዥ አድርገው እንዴት እንደሾሙም ጠየቁ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እኒሁ ሰዎች ከዚህ በፊት የኡሳማህን አባት የሠራዊቱ አዛዥ አድርገው ነቢዩ መሾማቸው እንዲሁ ተችተዋቸው ነበር፡፡ በትችታቸው በገፉበት ጊዜ ነቢዩ እጅግ ተናደው ሁለት ሰዎች ተሸክመዋቸውና ጭንቅላታቸውን ግጥም አድርገው አስረው እየተንቀጠቀጡ ከአልጋቸው ላይ ተነሱ፡፡ ምንበር ላይ ወጥተው አላህን

እጅግ ካመሰገኑ በኋላ እንዲህ አሉ፡፡ «ሰዎች ሆይ! ኡሳማን የሰራዊቱ አዛዥ አድርጌ በመሾሜ አንዳንዶቻችሁ እንደተቃወማችሁ ተነግሮኛል፡፡ ከዚህ በፊት አባቱን የሠራዊቱ ጠቅላይ አዛዥ አድርጌ ስሾም እንደተቃወማችሁኝ ሁሉ አሁን ኡሳማህን ጠቅላይ አዛዥ አድርጌ በመሾሜ ተቃወማችሁኝ፡፡ በአላህ እምላለሁ ለጠቅላይ አዛዥነት ሹመት በእርግጥ ብቁ ነበር፡፡ ልጁም ለሹመቱ እንዲሁ ብቁ ነው»[6] ከዚያም ካለ ምንም መዘግየት እንቅስቃሴ እንዲጀምሩ አጥብቀው ተናገሩዋቸውና «የኡሳማህን ሰራዊት ላኩ፡፡ የኡሳማህን ሰራዊት አሳልፉ፣ የኡሳማህን ሰራዊት ወደፊት እንዲገሰግስ አድርጉ» እያሉ በመደጋገም መናገር ቀጠሉ፡፡ ይህን ጉትጎታቸውን ቢቀጥሉም ሰሀቦች እጅግ ዝግ እያሉና እየተጎተቱ ስለነበር በአል-ጁርፍ ካምፕ ሰሩ፡፡ እንደዚያ አይነት ክንዋኔዎች ጥያቄዎችን እንዳነሳ ያደርጉኛል፡፡ «እንደዚህ ዓይነት ብልግና በአላህና በመልዕክተኛው ላይ ምንድን ነው? ለሁሉም አማኞች ደግና ተንከባካቢ በነበሩት የተባረኩ መልዕክተኛ ትዕዛዝ ላይ ይህ ሁሉ አሻፈረኝ ባይነት ለምንድን ነው?»

ለዚያ ሁሉ አሻፈረኝ ባይነትና ብልግና እንዲህ ነው የሚባል ተቀባይነት ያለው ምክንያት ይቀርባል ብሎ እኔም ሆንኩ ማንም ሰው ሊገምት አይችልም፡፡ እንደተለመደው እኒያን ድርጊቶች አስመልክቶ የሰሀቦቹን ሀቀኝነት የሚዳስስ ነገር ሳነብ እንዲህ አልተፈፀመም በማለት ወይም ቶሎ ብዬ ለማለፍ እሞክራለሁ፡፡ ሆኖም ግን የሱኒም የሺአም ታሪክ ሰዎችና ምሁራን በእውነተኛነቱ ስለሚሰማሙ እንዲህ አድርጎ ማለፉ አይቻልም፡፡

ሚዛናዊ ለመሆን ለአምላክ ቃል ገብቻለሁ፡፡ ለአስተሳሰቤ በማድላት የልብ ትርታዬን ብቻ ላልሰማ ቆረጥኩ፡፡ እንደ መስፈርት እውነትን ብቻ ልጠቀም ወሰንኩ፡፡ ነገር ግን እውነት በጣም መራራ እንደሆነች አውቃለሁ፡፡ ነቢይም

እንዲህ ብለዋል «እራሳችሁን በሚመለከትም እንኳ ቢሆን እውነትን ተናገሩ፣ መራራ እንኳ ቢሆን እውነትን ተናገሩ . . .»

በዚህ ጉዳይ ላይ እውነቱ እንግዲህ የኡሳማህን ሹመት የተቹት ሰሀቦች ሊጠረጠርና የተሳሳተ ትርጓሜ ሊሰጠው የማይችለውን ግልጹን መጽሀፍ (ትዕዛዝ) አለመታዘዛቸው ነው። ምንም እንኳ አንዳንድ ሰዎች የሰሀቦችን ሀቀኝነትና «የአባቶችን ክብር» ለመጠበቅ ሲሉ ደካማ ምክንያቶችን ቢያቀርቡም ድርጊቱ ግን ምንም ይቅርታ የማይደረግለት ነው። ምንም የማይገባው ደንቆሮ ወይም ባደረበት ጥላቻ ዓይኑ ተሸፍኖ መፈጸም ያለባቸውን ግዴታዊ ተግባሮችና ልናስወግዳቸው ከሚገባን የተከለከሉ ነገሮች መለየት የተሳነው ካልሆነ በስተቀር ነፃና አመዛዛኝ የሆነ ሰው እነዚህን ደካማ ምክንያቶች አይቀበልም።

ለነዚህ ሰዎች ተቀባይነት ያለው ምክንያት ለማግኘት እጅግ ብጥርም ሊሳካልኝ አልቻለም። ነገሩን ለማርገብና ምክንያታዊ እንዲመስል ለማድረግ የሱኒዎችን አስተሳሰብ የሚያንጸባርቁ መጽሀፍትን አንብቤአለሁ። ይኸውም አብዛኞቹ ሰዎች የቁሬይሽ ታላላቅ ሰዎችና ወደ እስልምና ቀድመው የገቡ አንጋፎች ሲሆኑ ኡሳማ ግን በበድር፣ በኡሁድ፣ በሁነይንና በመሳሰሉት ወሳኝ የነበሩ ዘመቻዎች ያልተሳተፈ ለጋ ወጣት ስለነበረ በወቅቱ ብዙም የህይወት ተሞክሮ ስላልነበረውና በተፈጥሮ ደግሞ ትላልቅ ሰዎች በልጅ የመመራት ነገር የማይዋጥላቸው ጉዳይ በመሆኑ ነው በማለት ብዙ ምክንያቶች ተዘርዝረዋል። ሰሀቦች ሹመቱን ተችተው የአላህ መልዕክተኛ ታዋቂና የተከበረ ሰሀባ እንዲሾሙ የፈለጉት ለዚህም ነው ይላሉ።

ይህም ሳይንሳዊ ባልሆነ የአስተሳሰብ አቅጣጫ ላይ የተመሰረተ ምክንያት ነው፡፡ ቁርዓንን ያነበበና ህግጋቱንም የተረዳ ማንኛውም ሙስሊም እንዲህ ዓይነቱን ምክንያት ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡ ምክንያቱም ሃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

«***መልዕክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት፣ ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ***» (ቅዱስ ቁርአን 59:7) «***አላህና መልዕክተኛ ውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምዕምናት ከነገሯቸው ከእነሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም፡፡ የአላህንና የመልዕክተኛውንም ትዕዛዝ የጣሰ ሰው ግልጥ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ***» **(ቅዱስ ቁርአን 33:36)**

ጤናማ አእምሮ ያለው ሰው እነዚህን ሁሉ ግልጽ አንቀፆች ካነበበ በኋላ ምን ዓይነት ምክንያት ነው ሊቀበል የሚችለው? የመልዕክተኛው ቁጣ የአላህ ቁጣ መሆኑን እያወቁ የአላህን መልዕክተኛ ስላስቆጡ ሰዎችስ ምን ማለት እችላለሁ? ውጡልኝ ብለው እስኪያዙዋቸው ድረስ «የማይረባ ነገር ተናገሩ» ብለው ወነጀሉዋቸው፡፡ ታመው እያሉም (ወላጆቼ ለእሳቸው መስዋዕት ይሁንና) ፊታቸው ላይ እየጮሁ ተሟገቱ፡፡ ያም ለእነሱ በቂ ሆኖ አልታያቸውም፡፡ ወደ ትክክለኛው መንገድ ተመልሰው መልዕክተኛው ላይ በሰሩት ሥራ የአላህን ይቅርታ ከመጠየቅ ብሎም ቁርዓኑ እንዳስተማራቸው መልዕክተኛውን ይቅርታ ከመጠየቅ ለእነሱ የነበራቸውን ደግነትና ክብካቤ ዘንግተው መልዕክተኛውን መተቸታቸውን ቀጠሉ፡፡ ለመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) አድናቆትና አክብሮት አልነበራቸውም ማለት ነው፡፡ «የማይረባ ነገር ተናግረዋል» ብለው ከወነጀሉዋው ከሁለት ቀናት በኋላም ኡሳማህን የሠራዊቱ አዛዥ አድርገው በመሾማቸው እንዲሁ ትችት አወረዱባቸው፡፡ የታሪክ ፀሐፊዎች በዘገቡት አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ከታመሙበት ተነስተው እንዲወጡ አስገደዱዋቸው፡፡ ህመማቸው ከፍተኛ ስለነበረም

በሁለት ሰዎች ተደግፈው ነበር የሚራመዱት። በእንዲህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው በአላህ እየማሉ ኡሳማህ ለሰራዊቱ ብቁ አዛዥ መሆኑን ተናገሩ። በተጨማሪም አባቱን አዛዥ አድርገው በመሾማቸው ከዚህ በፊት ተችተዋቸው እንደነበረ መልዕክተኛው ነግረውናል። ይህም የሚያሳየው እነዚህ ሰዎች ከእሳቸው ጋር ብዙ ጊዜ ተጋፍጠው እንደነበርና ትዕዛዛቸውን ለማክበር ወይም ውሳኔአቸውን ለመቀበል ፈቃደኞች አለመሆናቸውን ነው። ይልቁንም እንዲህ ዓይነቱ ባህሪ ከአላህና መልዕክተኛ ህግጋት ጋር የሚጋጩ ቢሆኑም ሰሀቦቹ ግን ህግጋቱን ለመጋፈጥ ዝግጁ ነበሩ።

ግልጽ የሆነ ተቃውሞ መኖሩን እንድናምን የሚያስገድደን ይህን ያህል ቁጣ ከአላህ መልዕክተኛ እየታየ እራሳቸው በከበረው እጃቸው ባንዲራውን መስቀያው ላይ አስረው ወዲያውኑ እንዲዘምቱ እያዘዙ ሰሀቦቹ እየተንቀራፈፉ ለመንቀሳቀስ አለመፈለጋቸውና ወደፊት መሄድም የጀመሩት እሳቸው ከሞቱ (ወላጆቼ ለእሳቸው መስዋዕት ይሁንና) በኋላ በመሆኑ ነው። ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡ ወደ ኃላ ተመልሶ፣ ከጥቂቶች በስተቀር ወይም እንደ መልዕክተኛው አገላለጽ በጣት ከሚቆጠሩት በስተቀር መጨረሻው ጀሀነም ይሆናል ብለው ለፈሩለት ዕድለ ቢስ ህዝብ እያዘኑ አለፉ።

«***በላቸው! አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋልና***» **(ቅዱስ ቁርአን 3:31)**

ቁርአኑ እንዲህ እያለ በዚያች ሀሙስ ቀን እነዚያ ሰሀቦች ነቢዩን በማስቆጣታቸውና «የማይረባ» ነገር ይናገራሉ፣ «የአላህ ቁርአን በቂያችን ነው» በማለት በመወንጀላቸው ተገረምኩ። ስለአላህ መጽሐፍና ህግጋቱ ከወረደላቸው በላይ አዋቂ እንደመሆን አደረጋቸው። ከዚያች አሳዛኝ እለት ሁለት ቀናት በኋላና እሳቸው (ቅዱሱ ነቢይ) ከሀያሉ አላህ ጋራ ለመገናኘት

ከመሄዳቸው ሁለት ቀናት በፊት አሁንም ትዕዛዛቸውን ባለማክበር ኡሳማህን በመሾማቸው ተችተዋቸው ይብሱኑ አስቆጡዋቸው፡፡ በመጀመሪያ አሳዛኝ ዕለት ታመው የአልጋ ቁራኛ እንደነበሩ ሲሆን በሁለተኛው ግን እራሳቸው ታሽገና እግራቸው ሙሉ ለሙሉ መሬት ሳይነካ ሁለት ሰዎች ደግፈዋቸውና ብርድ ልብስ ለብሰው ለመነሳት ተገደዱ፡፡ ከዚያም ምንበር ላይ ወጥተው ንግግር አደረጉ፡፡ የአላህን አንድነትና ሃያልነትን በማውሳትና ውዳሴ በመደርደር፣ የሚናገሩት በ «ቅዠት» እንዳልሆነ ግልጽ በሆነ መልኩ ንግግራቸውን ጀመሩ፡፡ በትዕዛዛቸው ላይ የተነሳውንም ትችት አስመልክተው የሚያውቁትን ነገሩዋቸው፡፡ አክለውም ከአራት ዓመታት በፊት እንዲሁ በእነሱ የተተቹበትን አጋጣሚ አስታወሱአቸው፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ እንግዲህ የሚናገሩት በ «ቅዠት» ነው ብለው ያስቡ ይሆን ወይስ በሽታቸው ጠንቶባቸው የሚናገሩትን አያውቁም ይሉ ይሆን?

አላህ ሆይ! ክብርና ምስጋና ለአንተ ይሁን፡፡ እኒህ ሰዎች የአንተን መልዕክተኛ እንዴት ደፍረው ይቃወሙዋቸዋል? ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሰላም ስምምነቱን ሲፈርሙ ሰሀቦቹ ተቃውሙአቸው፣ የመስዋዕት አርድ እንዲያርዱና ጸጉራቸውን እንዲላጩ በተደጋጋሚ የተነገራቸው ጊዜም አሻፈረኝ ብለው ነበር፡፡ ለአብደላህ ኢብን ኡበይ ዱዓዕ ሊያደርጉ ሲሉም ሸሚዛቸውን በመጎተት «አላህ ለሙናፊቆች ከመስገድ ከልክሎሀል» ብለው አቋረጡአቸው፡፡ አንተ ግን በቁርአንህ እንዲህ ብለሀል፡-

«***በግልጽ ማስረጃዎችና በመፃህፍት (ላክናቸው) ወደ አንተም ለሰዎች ወደነሱ የተወረደውን (ፍቺ) ልትገልፅላቸውና ያስተነትኑትም ዘንድ ቁርዓንን አወረድን***» **(ቅዱስ ቁርዓን 16:44)**

እንዲህም ብለሃል «*እኛ በሰዎች መካከል አላህ ባሳወቀህ ልትፈርድ ወደ አንተ መጽሐፉን በእውነት አወረድን። ለከዳተኞችም ተከራካሪ አትሁን*» **(ቅዱስ ቁርዓን 4:105)**

እንዲህም ብለሃል አባባልህም እውነት ነው። «*በውስጣችሁ ከእናንተው የሆነን በናንተ ላይ አንቀፆች የሚያነብላችሁና የሚያጠሯችሁ መፅሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራችሁ ታውቁት ያልነበራችሁትንም ነገር የሚያሳውቃችሁ የሆነን መልዕክተኛ እንደላክን (ፀጋን ሞላንላችሁ)*» **(ቅዱስ ቁርዓን 2:151)**

ከነቢዩ በላይ እራሳቸውን ከፍተኛ ቦታ ያስቀመጡት ሰዎች ይገርሙኛል። በአንድ ወቅት ትዕዛዛቸውን ጣሱ። በሌላ ጊዜ በቅዠት ነው የሚናገሩት ብለው ወነጀሉአቸው። ከዚያም በእሳቸው ፊት ሳያከብሩአቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተናገሩ። ዘይድ ኢብን ሃሪስን ለሰራዊት አዛዥነት ቀጥሎም ልጃቸው ኡሳማህን በመሾማቸው ተቹዋቸው። በአንዳንዶቹ ሰሀቦች ሁኔታ ላይ ጥያቄ ማስቀመጣቸው ለመልዕክተኛውና ለቤተሰብ አባሎቻቸው ባላቸው አክብሮትና ፍቅርም የተነሳ በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ ጥላቻ ማሳየታቸው ሺአዎች ትክክል ናቸው።

አጠር ለማድረግና ለምሳሌነት ለመጠቀም ስል አራት ወይም አምስቱን አጨቃጫቂ ነጥቦች ብቻ ጠቅሼአለሁ። የሺአ ምሁራን ግን ሰሃቦች ግልጽ የሆኑትን ትምህርቶች የተቃወሙበትን ወይም የተቃረኑበትን በመቶ የሚቆጠሩ ሁኔታዎችን መጥቀስ ይችላሉ። ሺአዎች ይህን ሲያደርጉ በምንጭነት የሚጠቀሱት በሱኒ ምሁራን የተፃፉ መፃህፍትን ነው።

የአላህን መልዕክተኛ በተመለከተ አንዳንድ ሰሀቦች ያላቸውን አመለካከት ሳይ በጣም ይገርመኛል፡፡ በጣም የሚገርመኝ ግን የሰሀቦቹ አቋም ብቻ ሳይሆን ሰሀቦች ምንጊዜም ትክክልና መተቸት የሌለባቸው ጻድቅ ናቸው የሚለውን እምነት የቀረጹብንን የሱኒ ምሁራን አቋም ነው፡፡ በዚህም ሌላው ጥናት እንዳያደርግ፣ ተመራምሮ እውነቱ ላይ እንዳይደርስ በሚቃረኑና በተምታቱ ሐሳቦች እየዋዠቀ ነገሮችን አድበስብሶ እንዲያልፍ ተደርጓል፡፡

ከፍ ብዬ ከጠቀስኳቸው ምሳሌዎች በተጨማሪ የሰሀቦችን ምንነት በጣም ግልጽ በሆነ መንገድ ለማሳየትና ሺአዎችም በነሱ ላይ ያላቸውን አቋም ለመረዳት ሌሎች ምሳሌዎችን አቀርባለሁ፡፡

በአል-ቡኻሪ ሰሂህ፡ ቅጽ 4፡ ገጽ 47፡- ኪታቡል አደብ ውስጥ የሚከተለውን እናገኛለን፡፡

ሸቂቅ ከአብደላህ እንደሰማ ለአዕመሽ በነገረው መሰረት አዕመሽ እንዲህ በማለት ነግሮናል፡፡

«ከዕለታት አንድ ቀን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተለመደው የሆነ ነገር ለሰሀቦቹ በማከፋፈል ላይ ሳሉ አንድ የአንሳር ሰው ተነሳና «ይህ ክፍፍል ለአላህ ተብሎ በፍትህ የተከፋፈለ አይደለም» አለ፡፡ በዚህን ጊዜ «በኔ በኩል ይህንን ጉዳይ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እናገራለሁ» አልኩና ተነስቼ ነብዩ ጋር ሄድኩ፡፡ ከሰሀቦቻቸው ጋር ሆነው አገኙዋቸው፡፡ የሰማሁትን ነገር እያዘንኩ ነገርኳቸው፡፡ በዚህን ጊዜ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፊት ሲቀያየርና የንዴት ስሜት ሲያሳዩ አየሁ፡፡ ምነው ባልነገርኳቸው ብዬም ተቆጨሁ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡፡ «ሙሳ ከዚህ በባሰ ሁኔታ ችግር ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ግን ሁሉንም በትዕግስት አለፈው፡፡»

አል-ቡኻሪ በዚሁ መጽሐፍ «ፈገግታና ሳቅን» በተመለከተው ምዕራፍ ውስጥ አነስ ኢብን ማሊክ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ «ጠርዙ የሳሳ የናጃሪን ጀለቢያ ከለበሱት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋራ እየሄድን ነበር፡፡ ሳይታሰብ አንድ ሰው ወደ እሳቸው ተጠጋና ጀለቢያቸውን በሃይል ጎተተው፡፡ እኔም ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስመለከት በዚያ ሃይል በተሞላበት ጉተታ ምክንያት የጀለቢያቸው ጠርዝ እስከትከሻቸው ድረስ መተርተሩን ተመለከትኩ፡፡ ከዚያም ሰውየው እንዲህ አላቸው ፡፡ «መሐመድ ሆይ! በእጅዎ ካለው ከአላህ ሀብት ውስጥ ትንሽ ስጡኝ» ነቢዩ ወደ ሰውየው ዞር አሉና ፈገግ ብለው የሆነ ነገር እንዲሰጡት ሰሀቦቻቸውን አዘዙ፡፡

አል-ቡኻሪ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ «ሰዎችን በወቀሳ የማይጋፈጡ» በሚለው ክፍል ሥር ባቀረበው ሐዲስ የሚከተለውን ታሪክ እናገኛለን፡፡ አኢሻ እንዲህ ብለዋል፡- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ነገር ፈጸሙና ያንን ነገር የተፈቀደ ነገር አደረጉት፡፡ ሆኖም ግን ያ ነቢዩ የፈጸሙትን ነገር ማንም አልተገበረውም፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን ሰሙና ለህዝቡ ንግግር ለማድረግ ወሰኑ፡፡ «እኔ ከሰራሁት ስራ ሰው መቆጠቡ ምን ነክቶት ነው? በአላህ እምላለሁ እኔ ከእነሱ በላይ ስለአላህ አውቃለሁ፡፡ እጅግም እፈራዋለሁ፡፡»

እላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ሁኔታዎች በጥልቀት ስንመለከት ሰሀቦቹ ራሳቸውን ከነቢዩ የበለጠ ትክክለኞች አድርገው እንደሚገምቱና እነሱ ትክክል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ደግሞ እንደተሳሳቱ አድርገው ያሰቡበት አጋጣሚዎች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ በተጨማሪም የሰሀቦቹ አቋምና አስተሳሰብ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተግባር ጋር ቢቃረንም አንዳንድ የታሪክ

ጸሀፊዎች ሆን ብለው የሰሀቦችን አቋም ሊያወድሱና የዕውቀታቸውን ደረጃ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዕውቀት ደረጃ በላይ ከፍ አድርገው ሲያስቀምጡ ተስተውለዋል፡፡ በበድር ጦርነት ላይ የተያዙትን የጦር ምርኮኞች አስመልክቶ ነቢዩን ስህተተኛ አድርገው መበየናቸው፤ ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ ትክክለኛ ነበሩ እንደማለት ነው፡፡ የሚቀጥለውን አባባል የመሳሰሉ የተሳሳቱ ተረቶችን ይተርታሉ፡፡ «አላህ በእኛ ላይ ጥፋት ለማስከተል ከወሰነ ከኢብን አል-ኸጣብ በስተቀር ማንም አያመልጥም» በሌላ አነጋገር «ዑመር ባይኖሩ ኖሮ ነቢዩ በጠፉ ነበር» እንደማለት ነው፡፡ ከዚህ ዓይነት አስከፊና አሳፋሪ እምነት አምላክ ይጠብቀን፡፡ የዚህን ዓይነት እምነት የሚከተል በእርግጥ ከእስልምና የራቀ ነውና እምነቱን መልሶ ማሰብና ከሸይጣን መላቀቅ ይገባዋል፡፡ ከሁሉም በላይ የሆነው አላህ እንዲህ ብሏል

«***ዝንባሌውን አምላኩ አድርጎ የያዘውን አላህም ከዕውቀት ጋር ያጠመመውን በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን በዓይኑም ላይ ሽፋን ያደረገበትን ሰው አስተውለሀል? ታዲያ ከአላህ ኋላ የሚያቀናው ማነው? አትገሰፁምን?***» **(ቅዱስ ቁርአን 45:23)**

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የስሜታቸው ተገዥ ስለነበሩ ከትክክለኛው መንገድ እስከማፈንገጥ ደርሰው የሚሰጡትም ውሳኔ ለአላህ አላማ ሲሉ አልነበረም ብለው የሚያስቡትን ወይም የአላህ መልዕክተኛ ከሚሰሩዋቸው ነገሮች እራሳቸውን ከመልዕክተኛው የበለጠ አዋቂና ሃይማኖተኛ አድርገው በመገመት ነገሮችን ከመስራት የሚቆጠቡ ከሙስሊሞች ምንም ዓይነት ክብርና አድናቆት ሊያገኙ አይገባቸውም ብዬ አምናለሁ፡፡ እኒህን ሰሀቦችም ከመላኢካዎች በእኩል ደረጃና ከአላህ መልዕክተኛም በኋላ ከመላ ፍጥረት

ሁሉ ምርጥ ህዝቦችም ተደርገው ተቀምጠዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ሰሀቦች በመሆናቸው ብቻ ሙስሊሞች በአርአያነት እንዲወስዱዋቸውና እንዲከተሉዋቸው ግዴታ ሆነዋል፡፡ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሰለዋት ሲያወርድ ሰሀቦችን በሙሉ ሳይጨምር የቀረ ከአህለል ሱና እምነት እንዳፈነገጠ ይቆጠራል፡፡ አላህ ከሁሉም በላይ ለሆነው ምስጋና ይግባውና ከአደነቃቸውና በትክክለኛው ቦታቸው አስቀምጦአቸው ለመልዕክተኛውና ለጠሩት የቤተሰብ አባሎቻቸው ሰላም እንዲያወርዱ ካዘዛቸው አሜን ብለው ተቀብለው ከአላህ የሚኖራቸውን ቦታ ባወቁ ነበር፡፡ ከሚገባቸው በላይ ትልቅ ቦታ ላይ የምናስቀምጣቸውና አላህ ከሰው ሁሉ መርጦ ከፍ ካደረጋቸው ሰዎች ጋራ የምናስተካክላቸው ለምንድነው?

ኡመያዎችና አባሲያዎች የአህሉል በይትን ደረጃና ቦታ ስለተረዱና አደገኛነታቸውን ስላወቁ አሳደው በመግደልና ለስደት በመዳረግ በስልጣን ላይ የመቆየት ፍላጎታቸውን አሳዩ፡፡ አላህ ምስጋና ለእሱ ይሁንና በአህሉል ቤይት ላይ ሰለዋት ያላወረደ የሙስሊም ሰላት ስለማይቀበል በአህሉል በይት ያላቸውን ተቃውሞ እንዴት ይገልጹታል? ስለሆነም ለህዝቡ ሁለቱም እኩል ናቸው የሚለው ሀሳብ እንዲያድርበት ከአህሉል ቤይት ጋራ ሰሀቦችን ያቀራኛሉ፡፡

በተለይ አለቆቻቸውና ባስልጣኖቻቸው ሰሀቦች እንደነበሩና እነሱም ደካማ ባህሪያት የነበሩዋቸውን ሌሎች ሰሀቦች ደልለው ሰሀቦችንና የሚቀጥለውን ትውልድ በተለይ የኻሊፋ ስልጣን ላይ የደረሱትን (ማለትም ኡማያድና አባሲያ) ለማመስገን የፈጠራ አባባሎችን (የነቢዩን) እንዲያሰራጩ አደረጉዋቸው፡፡ ይህንን ስልጣን እንዲጨብጡና በመላው ሙስሊም ላይ

መሪዎች እንዲሆኑ ያደረጉዋቸው ቀጥተኛ ምክንያቶች እነሱ ነበሩ፡፡ ለዚህ ለምናገረው ነገር ራሱ ታሪክ ምስክር ነው፡፡ በእሱ ስር ባሉት ገዢዎች ላይ በጥብቅነቱ የሚታወቀውና በትንሽ ጥርጣሬ ከሥልጣናቸው የሚያነሳቸው ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ በሙአዊያህ ኢብን አቢ ሱፍያን ላይ ለስለስ ይል እንደነበረና ፍፁም ቀጥቶት እንደማያውቅ ይታወቃል፡፡ ሙአዊያህ የተሾመው በአቡ በከር ሲሆን ሹመቱም እስከ መጨረሻው የፀደቀለት በዑመር ነው፡፡ አብዛኛው ህዝብ በሙአዊያህ ላይ ቅሬታውን ቢያቀርብና በአላህ መልዕክተኛ የተከለከለውን የሀር ልብስና ወርቅ እንደሚያደርግ ቢያመለክትም ዑመር በፍፁም ተቀጥቶም ወቅሶትም አያውቅም፡፡ ለሚቀርቡት ቅሬታዎች ሁሉ ዑመር እንዲህ በማለት ይመልሱ ነበር፡፡ «ተውት እሱ የአረቦች «ኪስራ» (ንጉስ) ነው፡፡ ሙአዊያህን ሳይነካና ሳይተች በገዥነቱ ከሃያ ዓመታት በላይ ቆየ፡፡ ኡስማን የሙስሊሞች ኸሊፋነታቸውን በውርስ ሲረከቡ ተጨማሪ ወረዳዎችና ክልሎቻቸውን ሰጥተውት ስልጣኑ ተጠናከረ፡፡ ይህም ከእስላማዊው ህዝብ ብዙ ሀብት እንዲያካብትና ሰራዊት እንዲያደራጅ ረዳው፡፡ ከዚያም በሀገሪቱ ኢማም (መሪ) ላይ አምጾ በሃይልና በትንኮሳ ሙሉ ስልጣን በመጨረሻ ጨበጠ፡፡ እናም የሙስሊሞች ብቸኛ መሪ ሆነ፡፡ ቆየት ብሎም በሙስና ለተዘፈቀውና በአልኮል መጠጥ ለተነደፈው የዚድ ለሚባለው ወንድ ልጁ ህዝቡ የሱ ተተኪና ወራሽ እንዲሆን የድምጽ ድጋፍ እንዲሰጡ ህዝቡን በሃይል አስገደዳቸው፡፡

ይህ ረጅም ታሪክ በመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ወደ ዝርዝሩ አልገባም፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ቁም ነገር ነቢይነትንና ኻሊፋነትን በበኒ ሀሺም[7] ቤት ውስጥ ለማየት የማይሻውን ቁሬይሽን ለማስደሰት የኸሊፋነት ደረጃ ላይ ደርሰው በቀጥተኛ መንገድ የኡማያድን መንግስት መቋቋምን ያፈጠኑበት

የነዚያን ሰሀቦች አስተሳሰብና አእምሮን መረዳት ያለብን መሆኑ ነው፡፡ የኡማያድ መንግስት ምስረታውን ያፈጠኑለትን ከሁሉም በላይ ስለአለቆቻቸው መልካም ገድልና ስብዕና በተመለከተ ተረቶችን እንዲአወሩ የቀጠራቸውን «ተረት ተናጋሪዎች» በእርግጥ ማመስገን ይገባዋል፡፡ ስለ ገዢዎቹ ትሩፋትና መልካምነት የፈጠራ ተረቶችን በመደስኮር ከጠላቶቻቸው ከአህሉል ቤይት በላይ ገነው እንዲታዩ ተደረገ፡፡ ነገር ግን (አላህ ምስክሬ ነው) አነዚህ ተረቶችና የአሉባልታ ውዳሴዎች በጥሞና ቢመረመሩና በሰከነ አዕምሮ ቢታዩ መሠረት የሌላቸውና ተነው የሚጠፉ ሀሰቶች መሆናቸውን እንረዳለን፡፡ አዕምሮአችን ችግር ከሌለበትና በሚቃረኑ ነገሮች የማመን አባዜ ካልተጠናወተን በስተቀር ግልጽ አሻጥር ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡

ለምሳሌ ስለ ዑመር ፍትሃዊነት «ተረት ተናጋሪዎች» የሚያወሩትን እንሰማለን፡፡ ስለእሳቸውም እንዲህም ተብሎ ነበር፡፡ «በፍትህ መርተሃል፣ ስለሆነም መተኛት ትችላለህ» ፍትህ ከእሳቸው ጋራ እንዳይሞት ተብሎ «ዑመር የተቀበሩት በቁማቸው» ነው ተብሎም ተነግሮ ነበር፡፡ ስለ ዑመር ፍትህዊነት ብዙ ብዙ ተብሏል፡፡ ሆኖም ግን በሂጅራ ሃያኛው ዓመት ላይ እርዳታ ህዝቡ እንዲከፋፈል ዑመር ሲያዙ የአላህ መልዕክተኛን ሱና አልተከተሉም፡፡ ያም ለትዕዛዛቱ እራሳቸውን አላስገዙም ነበር ሲል ትክክለኛ ው ታሪክ ይነግረናል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እርዳታን በእኩል ደረጃ ለሙስሊሞች ሲያከፋፍሉ አንዱን ከአንዱ አይለዩም፡፡ አቡበከርም በኸሊፋነታቸው ጊዜ እንዲሁ ነበር የሚያደርጉት፡፡ ዑመር ግን አዲስ ዘዴ ፈጠሩ፣ አስተዋወቁ፡፡ እስልምናን ከቅርብ ከተቀበሉት ይልቅ ቀደም ብለው ለተቀበሉት አድልተዋል፡፡ የቁሬይሽ ሙሀጂሮችን ከሌሎች ሙሀጂሮች ለይተው ያዩ

ነበር። ከአንሷሮች ይልቅ ደግሞ ለሙሀጂሮች ያደሉ ነበር። በአረቦችና አረብ ያልሆኑ፣ በነጻና በባሪያ እንዲሁም በጎሳዎች መካከል ልዩነት ፈጥረው ነበር።[8] የሙደርን ጎሳ ከራቢያ ጎሳ አስበልጠው ያዩ ነበር። ለሙደር 300 ዲናር ሲሰጡ ለራቢያ ግን 200 ብቻ ይሰጡ ነበር።[9] ከአል-ካዝራጅ ለአል-አውስ አድልተዋል።[10]

አእምሮ ያላችሁ ሰዎች ሆይ! በዚህ ሁሉ አድልኦ ውስጥ ፍትህ የት ነው ያለው? ዑመር ከሰሀቦች ሁሉ በዕውቀት የላቁ እንደሆኑና እንዲያውም ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ያልተስማሙባቸው በርካታ ጉዳዮችን በተመለከተ ብዙ የቁርአን አያቶች ዑመርን በመወገን እንደወረዱ ሁሉ ተወርቷል። ግን ከወረደም በኋላ ዑመር በቁርአን አለመስማማታቸውን አንድ ቀን ከሰሀቦቹ አንዱ «የአማኞች አዛዥ ሆይ! እኔ ንፁህ አይደለሁም፤ ለዉዱዕ ውሃም ሳገኝ አልቻልኩም» ሲላቸው «አትስገድ» ብለው መለሱለት በዚህን ጊዜ አማር ኢብን ያሲር ስለ ተየሙም (በአፈር ዉዱዕ ስለማድረግ) ሲያስታውሳቸው ዑመር ግን ስላላመኑበት አማርን እንዲህ አሉት «አንተ ሃላፊነትህ ለተሰጠህ ስራ ብቻ ነው»[11]

በአላህ መጽሐፍ ውስጥ የወረደውን የ«ተየሙም»ን አንቀጽ አስመልክቶ የት አለ የዑመር እውቀት? በ«ተየሙም» ዉዱዕ እንዴት እንደሚከናወን ያስተማራቸው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና ላይ የዑመር እውቀት የት አለ? በብዙ አጋጣሚዎች ዑመር እራሳቸው ሁሉም ህዝብ ሴቶች እንኳ ከእሳቸው በላይ እውቀት ያላቸው መሆኑንና እሳቸው የተማሩ እንዳልሆኑ በግልጽ ተናግረዋል። ብዙ ጊዜያትም እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል። «አሊ ባይኖር ኖሮ ዑመር ጠፍቶ ነበር»። ታሪክ እንደሚመሰክረው ምንም እንኳን አል-ካላላህን

(ውርስን) አስመልክቶ የተለያዩ ብያኔዎችን ቢያስተላልፍም ዑመር በሕይወታቸው ሙሉ የአል-ካላላህ ህግን ጭራሽ አያውቁትም ነበር።

ስለዑመር ደፋርነትና አካላዊ ጥንካሬም ብዙ ሰምተናል። «እሳቸው ወደ ሃይማኖቱ ሲገቡ እስልምና ይበልጥ ጠነከረ፣ ቁሬይሽም ዑመር ሙስሊም የሆነበትን ቀን ፈራ» ተብሎ ተናግሮአል። «አላህ እስልምናን ከዑመር ጋር አንፀባረቀው፣ የአላህ መልእክተኛ ዑመር ሙስሊም እስኪሆኑ ድረስ ለእስልምና በግልጽ አልተሙዋገቱም» ተብሎ ተነግሯል።

ትክክለኛ የታሪክ መዛግብት ግን ያንን ድፍረት የሚጠቁሙ አይመስሉም እንደ በድር፣ ኡሁድና ከንደቅ ያሉ ዘመቻዎች ውስጥ ዑመር አንድ ታዋቂም ሆነ ተራ ሰው እንኳ ገድለዋል የሚል ታሪክ እስከ አሁን የለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ትክክለኛ የታሪክ መዛግብት የሚነግሩን ተቃራኒውን ነው።

በኡሁድና በሁነይን ዘመቻዎች ጊዜ ከፈሪዎች ጋር ሸሽተው ጠፍተዋል። የአላህ መልዕክተኛ የኸይበርን ከተማ እንዲይዙ በላኩአቸው ጊዜም ተሸንፈው ተመልሰዋል። ሲያገለግሉበት በነበረው ሰራዊት ውስጥ ፈጽሞ መሪ እንኳ ሆነው አያውቁም። በመጨረሻም ዘመቻ ላይ በወጣቱ ኡሰማህ ኢብን ዘይድ ሃላፊነት ስር ውለዋል። ከኒህ ታሪካዊ ሀቆች ጋራ ሲወዳደር ታዲያ ያ ሁሉ ድፍረት የት አለ አእምሮ ያላችሁ ሰዎች ሆይ?

የዑመርን እስከማልቀስ ደረጃ የሚያደርስ ሃይማኖታዊ ጽናትና በአላህ ላይ ስለአላቸው ታላቅ ፍርሃትም እንዲሁ ሰምተናል። መንገዱን ጠርገው ባለማስተካከላቸው እንዲት በቅሎ ኢራቅ ውስጥ ቢያደናቅፋት በአላህ

እጠየቃለሁ ብለው ይፈሩ እንደነበር ተነግሯል:: አንድ ሰው ስለ ቁርአን ጥቅስ ከጠየቃቸው ደም በደም እስኪሆን ከመግረፍ የማይመለሱ እንዲያውም ሴቶች እሳቸውን ባዩ ጊዜ በሚያድርባቸው ከፍተኛ ፍርሃት የተነሳ ያስወርዳቸው እንደነበርና የአላህ ፍራቻ የጎደላቸው ተደባዳቢ ሰው እንደነበሩ ትክክለኛ የታሪክ ምንጮች ይነግሩናል:: መሐመድ ሞተዋል የሚለውን ሰው አልሞተም፤ ልክ እንደሙሳ አምላካቸውን ለማነጋገር ነው የሄዱት እያሉ በአላህ እየማሉ ጎራዴአቸውን አውጥተው ሲያስፈራሩ ለምን አላህን አልፈሩም:: መሐመድ ሞተዋል የሚለውን ሁሉ እንደሚገድሉ አስፈራርተዋል::[12]

ለኸሊፋነት ድምጽ ከመስጠት ተቆጥበው የነበሩት ሰዎች ወጥተው ድምጽ ካልሰጡ የፋጡማ አል-ዛሃራን ቤት እንደሚያቃጥሉ ሲያስፈራሩ ለምን አላህን አልፈሩም?[13] ፋጡማ እቤት ውስጥ እንዳሉ በተነገራቸው ጊዜ «ታዲያ ምን ይሆን» ብለው መመለሳቸውም ተነግሯል::[14]

በኸሊፋነታቸው ወቅትም የአላህን መጽሀፍና የነቢዩን ሱና በመጣስ የቅዱስ ቁርዓንን ትምህርቶችና የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና የሚቃረኑ ህጎችንና ውሳኔዎችን አስተላልፈዋል::

እነዛ ሁሉ የሃይማኖት ጽናቶችና የአላህ ፍራቻ በእነዚህ መራራና አሳዛኝ የታሪክ ሀቆች ውስጥ ታዲያ የት አሉ? የአላህ መልካም አምላኪዎች ሆይ! እኒህን ታላቅና ስመጥር ሰሀባ እንደምሳሌ ወስጃቸዋለሁ:: መንዛዛትን ለማስወገድ ብዙ አሳጥሬአለሁ:: ዘርዘር ባለ ሁኔታ ለማቅረብ ብፈልግ ኖሮ ብዙ ቅጾችን በሞላሁ:: ሆኖም እንዳልኩት እኒህን ታሪካዊ መዛግብት ለምሳሌነት እንጂ ለተለየ ምክንያት የጠቀስኳቸው አይደሉም::